የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች
የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት
የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

ጥራዝ 1

ግንቦት/2011

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ 1

2. ኦዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report/ 4

3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በዘርፍ የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት

   3.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን 40

   3.2 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች 58

   3.3 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች 75

   3.4 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት 102

   3.5 የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች 124

   3.6 የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች 155

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት
ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

I. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲያስችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በኢንጌጅሜነት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ6 የኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፣ የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች፣ የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፣ የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች እና የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች ስር በተደራጁት የሕጋዊነት ኦዲት ስራዎች ተከናውኗል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት የስጋት ደረጃ እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በሪፖርት ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፣ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም ስጋትን ያማከለ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መንግስት መ/ቤትና እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን ምላሽና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡

መ/ቤታችን በሚከተለው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከየካቲት 1/2010 እስከ ጥር 30/2011 ዓ.ም (በጊዜያዊነት የተስተካከለ) የ174 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፤ በመከናወን የኦዲት ሪፖርቶቹ ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፤ በዚህ ጥራዝ የተጠቃለለ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች ቀርቧል፡፡

II. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

ኦዲት በተደረገ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 41 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ 3 መ/ቤቶች ብር 960,832.66 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 2 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 102,532.99 በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ 2/1 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በተለያዩ መ/ቤቶችና ተጠሪ የሆኑ ቅ/ጽ/ቤቶች በርካታ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ-3/ሀ-ሰ እና አባሪ 4፣ 4/1 እና አባሪ 5፣ እና 5/1 ተመልክቷል፡፡

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፤

- በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ እጅ መያዝ ከሚገባው በላይ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት የተገኘ በ2 መ/ቤቶች ብር 694,110.02 መሆኑ፤
- የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ ያላስገቡ በ3 መ/ቤቶች ብር 7,131,997.25 መገኘቱ፣
- የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 525,637,742.86
- በክፍያ መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው በ2 መ/ቤቶችና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 411,532.99 መሆኑ፤
- የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ /ዴቢት/ በ3 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 214,749,495.37 መገኘቱ እና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,150,445.75 መደበኛ ሚዛን ያልሆነ (መክፈቻ ሚዛን) (ክሬዲት ባላንስ) ያለው የጥሬ ገንዘብ የተገኘባቸው፤
- የተጣራ ሃብት ሂሳብ 5601 የመነሻ ምዝገባ ያልተደረገላቸው በ1 መ/ቤት ብር 67,785.40 እና በ1 መ/ቤት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ (4101) የመነሻ ሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገባቸው ብር 10,037.61 መኖሩ፤
- ዓመታዊ ቆጠራ ባለመካሄዱ በሰኔ 30/2010 ሂሳብ ሪፖርት ላይ በካዝና የሚታይ ጥሬ ገንዘብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር495,016.36፤
- በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫ ያልተካተተ በ1 መ/ቤት ብር 74,913,188.22 እና
- የባንክ ማስታረቂያ ሚዛን በትክክለኛ የሂሳብ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የማጠቃለያ ሂሳብና በ1 ቅ/ጽ/ቤት ብር 89,980,491.54 መገኘቱ፤

  የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ በየወቅቱ ቁጥጥር በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲተገበር፤ በኦዲት የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንዲተካ፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2 <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

2.1 <u>በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግገር ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ129 መ/ቤቶች እና በ11 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,252,562,207.37 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ 6 እና አባሪ 6/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	2,316,439.51
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	809,921,206.58
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	1,269,686,923.83
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,394,657,718.74
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	410,241,540.57
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	374,559,559.40
ጠ/ድምር	ብር	**4,252,562,207.37**

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 763,279,769.15፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 2,356,252,611.41፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 524,990,497.56 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 168,604,776.56 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 439,424,322.50 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው፡፡

በተጨማሪም በ8 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,298,391,518.67 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከውዝፍ ተሰብሳቢ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራአመራር ኮሚሽን ብር 608,731,337.69፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 441,828,292.09፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 322,520,418.09፣ የቀድሞ የውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 282,965,014.42፣ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 256,674,976.65፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 250,218,048.94፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 169,647,495.93፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ብር 160,457,088.68፣ ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 153,255,211.99፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 114,611,493.86፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 111,362,647.02፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 108,079,052.31፣ እና ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 102,777,501.69 ይገኙበታል፡፡

የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብም የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 1,203,900,478.44፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 33,064,845.86 እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 23,412,458.30 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡ ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ሆኖ የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም፤ ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው፣ በ10 መ/ቤቶች እና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 52,054,783.31 መሆኑ፣
- በአንድ መ/ቤት ያለአግባብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ የተሰረዘ ብር 9,712,330.24 መኖሩ፤
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለት ተሰብሳቢ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 361,743,928.36 መገኘቱ፤
- በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በተጣራ ሀብት የተመዘገበ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 60,574.43 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ-7 ሀ እስከ ሠ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ/እንዲሰበሰቡ፣ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብላቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግላቸው፣ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3 የገቢ ሂሳብ

3.1 በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ የተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 302,835,172.76፣ በሌሎች በ 59 መ/ቤቶችና 2 ቅ/ጽ/ቤት ብር 54,615,686.58 በድምሩ ብር 357,450,859.34 የንግድ ትርፍ ግብር፤ የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ለመሰብሰብ በሚያስገድዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት ያልተሰበሰበ እና በሌሎች 15

መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ቅጣት ሂሳብ ብር 53,033,612.64 ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-9 እና 9/1 እስከ አባሪ - 9/3 እና 9/4 ተመልክቷል/

ገቢ ለመሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበው ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	302,835,172.76
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	13,058,191.32
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	9,848,324.35
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	18,717,284.32
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	2,324,341.87
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	10,667,544.72
ጠ/ድምር	ብር	**357,450,859.34**

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 129,320,116.87፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 42,103,121.15፤ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,515,511.90፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 25,685,575.29 እና የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 15,699,207.46 ሲሆን፤ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 12,625,775.80፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት ብር 10,666,140.00 እና በፌዴራል የቴክ/ሙያ ትም/ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 5,723,497.08 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፡-

- የመጫኛ/ማራገፊያ፣ የባህር ትራንስፖርት፣ የየብስ ትራንስፖርት እና የኢንሹራንስ ወጪ በትክክል በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ እንዲሁም ማስረጃ ባለመቅረቡ፤
- በግብይት ዋጋ (FOB) ላይ የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ (marine insurance) ወጪ ባለመደመሩ፣

- እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ኮድ ባለመመደባቸው፣
- የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ከጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS) አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ ከ10 በመቶ በላይ በመሆኑ፣
- በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት ያለበት የትራንስፖርት ወጪ በአግባቡ ባለመካተቱ፣
- በትክክለኛ የቀረጥና ታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ እና ተቀናሽ መደረግ የማይገባቸው አግባብነት የሌላቸው ወጪዎች ከገቢ ላይ ተቀናሽ በመደረጋቸው፣
- በ2009 ዓ.ም በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ካሳወቁት ልዩነት ያለው በመሆኑና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ፣
- ያልተከፈለ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር በመኖሩ፣
- ዕቃው በዲክላራሲዮን ላይ በተመዘገበበት ቀን በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት ባለመሰላቱ፤
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በሚቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረት የሽያጭ ገቢያቸውን ባለማስታወቃቸው እና በመሳሰሉት ሲሆን፤
- በሌሎች መ/ቤቶችም ከፈጸሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስር ባሉት በ16 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በ3 መ/ቤቶች ከውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና ውዝፍ የአገር ውስጥ ግብር መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 7,670,055,993.73፣ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ እና በግብር ከፋዮች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ዕዳ ውሳኔ አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ግብር በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 11,323,297,368.69፣ በዋና መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች የፍ/ቤት ውሳኔ ክትትል ምዝገባ መካከል የታየ ልዩነት፤ በአንድ ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,312,069,929.97፣ በቅ/ጽ/ቤቶች የዕዳ ክትትል መዝገብ ላይ አቤቱታቸውን ለዋና መ/ቤት ያቀረቡ የተባሉ ግብር ከፋዮች ቢኖሩም ግብር ከፋዮቹ በዋና መ/ቤት የክትትል መዝገብ ላይ ዝርዝራቸው ያልገኘ የግብር ዕዳ ውሳኔ፣ በአንድ ቅ/ጽ/ቤት ብር 481,837,038.37፣ የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታን በተመለከተ ዋና መ/ቤት ውሳኔው በፍርድ ቤት ክትትል ላይ ያለ መሆኑን መረጃውን የያዘ ሲሆን፤ ቅ/ጽ/ቤች ግን በዕዳ ክትትል መዝገባቸው ላይ መዝግበው ያልያዙ በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 6,895,954,886.08፣ ዋስትና በማስያዝ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም የተያዘው ዋስትና ሂሳብ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ወይም ዋስትናው ያልተራዘመ የቀረጥና ታክስ መጠን በአራት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር109,687,117.26 መኖሩ እና በጉምሩክ አስመጪዎች የቀረበ አቤቱታ ለዋና መ/ቤት የቀረበና አቤቱታ ተገቢው ውሳኔ ሳያገኝ የቆየ የቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 6,699,429.01 በመኖሩ፤ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-8 እና 8/1 እና 8/1 ሀ-ረ ተመልክቷል/

በተጨማሪም የሱቅና የቢሮ ኪራይና በሌሎች ውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ሂሳብ፣ ወለድና ቅጣት በ4 መ/ቤቶች ብር 3,634,488.76፣ የመንግስት ነፃ ሕክምና መብት ተጠቃሚ ከሆኑ ኃላፊዎች ያልተቀነሰ የሕክምና መዋጮ በ4 መ/ቤቶች ብር 16,081.84 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ፤ በአንድ መ/ቤት ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ ብር 379,831.22 እና የአሜሪካ ዶላር 156,536.17 መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 9/1- 9/4 ተመልክቷል፡፡

ውዝፍ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ እና የአገር ውስጥ ግብር እና ታክስ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,452,745,400.00፣ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 991,128,073.20፣ በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 549,978,782.00፣ ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት ብር 484,094,194.69፣ የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 411,555,324.63፣ እና ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር188,798,632.61 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ውዝፍ የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ-ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፣ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በአራት ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 89,033,632.59 ወጪው በዝርዝር የቀረበ ባለመሆኑና ተቀባይነት ያለው ወጪ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም የገቢው ሁኔታ በዝርዝር ሳይገለጽ ከገቢ ላይ የተቀነሰ ወጪ መጠን ዝርዝር ወጪው ሳይገለጽ ከገቢ የተቀነሰው የወጪ መጠን ብር 64,680,345.98፣ በሌሎች 4 ቅ/ጽ/ቤቶች የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ያልተቻለ፣ ብዛታቸው 399 የሆኑ ዲክለራሲዮን በቅ/ጽ/ቤቶቹ ያልቀረበው በገንዘብ መጠን ብር 748,971,389.57 ፤እንዲሁም ዕቃ ወደ አገር ለማስገባት በቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ቀረጥና ታክሳቸው ግን በቅ/ጽ/ቤቱ ሳይሰላ የቆየ፤ በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 50,616,773.33፣

በ7 መ/ቤቶች የማስከፈያ የዋጋ ተመን/ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 12,533,320.71 እና በሌሎች 1 መ/ቤት ብር 12,900.00 በተመኑ መሠረት ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። /ዝርዝራቸው በአባሪ-10 እና አባሪ-14 ተመልክቷል/

ዋና ዋና ምክንያቶቹም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ፣ ወጪው በዝርዝር የቀረበ ባለመሆኑና ተቀባይነት ያለው ወጪ ስለመሆኑ በዝርዝር ሳይገለጽ ከገቢ ላይ የተቀነሰ ወጪ መጠን፤ የተሟላ መረጃና ዲክለራሲዮን ባለመቅረቡ ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በሌላም በኩል ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያለሳወቁ በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች 40 ግብር ከፋዮች እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 34 ግብር ከፋዮች በድምሩ 74 ግብራቸውን ያላሳወቁ በመሆኑ፤ የሚፈለግባቸው ግብር ምን ያህል እንደሆነም፤ ስለመክፈላቸው/ ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 <u>በገቢ ያልተመዘገበና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተተ የገቢ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ10 መ/ቤቶች ብር 157,466,831.46 የገቢ ሂሳብ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች፣ በሶስት መ/ቤቶች በብር 18,041,754.71 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ፣ በ1 መ/ቤት ብር 153,729.19 አለአግባብ በገቢ የተመዘገበ ሂሳብ እና በሌላ 1 መ/ቤት ደግሞ ብር 177,440.00 በድጋሚ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-11 እና አባሪ-14 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	3,497,452.96
የልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች	"	11,467.00
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	132,174,723.20
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	21,783,188.30
በድምር	ብር	**157,466,831.46**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በ3 መ/ቤቶች ብር 2,390,798.60 በትክክለኛው/በተገቢው ሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ፣ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገንዘብ ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 <u>የተሰበሰበው ገቢና ከወጪ ቀሪ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች</u>

በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜውና በሰኔ 30/2009 የሚታየው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት /ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ማጠቃለያ ብር 81,037,046.82፣ ለማዕከላዊ ግምጃቤት ፈሰስ ያልተደረገ የባንክ ሂሳብና በ4 መ/ቤቶች ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ብር 3,389,765.45 በድምሩ ብር 84,426,812.27 ለገንዘብ ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ አባሪ-12 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈሰስ መሆን እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.6 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የመንግስት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር፤የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ኤክሳይስ ታክስና ተርንኦቨር ታክስ በወቅቱ ያላሳወቁ በ4 ቅ/ጽ/ቤ/ቶች 74 ድርጅቶች መገኘታቸው፣
- ዕቃ ወደ አገር ለማስገባት በቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን በወቅቱ ቀረጥና ታክሳቸው ያልተሰላ ወይም ያልተሰረዙ በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ግምት መሰረት የብር 50,616,773.33 ቀረጥና ታክስ መኖሩ፣
- በግብር ከፋዮች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ዕዳ ውሳኔ በተለያዩ አካላት አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ግብር ብር 11,329,996,797.00 መኖሩ፣
- ግብር ከፋዮች ላቀረቡት የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታው በዋና መ/ቤት ውሳኔው ተሰጥቶበት በቅ/ጽ/ቤቶች ግን ቅሬታቸው ውሳኔ ያላገኘ ተብሎ የተያዘ የብር 1,312,069,929.97 የግብር ዕዳ ውሳኔ መኖሩ፣
- በቅ/ጽ/ቤቶች የዕዳ ክትትል መዝገብ ላይ አቤቱታቸውን ለዋና መ/ቤት ያቀረቡ የተባሉ ግብር ከፋዮች ቢኖሩም ግብር ከፋዮቹ በዋና መ/ቤት የክትትል መዝገብ ላይ ዝርዝራቸው ያልተገኘ የግብር ዕዳ ብር 481,837,038.37 መኖሩ፣
- የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታን በተመለከተ ዋና መ/ቤት ውሳኔው በፍርድ ቤት ክትትል ላይ ያለ መሆኑን መረጃውን የያዘ ሲሆን ቅ/ጽ/ቤች ግን በዕዳ ክትትል መዝገባቸው ላይ መዝግበው ያልያዙ የብር 6,895,954,886.08 ሂሳብ መኖሩ፣

- ዋስትና በማስያዝ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም የተያዘው ዋስትና ሂሳብ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ወይም ዋስትናው ያልተራዘመ የቀረጥና ታክስ 109,687,117.26 መኖሩ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩን በአባሪ 8/1(ሀ-ሠ፣ አባሪ 9/ለ እና አባሪ 10 ሀናለ ይመልከቱ/

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም ከላይ የተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

3.7 ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣

- ዩኒቨርሲቲው ለገቢ ማመንጫነት ከሰራቸው ቤቶች ውስጥ ከኪራይ ገቢ መሰብሰብ ሲገባው ለተለያዩ ባለሀብቶች በነጻ ወይም ያለ ምንም ክፍያ የተሰጠ መሆኑን እና ከዩኒቨርስቲው መብራትና ውሃ በነጻ እየተጠቀሙ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይከፍሉ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በ2010 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደው የገንዘብ መጠን ወይም የገቢ መሰረተ-ግምት፣ የሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነትና አገልግሎቱን በመስጠት ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ መጠን በዝርዝር የሚገልጽ የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን፣ የገቢ ዕቅድ ከክንውን ጋር በማነጻጸር ለመገምገም እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብሰብ በሚገባው መጠን የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፣
- ዩኒቨርስቲው የሚሰበስበው ገቢ በሚመለከተው አካል የገቢ ተመን /ታሪፍ ሳይወሰን የሚሰበስብ መሆኑን፣ የገቢ ዕቅድ የማያዘጋጅ (የሌለው) መሆኑን እና በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምርት ዘመን፣ ሴሚስተር በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ መሆኑን፣

- በዩኒቨርሲተው ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምርት ዘመን፣ ሴሚስተር በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

<u>በመቱ ዩኒቨርስቲ፣</u>

- በሂሳብ መደብ 1489 በድምሩ ብር 6,200.00 የውስጥ ገቢ መሰብሰብ ከነበረበት ግዜ (ወቅት) ዘግይቶ የተሰበሰበ መሆኑን እና የውስጥ ቁጥጥሩ ክፍትት ያለው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- ከሙያና ትምህርት ተቋሞች የሰበሰበውን ገቢ ብር 294,886.00 በሂሳብ መደብ 1443 መመዝገብና ሪፖርት ማድረግ ሲገባው በሂሳብ መደብ 1441 ምዝገባው የተከናወነና ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፣

- ስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ባካሄደው ስብሰባ ላይ ለግቢው ማህበረሰብ ለሻይ ቡና አገልግሎት በተዘጋጁ አምስት (5) ቦታዎች ላይ አለአግባብ ገቢ ለመሰብሰብ ሥልጣን ባልተሰጣቸው በተማሪዎች ህብረት በነጭ ወረቀት የሚሰበሰብ መሆኑን እና የገቢውም መጠን ለማወቅ ያልተቻለ መሆኑንን፣

አዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ፣

- የተከታታይ ትምህርት አጠቃላይ ወጪው የሚሸፈነው አገልግሎቱን ከሚያገኙት ተማሪዎች በሚሰበስበው ገቢ መሆን ሲገባው ብር 166,714.00 የተከታታይ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተባበሩ ኃላፊዎችና ትምህርቱን ላስተማሩ መምህራን ከመደበኛ በጀት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ፣

- በግቢው ውስጥ አምስት (5) ማህበራትና ግለሰቦች ኪራይ ሳይከፈሉ፣ እንዲሁም የመብራትና ውሃ በነጻ እየተጠቀሙ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይከፍሉ መሆኑን፣

3.8 <u>የገቢ ሂሳብ ዕቅድ አፈጻጸም</u>

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በዕቅድ የያዙትን ገቢዎች የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ሀ/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት፡

-ብር 54,049,425,657.14 (23%)

ለ/ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 191,588,705.98 (38%) ከዕቅዱ በታች ወይም በዕቅዱ መሰረት ያልተሰበሰ ገቢ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 16 ተመልክቷል፡

በመሆኑም ለመ/ቤቶቹ የገቢ ዕቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት እንዲሰበሰብ እሳስበናል፡፡

4 <u>የወጪ ሂሳብ</u>

4.1 <u>ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ27 መ/ቤቶች ብር 413,280,996.45 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	6,784,074.74
አቅም ግንባታ መ/ቤት	"	142,840,824.60
የልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች	"	19,133,218.94
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	319,785,192.06
በድምሩ	**ብር**	**413,280,996.45**

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ብር 134,472,633.18፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 129,001,549.44፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 53,772,357.80፣ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 95,100,095.07፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 41,937,315.62 እና የቀድሞው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 13,456,488.42 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ፣ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ63 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 1,475,867,250.28 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 17 ተመልክቷል/ ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	850,678,819.23
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	1,916,979.53
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	103,645.21
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	85,007,096.62
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	516,299,420.06
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	21,861,289.63
በድምሩ	ብር	**1,475,867,250.28**

ሆኖ ተገኝቷል።

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች፤ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 842,885,505.51፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 356,715,318.54፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 129,587,507.28፣ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,381,996.90፣ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ብር 18,952,906.73፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,663,770.37፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 9,329,585.59 እና የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ብር 8,805,060.25 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፣ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ፣ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጉላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ77 መ/ቤቶችና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 145,676,300.91 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	2,777,149.94
በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	394,192.73
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	44,848,365.62
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	94,092,844.08
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	1,125,120.38
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,438,628.16
በድምሩ	ብር	**145,676,300.91**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- ትምህርት ሚኒስቴር ብር 73,982,403.47፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 10,569,744.81፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,960,196.57፣ ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ብር 7,671,634.60፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,507,155.91፣ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,196,212.00 እና ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,001,671.53 እና ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,317,438.53 ሲሆኑ፣ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት በሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ በ8 መ/ቤቶች በመስሪያ ቤቱ ለሌሉና ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ ብር 122,920.11 እና በሌሎች በ8 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብር 13,904,355.05 የስራው ባህሪ በቋሚነት ወይም ቀጣይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ፣

እንዲሁም በ29 መ/ቤቶች ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 41,703,125.15 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-19/1 እና አባሪ-19/2 ተመልክቷል/

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ገንዘብ ከሚመለከታቸው ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ4 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 3,266,061.85 እና በ55 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 28,865,144.17 በጠቅላላው ብር 32,141,206.02 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡
በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡትን ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፣ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.5 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ100 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 956,822,601.96 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 21 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	580,832,851.55
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	7,925,158.76
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	13,490,558.78
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	91,694,070.66
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	129,735,606.19
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	133,144,356.02
በድምር	**ብር**	**956,822,601.96**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡- ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 802,199,221.84፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 5,937,639.38፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 78,267,524.87፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 18,393,839.63 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 52,024,352.94 ናቸው፡፡ ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፡- ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 556,832,185.29፣ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 43,360,623.00፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 96,974,563.35፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 18,697,650.65፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 17,927,784.00፣ ወራቤ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,574,142.14፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,663,136.22፣ የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ብር 15,415,976.04 እና ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,956,353.16 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ በ11 መ/ቤቶች የብር 21,628,420.99 መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ 21/1 ተመልክቷል፡፡/

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.6 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ20 መ/ቤቶች በብር 2,006,431,091.87 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ6 መ/ቤቶች ብር 1,361,059,364.44 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ 22 እና አባሪ 22/1/ሐ ተመልክቷል/

ገቢ ያልሆነው ንብረት ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		174,050.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	1,939,546,380.97
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	5,113,574.43
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	35,020,535.36
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	26,576,551.11
በድምሩ	ብር	2,006,431,091.87

ከዚህም ውስጥ የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,928,982,791.60፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 35,020,535.36፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,442,455.35፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ብር 10,151,406.77 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ወይም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ ማስረጃ ካላቀረቡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸውም፡-

የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,311,908,803.11 እና የጤና ሚኒስቴር ብር 23,969,464.20 እና የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 22,173,426.52 ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ላወጣው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ10 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 186,009,704.35 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 28 ተመልክቷል/

የቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል፡- ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 116,821,986.39፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 41,573,161.15፣ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ብር 15,437,979.87 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 6,078,078.54 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ የግንባታ ክፍያዎችም በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት ከእያንዳንዱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተቀንሶ ለመንግሥት ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ86 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 252,767,992.68 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	6,215,275.76
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	7,261,257.66
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	24,640,359.14
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	41,897,945.59
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	13,950,444.23
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	158,802,710.30
በድምር	ብር	**252,767,992.68**

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል፡- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 71,281,322.37፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 53,540,259.43፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,442,455.35፣ በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 14,303,722.18 እና የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ብር 7,819,589.91 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡ የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ34 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 257,621,118.90 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2010 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	73,116,748.19
የፋይናንስን ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	66,690,494.85
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	115,253,819.67
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,560,056.19
በድምሩ	ብር	257,621,118.90

ሲሆን፤ ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት ዓመቱ ለተገኘ አገልግሎት ወጪውም በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ/ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 65,725,429.61 የወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ወይም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 23 ተመልክቷል/

ከዚሁ የወጪ የሂሳብ ሪፖርት ጋር በተያያዘ በ12 መ/ቤቶች ብር 5,092,228.55 በድጋሚ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ እና በ4 መ/ቤቶች ብር 591,780.44 በብልጫ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 389,549.42 በማነስ የተመዘገበ እና በ1 መ/ቤት ደግሞ ብር 120,193.48 ያልተመዘገበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡ በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለአመዘጋገብ ስህተቶቹ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች፤

ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የወጡ የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተከናወኑ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ስምምነት ያልቀረበለት በ1 መ/ቤት ብር 18,629,844.49፣ በአዋጁ መሠረት በዋና ውል ላይ 25% በማስላት ብቻ ተጨማሪ ውል መግባት ሲገባው ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ውል የተገባ በ1 መ/ቤቶች ብር 9,001,699.77፤ የግንባታ ሥራዎች ክፍያ ከ 30% በላይ ብር 1,270,586.85 ጭማሪው (38.84%) ተከፍሎ መገኘቱ፤
- ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ በ1 መ/ቤት ብር 5,106,668.90፤
- በ4 መ/ቤቶች ብር114,959,683.05 ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያ ሠርተፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ መገኘቱ፤
- በግንባታ አማካሪ ድርጅት ባልተዘጋጀና ባልጸደቀ የክፍያ ሰርተፍኬት የተከፈለ ክፍያ በ1 መ/ቤት ብር 36,238,839.25 ወጪ መሆኑ፤
- ለሕንጻ ተቆራጮች የብረትና ሲሚንቶ ቅድሚያ የተሰጠ ቢሆንም የመከታተያ ሌጀር ያልተዘጋጀ በ1 መ/ቤት ብር 53,130,865.05 መገኘቱ፤

- በውላቸው መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁ የግንባታ ፕሮጀክቶች፣ በ3 መ/ቤቶች ሳይጠናቀቁ የተቀረጡ 12 የግንባታ ፕሮጀክቶች፤ (በገንዘብ መጠን ብር 265,681,830.82) የሆኑ፤ እና በግንባታ ሂደት ያሉ ግን ከማጠናቀቂያ የውል ጊዜያቸው በላይ የዘገዩ በ7 መ/ቤቶች 55 የግንባታ ፕሮጀክቶች እንደሚገኙ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ 20/1 እስከ አባሪ 20/5 ተመልክቷል/

በመሰረቱ ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰብሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ የግንባታ ክፍያ በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት መቀነስ ነበረበት፡፡ ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ አገልግሎት ሳይገኝ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

በመሆኑም የማማከር ስራዎችም ገለልተኛና የሙያ ብቃት በተሰጣቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን ተጨማሪ ውል ሲያስፈልግም ሕጉ በሚፈቅደው ልክ እንዲሆንና በአጠቃላይ የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ፣ የተቀረጡ ፕሮጅክቶች ላይ አሰፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድና የዘገዩት እንዲጠናቀቁ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

4.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ19 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 25,367,673.85፣ በ1 መ/ቤት ደግሞ ብር 4,172,688.00 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አጽድቀው መገኘቱ እና በ17 መ/ቤቶች በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች ብር 17,670,108.12 መገኘቱ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-26 እና 26/1 እና አባሪ 33/ለ ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፣ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፣ ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያጋልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል።

4.13 ሌሎች ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዘ የሚታዩ ችግሮች

4.13.1 የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ

ከተለያዩ የግንባታ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን የተጠናቀቁት የግንባታ ሥራዎች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በ10 መ/ቤቶች የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜያቸው የዘገየ 55 ፕሮጀክቶችና በ2 መ/ቤቶች የግንባታ ሂደታቸው የተቋረጠ መሆኑ ተውቋል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ 20/5 ተመልክቷል/ በተጨማሪም፤

- **የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ** በመከናወን ላይ ያሉ የኮንስትራክሽንና የመሠረተ-ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቀው ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን ወይም አገልግሎት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ግንባታዎች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ37 እስከ 188 ቀናት የዘገዩ መሆኑን፣
- **በመቱ ዩኒቨርሲቲ፡-**
  ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት የፈርኒቸር ዕቃዎች ግዥ ብር 14,765,020.84 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ የውሉ አንድ አካል ሆኖ በግልፅ በውሉ ያላስቀመጠ በመሆኑ በውል ክፍተት ምክንያት የጉዳት ካሳ ለማስላትና ለመጠየቅ የማያስችል መሆኑን፣
- **አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣**
  - ያስገነባቸውን ግንባታዎች (ህንፃዎች) እንደቋሚ ንብረት በመዝገብ የማይመዘግብ መሆኑን፣

- በመከናወን ላይ ያሉ የኮንስትራክሽንና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው (በተቀመጠለት) የጊዜ ገደብ መሰረት ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣
- በድምሩ ብር 2,291,218.30 የሚያወጣ ሲሚንቶ በተቋራጮቹ በቀረበ መረጃ ብቻ የተቀነሰ ለመሆኑ እና በእያንዳንዱ ተቋራጭ የተወሰደው የሲሚንቶ ዕዳ በተሰብሳቢ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) የማይያዝ (የማይመዘገብ) መሆኑን፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት፣ የግንባታ ውል ሲዘጋጅ የዩኒቨርስቲውን ጥቅም የሚያስጠብቁ ሁኔታዎች በውል እንዲካተቱ፣ በቅድሚያ የሚሰጡ ስሚንቶና ሌሎች ዕቃዎች በተሰብሳቢ ሊያዙና በወቅቱ እንዲወራረዱ መደረግ የሚገባው እና ሕንጻዎች በተሰጣቸው ቁጥር መሠረት በንብረትነት መመዝገብ እንደሚገባቸው አሳስበናል፡፡

5 የተከፋይ ሂሣብ

5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በገ/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-በ88 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,301,454,860.35 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	231,874,492.83
የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	40,868,202.31
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	198,572,016.98
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	709,413,407.68
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	105,230,484.85
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	15,496,255.70
ድምር	**ብር**	**1,301,454,860.35**

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡

የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታ ጊዜው ሲተነተን፡- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 230,432,305.20፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 304,489,394.63፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 232,452,595.52 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 7,968,195.76 ሲሆን፣ ቀሪው ሂሳብ ብር 526,112,369.24 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡ በተጨማሪም በ9 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 385,575,238.97 በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ ቢሆንም ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/ በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 445,781,634.00፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 213,767,213.72፣ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 125,843,637.00፣ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ብር 107,026,553.84፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ብር 59,896,212.41፣ መደወላቡ ዩኒቨርስቲ ብር 58,638,207.92 እና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 5,228,032.65 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የተከፋዩን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለባቸው መ/ቤቶች፡- የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 218,576,198.26፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 48,305,103.58 እና ምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ብር 61,164,814.07፣ አዲስ አበባ ኤርፖርት ብር 24,455,940.54 እና የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር 15,472,158.61 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑ እየተጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ሌሎች ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በብልጫ ሪፖርት የተደረገ የተከፋይ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 192,046.79 መገኘቱ፣

- በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 3,126,737.51 መገኘቱ፣ (አባሪ-27/1)
- መደበኛ የመነሻ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ(ዴቢት ሚዛን) የተከፋይ ሂሳብ በ1 መ/ቤት ብር 114,823.52 መገኘቱ፤
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ12 መ/ቤቶችና በአንድ ቅ/ጽ/ቤት ብር 64,634,272.14 መኖሩ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 325,344,429.30 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6 <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 <u>ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ</u>

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ53 መ/ቤቶችና 10 ቅ/ጽ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 312,314,378.22 ፣ የውስጥ ገቢ ብር 10,676,983.96 እና ከካፒታል በጀት ብር 208,375,565.99 በድምሩ ብር 531,366,928.17 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	ብር	9,047,293.14
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች		585,176.68
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	300,402,340.56
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	186,028,562.22
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		7,750,358.94
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	27,553,196.63
ጠ/ድምር	ብር	**531,366,928.17**

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፣ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 111,987,647.53 ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 79,615,377.18፤ የፌ/ቴክኒክና ሙያ ት/ትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር76,710,149.04፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ብር38,598,157.84 ፤የወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 35,664,551.36፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ብር 29,063,652.11፤ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 26,797,772.27 እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 23,487,495.67 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ17 መ/ቤቶች ብር 17,670,108.12 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች፡- በ5 መ/ቤቶች ብር 26,195,153.19 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የበጀት ዝውውር የፈፀሙ እና በ3 መ/ቤቶች ብር 66,929,084.32 ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበን ሂሳብ በጀት ሳያስፈቅዱ ወጪ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተጠቀሙበትን ብቻ በመውሰድ በ156 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 6,480,797,414.15፣ የውስጥ ገቢ ብር 99,029,157.37 እና ካፒታል ብር 8,250,647,805.65 በድምሩ ብር 14,830,474,377.17 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	2,274,735,273.31
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	452,252,633.56
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,052,896,011.44
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	3,783,581,128.68
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	3,304,106,362.84
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	2,962,902,967.34
ጠ/ድምር	ብር	**14,830,474,377.17**

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- ትምህርት ሚኒስቴር ብር 1,814,291,032.86፣ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 1,678,256,147.22፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ብር 785,140,206.00፣ አዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 573,497,035.94፣ የቀድሞው የስትራቴጂ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ ብር 536,591,781.98፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 506,085,595.77፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 452,252,633.56፣ አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 444,208,233.70፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 419,859,663.02፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 417,400,462.94፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 353,343,805.89 እና ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብር 320,079,284.82 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 34/ሀ እስከ አ ተመልክቷል፡፡/

የግኝቶች መግለጫ	መ/ ቤቶች	ቅ/ጽ/ ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	45	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	35	3
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	17	3
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	19	4
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	35	4
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	62	4
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	80	13
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	36	2
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	24	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው፡- 157 የተለያዩ ተሽከሪካሪዎችና 24 ሞተር ብስክሌቶች ሲሆን፤ በ4ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት ያልተገለጸ	1	11
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለጹ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር2,956,884.52 ይገኙበታል)	28	
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤	2	
የንብረት ጉድለት የተገኘባቸው ፤ ዋጋቸው ብር 20,346.01 እና 1 ታብሌት ኮምፒዩተር፣ 18 የላቦራቶሪ ዕቃዎች	2	1
በዱቤ ተሰጥቶ ተመላሽ ያልተደረገ ንብረት(ዋጋቸው ብር 210,220.76 የሆነ)	1	
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	6	6

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡

አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል። እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸውና ሊወገዱ የሚገባ የተለያዩ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች በበርካታ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በእያንዳንዱ የኦዲት ሪፖርት በዝርዝር እና ዋና ዋናዎቹም በየዘርፍ የንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል።
በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፣ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	29/ 3ቅ*	174	41
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	37	373/4	42
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	7/ 1ቅ*	11	28/63*
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	26	300	21
የሻንሲ ቁጥር የሌላቸው	1	1	
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	2/ 1ቅ*	31	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	3	2	1

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ያለው			
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው/ጌጅ/ የማይሰራ	4	11	
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	4	10	11
በኃላፊ ተወስዶ ተመላሽ ያልተደረገ ተሽከርካሪ	2	3	
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	3/ 1ቅ*	14	2

ቅ*- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች * ሌሎች- ቦክሰር፤ጂያንሺ፤ዚንግሸ፤ ትራክተር

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 /ሀ እስከ ቀ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፣ ሊብሬ እና ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው እንዲወጣላቸው፤ በኃለፊዎች ተወስደው ያልተመለሱትም ተመላሽ እንዲደረጉ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8. ባለፊው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

በ2009 በጀት ዓመት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

በ108 መ/ቤቶች እና በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች/ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት የተሰጠበት ብር 228,717,664.13 ውስጥ ተመላሽ የተደረገ ብር 12,536,323.36 እና በሁለት መ/ቤቶች ተመለሽ ተደርጎል ቢባልም ያልተረጋገጠ ብር 13,697,724.66 ብቻ ሲሆን ቀሪው ብር 216,225,140.67 በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልተወሰደበትና ተመለሽ ያልተደረገ መሆኑ ተውቋል፡፡ አሁንም ትኩረት እንዲሰጥበቸው ያሀል ፤ዝርዝሩ በአባሪ-36 ተመልክቷል፡፡

የገቢ ሂሳብን በተመለከተም የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና በስሩ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 198,199,027.59 በኦዲት ተገኝቶ እንዲሰበሰብ አስተያየት ከተሰጠበት በ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት መሰብሰቡ የተረጋገጠ ብር 59,966,560.87 ብቻ ሲሆን ቀሪው ብር 138,232,466.72 በኢዲት አስተያየቱ መሰረት አልተሰበሰበም፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ
የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 መሰረት ፤የባለስልጣኑን የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት በማድረግ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋና መ/ቤትን፣ የአስራ ሰባት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብን ኦዲት አድርገናል፡፡

ሀ/ የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

የኦዲት ዕቅድና ክንውን፡- የዋና መ/ቤትን፣ የአስራ ሰባት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብን ኦዲት ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡

ተ/ቁ/	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት			የገቢ በጀት
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር	
1	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	2,327,151,431	218,836,739	2,545,988,170	229,999,988,683

የተሰጠው የኦዲት አስተያየት፡- የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse opinion/ ነው፡፡

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ

1.1 በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ውጤትና በሂሳብ መግለጫ መካከል ስለታየው ልዩነት፣

በሰኔ 30/2010 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በውስጥ ኦዲት መረጋገጡን እና ከሂሳብ መግለጫ ጋር መመሳከሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች በውስጥ ኦዲት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ሪፖርት በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ከታየው በማነስ ብር 102,532.99 የሚታይ መሆኑታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ- 2/1 ተመልክቷል)

በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ከተቆጠረው ጥሬ ገንዘብ በብልጫ ልዩነት ለታየው ሂሳብ የልዩነቱ ምክንያት ተጣርቶ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባና ጉድለት መሆኑ ከተረጋገጠ ከሚመለከተው ሰራተኛ ተመላሽ እንዲሆን በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የፌደራል መንግስት የሂሰብ አያያዝ መመሪያ መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ማለትም በሰኔ 30/2010 በጀት ዓመት በእጅ ወይም በሳጥን ያለ ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ በወቅቱ በነበረው የጥሬ ገንዘብ መጠን ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣ በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት የሚረጋገጥ መሆኑን፣ እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ሰኔ 30/2010 ላይ ዓመታዊ ቆጠራ ባለመካሄዱ ምክንያት በሪፖርቱ ላይ የሚታየው ጥሬ ገንዘብ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ ያልተቻለ በአንድ ቅርንጫፍ ብር 495,016.36 መኖሩ፣

- በባንክ ያለ ገንዘብ (cash at bank) ብር 525,637,742.86 ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም በአንድ ቅ/ጽ/ቤት በሪፖርቱ ላይ የሚታየውን የባንክ ሚዛን ትክክለኛ ስለመሆኑ የባንክ ስቴትመንት ማስረጃ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ሊያቀርብልን ባለመቻሉ በሪፖርቱ የሚታየውን የባንክ ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- በሰኔ 30/2010 የተዘጋጀው የባንክ ማስታረቂያ ሚዛን በትክክለኛ የሂሳብ መረጃ ላይ ተመስርቶ ያልተዘጋጀ በሁለት ቅ/ጽ/ቤት ብር 89,980,491.54 ትክክለኛነት አለመረጋገጡ፣
- የተጣራ ሀብት (Net Asset/Equity) በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ክሬዲት ሆኖ ሳለ በ 7 **ቅ/ጽ/ቤቶች** በሂሳብ መደብ 5601 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሀገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ ብር 194,724,298.47 እና የጉምሩክ ገቢ ሂሳብ ብር 15,711,451.19 በድምሩ ብር 210,435,749.66 የሚታይ መሆኑ፣
- ከሀገር ውስጥ ገቢ እንዲሁም ከጉምሩክ ቀረጥና እና ታክስ የተሰበሰበ ገንዘብ ብር 81,037,046.82 በወቅቱ ፈሰስ አለመደረጉ፣
- ጥሬ ገንዘብ በባንክ፣ በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብና የጥሬ ገንዘብ ጉድለት በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ዴቢት ሆኖ ሳለ በሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላይ በአጠቃላይ ብር 1,150,445.75 ትክክለኛ ባልሆነ ሚዛኑ ክሬዲት ሆኖ ሪፖርት የተደረገው ሂሳብ ማስተካከያ የተደረገበት ማስረጃ ሳይኖር በባለስልጣኑ ማጠቃለያ ሪፖርት ላይ ከሌላው ሂሳብ ጋር በማጣፋት በትክክለኛው ሚዛኑ በዴቢት እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩን ከአባሪ- 3-5 ይመልከቱ/

የሂሳብ መደብ ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ እና ወደ ማጠቃለያው በትክክል ያልዞረበት ምክንያት ሊጣራ እና አስፈላጊው ማስተካከያ ሊሰራእንደሚገባ፣ በባንክ እና በመዝገብ ላይ የታየውን የገንዘብ ልዩነት ምክንያቱን አጣርቶ አስፈላጊውን የሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ፣ የተሰበሰበ ገቢን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ማድረግ እንደሚገባ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ፡-

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ እንደሚሰበሰብ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-በ **4 ቅ/ጽ/ቤቶች** ሳይሰበሰብ የቆየ ብር **2,316,439.51** ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታይቷል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው፣

ተ.ቁ	የቆየበት ጊዜ	የገንዘቡ መጠን
1	ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት	3,420.64
2	ከ 1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	300,253.33
3	ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት	2,012,765.54
	ድምር	**2,316,439.51**

መሰብሰብ የሚገባውም የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ መሰብሰብ የሚኖርበት መሆኑንና ሊሰበሰብ የማይችል ሂሳብ ከሆነ በፋይናንስ ህግና ደንቡ መሰረት ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.2 ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- **በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች** ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ ብር **26,436,912.46** ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ /ዝረዝሩን በአባሪ6/1 ይመልከቱ/

መሰብሰብ የሚገባው የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ መሰብሰብ የሚኖርበት ሲሆን ማስረጃ የሌለውና ሊሰበሰብ የማይችል ሂሳብ ከሆነ በፋይናንስ ህግና ደንቡ መሰረት ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሥራ አመራር ሪፖርት ገልጸናል፡፡

3. የገቢ ሂሣብ

3.1 ያልተሰበሰበ ውዝፍ

በተለያዩ አካላት ማጣራት መሰረት የተገኘ ያልተሰበሰበ የመንግስት ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ለመሰብሰብ ቅ/ጽ/ቤቶቹ እየሰሩ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በየቅ/ጽ/ቤቱ በ 2010 በጀት ዓመት የታየው የእዳ መጠን እና በባለፉት አመታት እንዲሰበሰብ ተብሎ በዋና ኦዲተር መ/ቤት አስተያየት የተሰጠበት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ሳይሰበሰብ የቆየ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ፣

- የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በ 10 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,570,966,644.79 መኖሩ፣
- በ 10 ቅ/ጽ/ቤቶች ሳይሰበሰብ በመቆየቱ ምክንያት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደበት የግብር ዕዳ ብር 6,045,627,423.60 በድምሩ ብር 7,616,594,068.39 ከአንድ ዓመት እስከ 10 ዓመት እድሜ ያለው ውዝፍ እዳ መኖሩን ለማየት ተችሏል::/ዝርዝሩን በአባሪ 8 ይመልከቱ/

የቅ/ጽ/ቤቶቹ ዕዳ ክትትል ቡድን ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የውሳኔ ማስታወቂያ ወጥቶላቸው ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑ ግብር ከፋዮች ላይ ያለባቸውን ዕዳ ለመሰብሰብ ቀጣይ እርምጃቸውን በመውሰድ ውዝፍ ዕዳውን ሊሰበስቡ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.2 በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ

በገቢ ግብር አዋጅ፣ በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በጉምሩክ አዋጅ፣ በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፊያ ዋጋ አተማመን መመሪያ እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም በወጡት ደንብና መመሪያዎች መሰረት የመንግስት ገቢ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መሰብሰብ ቢኖርበትም በየቅ/ጽ/ቤቶች በአዋጆቹና በመመሪያዎቹ መሰረት በትክክል ባለመሰራቱ ብር 302,810,291.52 ያልተሰበሰበ ገቢ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩን በአባሪ 9 ተመልከቱ/

የገቢ ሂሳቡ ያልተሰበሰበበት ምክንያትም፤

- የመጫኛ/ማራገፊያ፣ የባህር ትራንስፖርት፣ የየብስ ትራንስፖርት እና የኢንሹራንስ ወጪ በትክክል በቀረጥና ታክስ ማስከፊያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ እንዲሁም ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
- በግብይት ዋጋ (FOB) ላይ የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ (marine insurance) ወጪ ባለመደመሩ፣
- እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ኮድ ባለመመደባቸው፣
- የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ከጉምሩክ የዋጋ መረጃ ስርዓት (ECVS) አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ልዩነቱ በማነስ ከ10 በመቶ በላይ በመሆኑ፣
- በቀረጥ ማስከፊያ ዋጋ ላይ መካተት ያለበት የትራንስፖርት ወጪ በአግባቡ ባለመካተቱ፣
- በትክክለኛ የቀረጥና ታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ፣
- ዕቃው በዲክላራሲዮን ላይ በተመዘገበበት ቀን በዋለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት ባለመሰላቱ፣

- ተሸከርከሪዎች ምንም አይነት አገልግሎት ካልሠጡ የእርጅና ተቀናሽ ሳይደረግ በአዲስ ዋጋ መሠረት ቀረጥና ታክስ መሰራት ሲገባው የእርጅና ቅናሽ በመካተቱ፣
- የቀረጥ ነጻ ማስረጃ ሳይቀርብለት ከቀረጥና ታክስ ነፃ በመግባቱ፣
- የዕቃው ዋጋ በዕቃዎች አካላዊ ፍተሻ ሪፖርት መሰረት ባለመሰራቱ፣
- በአየር ማጓጓዣ ክፍያ አንድ ሦስተኛው እና የማራገፊያ የመንከባከቢያ ወጪ ቀጥታ ተወስዶ ባለመሰራቱ ፣
- ለረዥም ዓመታት በፖስታ አገልግሎት ድርጅት ስም በተሰብሳቢ ተይዞ ለቅ/ፅ/ቤቱ ገቢ ያልተደረገ ቀረጥና ታክስ መኖሩ፣
- በ2009 ዓ.ም በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ካሳወቁት ልዩነት ያለው በመሆኑና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ፣
- ከ2008 የግብር ዘመን መዞር ያለበት ያልተሸጠ ወይም በምርት ሂደት ላይ ያለ ዕቃ/ending inventory ወደ 2009 የግብር ዘመን በሚዞርበት ጊዜ ከፍ እንዲል በመደረጉ፣
- ተቀናሽ መደረግ የማይገባቸው አግባብነት የሌላቸው ወጪዎች ከገቢ ላይ ተቀናሽ በመደረጋቸው ፣
- ያልተከፈለ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር በመኖሩ፣
- የጥገና እና የማሻሻያ ወጪ አቀናነስ ስሌቱ በህግ በተደነገገው መሰረት የተሰላ ባለመሆኑ፣
- የእርጅና ቅናሽ በትክክለኛው ስሌት መሰረት ባለመሰላቱ፣
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ግብር ከፋዮች ተቀናሽ የተደረገው ቅድመ-ግብር በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት የተፈጸመ ባለመሆኑ ፣
- ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በሚቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረት የሽያጭ ገቢያቸውን ባለማስታወቃቸው፣

- የተከፈለበት ማስረጃ ሳይቀርብ በቅድመ-ግብር ተከፋይ ሂሳብ ምክንያት ተቀናሽ የተደረገው ቅድመ ግብር በመኖሩ፣
- በአግባቡ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ በመኖሩ፣
- ግዢን አስበልጦ በማሳወቅ፣
- በንግድ ሥራ ግብር ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በ Z ሪፖርቱ ከታየው የዓመቱ ሽያጭ ጋር ልዩነት በመኖሩ ፣
- እንደ ወጪ ተቀናሽ መደረግ የሌለበት የውጭ ሀገር ምንዛሪ ኪሳራ ተቀናሽ በመደረጉ፣
- በሂሳብ መግለጫው ላይ ባሳውቁት የተጣራ ገቢ መሰረት የንግድ ትርፍ ግብራቸውን እንዲከፍሉ ባለመደረጉ፣
- በ 2008 ዓ.ም የግብር ዘመን መጨረሻ በቅድመ ክፍያ የተያዘ ሂሳብ በ 2009 ዓ.ም የግብር ዘመን ቢቀንስም በቀነሰው መጠን በገቢ እንዲያዝ ባለመደረጉ፣
- ያልተፈቀደ የኤክሳይዝ ታክስ ተቀናሽ በመያዙ፣
- ለዕቃዎች ማምረቻ የዋሉ ግብአቶች ወደ አገር ሲገቡ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተብሎ ተቀናሽ የተደረገው በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ወለድና መቀጫን በመጨመር ከአስመጪዎች መሰብሰብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡ ለወደፊቱም ቅ/ጽ/ቤቶቹ በአዋጆቹን ደንቦቹ መሰረት ለመስራት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን አስገንዝበናል፡፡

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ የገቢውን ትክክልኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

ለኦዲት ስራ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ሲጠየቁ በተሟላ ሁኔታ ሰነዶችን ያላቀረቡ በመሆኑ፣

- በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሰነዶቹ/በዲክላራሲዮኖቹ ላይ የተሰበሰበው ገቢ በድምሩ ብር 748,971,389.57 ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፤
- ከገቢ ላይ ተቀናሽ የሚደረጉ የጥገናና የማሻሻያ ወጪዎችና ሌሎች የተለያዩ ወጪዎች በግልጽና በዝርዝር የተገለጹ ባለመሆኑ እንዲሁም አንዳንድ ወጪዎች ተቀባይነት ያላቸው ወጪዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ በድምሩ ብር 64,680,345.98 መኖሩ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩን በአባሪ 10 ሀናለ ይመልከቱ/

ስለሆነም ግብር ከፋዮች ገቢያቸውን በሚያስታውቁበት ጊዜ ለቋሚ ንብረት ጥገናና ለማሻሻያ ያወጡትን ወጪ በየቋሚ እቃ አይነቱ በዝርዝር መገለጽ እንዳለበት፣ ሌሎች ወጪዎችን በተመለከተ በተዘጋጀው የባለስልጣኑ ቅፅ ላይ ወጪው ዝርዝር መሞላቱን እና የወጪው ምንነት ተረጋግጦ ወጪዎች በትክክል መቀነሳቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ የሚገባ መሆኑን፣ ለኦዲት ያልቀረቡ ፋይሎች በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ ተደራጅተው መቀመጥ ያለበት መሆኑንና ያልቀረቡት ሰነዶችም በድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ተደርገው በውስጥ ኦዲት ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ገቢ ያልተደረገው ግብር ካለ ገቢ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች

የመንግስት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር፤የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ኤክሳይስ ታክስና ተርንኦቨር ታክስ በወቅቱ ያላሳወቁ በ4 ቅ/ጽ/ቤ/ቶች 74 ድርጅቶች መገኘታቸው፣

- ዕቃ ወደ አገር ለማስገባት በቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን በወቅቱ ቀረጥና ታክሳቸው ያልተሰላ ወይም ያልተሰረዙ በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ግምት መሰረት የብር 50,616,773.33 ቀረጥና ታክስ መኖሩ፣
- በግብር ከፋዮች ቅሬታ/አቤቱታ የቀረበበት የግብር ዕዳ ውሳኔ በተለያዩ አካላት አስፈላጊው ውሳኔ ሳይሰጥበት የቆየ ግብር ብር 11,329,996,797.00 መኖሩ፣
- ግብር ከፋዮች ላቀረቡት የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታው በዋና መ/ቤት ውሳኔው ተሰጥቶበት በቅ/ጽ/ቤቶች ግን ቅሬታቸው ውሳኔ ያላገኘ ተብሎ የተያዘ የብር 1,312,069,929.97 የግብር ዕዳ ውሳኔ መኖሩ፣
- በቅ/ጽ/ቤቶች የዕዳ ክትትል መዝገብ ላይ አቤቱታቸውን ለዋና መ/ቤት ያቀረቡ የተባሉ ግብር ከፋዮች ቢኖሩም ግብር ከፋዮቹ በዋና መ/ቤት የክትትል መዝገብ ላይ ዝርዝራቸው ያልተገኘ የግብር ዕዳ ብር 481,837,038.37 መኖሩ፣
- የግብር ዕዳ ውሳኔ ቅሬታን በተመለከተ ዋና መ/ቤት ውሳኔው በፍርድ ቤት ክትትል ላይ ያለ መሆኑን መረጃውን የያዘ ሲሆን ቅ/ጽ/ቤች ግን በዕዳ ክትትል መዝገባቸው ላይ መዝግበው ያልያዙ የብር 6,895,954,886.08 ሂሳብ መኖሩ፣
- ዋስትና በማስያዝ በጊዜያዊነት ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ጊዜ የተጠናቀቀ ቢሆንም የተያዘው ዋስትና ሂሳብ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ወይም ዋስትናው ያልተራዘመ የቀረጥና ታክስ 109,687,117.26 መኖሩ፣

ታውቋል፡፡/ዝርዝሩን በአባሪ 8/1(ሀ-ሠ፣አባሪ-9/ለ እና አባሪ 10/ሀናለ ይመልከቱ/

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሰራ እንዲሁም ከላይ የተመለከቱት የአሰራርና የአፈጻጸም ድክመቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ እናሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ፣

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ **ከ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች** የወጪ ማስረጃ ተሟልቶ ሳይቀርብ ብር 1,916,979.53 የተከፈለ ክፍያ መኖሩ ታውቋል፡፡ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል የግዥ መጠየቂያ እና የክፍያ ትእዛዝ ማስረጃ በሚመለከተው ሀላፊ ሳይረጋገጥ፣ የተወዳዳሪዎች የንግድ ስራ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ስርተፊኬት እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ ተሳታፊዎች አገልግሎቱን ስለማግኘታቸው የተሳታፊዎች አቴንዳንስ ወይም የሰዓት መቆጣጠሪያ ፊርማ የተጠቀሙት የመስተንግዶ አይነት ሳይኖር እንዲሁም የአገልግሎት ሰጪውንና የአገልግሎት ተቀባይን የውል ስምምነት የሚያሳይ ውል ሳይኖር ወጪው እንዲከፈል በተጠየቀ ደብዳቤ መሰረት ብቻ የተከፈለ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ዝርዝሩን በአባሪ 17 ይመልከቱ/

በመሆኑም ለወደፊቱ የዕቃ ግዥ ወጪ ክፍያ ከመፈጸማቸው በፊት መሟላት ያለባቸዉ ማስረጃዎችን ማረጋገጥ እንደሚገባ፣ የተሟላ ማስረጃ ላልቀረበላቸው ወጪዎች አስፈላጊው ማስረጃ እንዲሟላ መደረግ እንዳለበትና ማሰረጃ ሳይኖር ለተፈጸሙ ክፍያዎች ግን ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት ገልጸናል፡፡

4.2 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣

የአገልግሎትም ክፍያዎች በጀት ተይዞለት እና ለመ/ቤቱ አላማ የሚውል መሆኑን ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገበት በከፍተኛ ደረጃ ውጤት ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን፣ የውሎ አበል በሚከፈልበት ወቅት ተገቢው ፎርም እየተሞላና በተመኑ መሰረት መከፈሉን፣

በስራ ገበታቸው ላይ ላልተገኙ ወይም ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች በስራ ገበታቸው ላይ ያልተገኙበትን ቀን በማስላት ከደመወዛቸው ላይ ተቀናሽ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑን፣ መመሪያው በሚያዘው መሰረት የውሎ አበል ክፍያ የሚፈጽም መሆኑን፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስሌትና አከፍፈል ለመደበኛ ስራ በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ ተባዝቶ ክፍያ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የውሎ አበል መመሪያን ያልተከተለ፤ የምግብ የትራንስፖርትና የመኝታ አበል ወጪ እና መመሪያን ያልተከተለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በ4 ቅ/ጽ/ቤቶችመ/ቤቶች	216,470.09
ለመ/ቤቱ ተግባር እና አላማ ጋር ለማይገናኝ ተግባር መመሪያ ከሚፈቅደው ውጪ የተከፈለ ክፍያ	119,465.00
ያለአግባብ የተከፈለ የደመወዝ ክፍያ	9,752.48
ተገቢ የሆኑ ማስረጃዎች ሳይቀርብ የተወራረደ የውሎ አበል	48,505.16
ድምር	**394,192.73**

በአጠቃላይ ብር 394,192.73 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩን በአባሪ 19 ተመልክቷል/ በመሆኑም የውሎ አበል በሚከፍልበት ወቅት መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት መሆኑን እና የማስረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ያለበት መሆኑን፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲፈጸም መመሪያውን መሰረት አድርጎ የተሞላ ቅጽ መቅረቡን ማረጋገጥና በህግ ከተፈቀደዉ ዉጭ አለግባብ የተከፈለ ክፍያ ለመንግስት ገቢ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.3 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ መቀነስ የነበረበት ተቀናሽ ሳይደረግ የተከፈለ ክፍያ

ግዥ በሚፈጸምበት ወቅት በመመሪያው መሰረት ቅድመ ግብርና የተጨማሪ እሴት ታክስ ቆርጦ በማስቀረት ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ገቢ ማድረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ **በ 2 ቅ/ጽ/ቤት** ግዥ በተፈፀመበት ወቅት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 41,764.28 እና የቅድመ ግብር ተቀናሽ ብር 31,534.88 በድምሩ ብር 73,299.16 ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 20/5 ተመልክቷል/

በመሆኑም ማንኛውም ክፍያ ሲፈፀሙ የተቀመጠውን አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ የተከተለ መሆን ያለበት በመሆኑ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቅድመ ግብር ተቀንሶ ባለመቅረቱ በአዋጁ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል በማለት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት ላይ ገልጸናል፡፡

4.4 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ግዥዎችን የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስተር ባወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት መፈጸሙን ለማሻሻልና ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቂ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 7,798,673.76 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 126,485.00 በድምሩ ብር 7,925,158.76 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ መፈጸሙ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያከናውኑትን ግዥ በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ማከናወን ያለባቸው መሆኑን በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አስገንዝበናል፡፡

4.5 በብልጫ የተከፈሉ /ስራ ለለቀቁ ሠራተኞች አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ

ሰራተኞች ስራቸዉን የለቀቁበት ቀን ወይም ከስራ የቀሩበት ቀን በሚገልጸዉ ማስታወቂያ መሰረት ክፍያዉ ያለመፈፀሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ስራ ለለቀቁ እና ስራ ሳይሰሩ የትርፍ ሰዓት ተብሎ **በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች** ያለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ በድምሩ ብር **86,725.80** መኖሩ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 20 ተመልክቷል/

በመሆኑም በማንኛውም ሁኔታ ለሚፈጽመው ክፍያ ወጪ ከመደረጉ በፊት በገንዘብ ክፍያ መመሪያ የተቀመጡ ነጥቦች መሰረት መሆኑን ማረጋገጥና ለወደፊቱም ማንኛውም ሰራተኛ ስራ የለቀቀ እንደሆነ በሚቀጥለዉ ወር ፔሮል ዉስጥ እንዳይካተት የሚመለከታቸው ሰራተኞች ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ ያለባቸው መሆኑን ጠቅሰን በብልጫ የተከፈለው ደመወዝም ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.6 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ ሂሳብ፣

ተገዝተው ወደ መጋዘን ገቢ መደረግ ያለባቸው ንብረቶች የንብረት ገቢ ደረሰኝ የሚቀረጥላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- **በዋና መ/ቤት** በድምሩ ብር 174,050.00 ለተፈጸሙ ክፍያዎች ንብረቱ ገቢ መደረጉን የሚያረጋግጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል19) ሳይቆረጥለት ወይም ሳይያያዝ ክፊያው የተፈፀመ በመሆኑ ንብረቱ ለመ/ቤቱ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመስሪያ ቤቱ የሚፈፀም ማንኛውንም እቃ በሞዴል 19 ገቢ ማድረግ ካልሆነም ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ

5.1 ማስረጃ ያልቀረበለት የተከፋይ ሂሳብ

በሂሳብ ሪፖርት ላይ ለሚታዩ ተከፋይ ሂሳቦች ማስረጃ ሊቀርብለት የሚገባ መሆኑን እና ሂሳቦች ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- **በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች** ሰኔ 30/2010 በድምር ብር 147,419,296.44 ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡/አባሪ 31/

በተከፋይነት የተያዙ ሂሳቦች ሰነዳቸው ቀርቦ ወቅታዊ ክትትል በማድረግ የማወራረድ ስራ ሊሰራ የሚገባ ሲሆን ተከፋይ ያልሆኑ ሂሳቦች ካሉ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል በማለት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት ገልጸናል፡፡

5.2 ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀፅ 5 ከሀ እስከ ሠ የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ በተከፋይ መያዙን፣

በጊዜ ቀነ-ገደቡ መሰረት ያልተወራረዱት በቂ ማስረጃ ሲቀርብ በመዝገብ እና በሌጀር በተከፋይ መያዝ የሚገባ መሆኑን እና የተከፋይ ሂሳብ ክምችት እንዳይኖር መወራረድ እንዳለበት በሚገልጸው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- **በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች** ሰኔ 30/2010 ሳይወራረድ ከ1 ወር እስከ 10 ዓመት እድሜ ያለው በድምር ብር 40,868,202.31 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡/ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ-30 ተመልክቷል/

በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርትም በተከፋይነት የተያዙ ሂሳቦች ላይ ወቅታዊ ክትትል በማድረግ የማወራረድ ስራ ሊሰራ የሚገባ መሆኑንና ተከፋይ ያልሆኑ ሂሳቦች ካሉ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግእንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.3 በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች

እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ከ2002 ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ የሚታይ ብር 144.91 ምንም አይነት ውሳኔ ያልተሰጠው ሂሳብ እና ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር የሚከፈል ተብሎ የተያዘው ብር 16,695.48 ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ ያልተመዘገበ እና በዴቢት የሚታይ መኖሩ ታውቀዋል፡፡/ አባሪ 32/

በመሆኑም የሚመለከተው ስራ ክፍል የሂሳቡን ዝርዝር ሁኔታ በማጣራት ማስተካከያ ሂሳብ ሊሰራለት እንደሚገባ አስገንዝበናል፡፡

6. የበጀት /የገቢ ዕቅድ እና የወጪ በጀት አጠቃቀም

6.1 የገቢ እቅድና ክንውን፣

በባለስልጣን መ/ቤቱ በ2010 በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው የሀገር ውስጥ እና የጉምሩክ ገቢ ሂሳብ ከተሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር፡-

- በዕቅድ ከተያዘው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ ብር 130,411,670,000.00 ውስጥ ብር 103,213,166,641.89 የተሰበሰበ ሲሆን ብር 27,198,503,358.11 (21%) ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

- በዕቅድ ከተያዘው ጠቅላላ የጉምሩክ ሂሳብ ብር 99,588,318,683.93 ውስጥ ብር 72,737,396,384.90 ብቻ የተሰበሰበ ሲሆን፣ ብር 26,850,922,299.03 (27%) ያልተሰበሰበ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለወደፊቱ የባለስልጣን መ/ቤቱን የገቢ ዕቅድ መሰረት በማድረግ ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ ከፍተኛ ትኩረትና ክትትል በማድረግ ሊሰበስብ ይገባል በማለት በሪፖርታችን አሳስበናል ፡፡

6.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

ባለስልጣን መ/ቤቱ በ2010 በጀት ዓመት የተመደበለትን የካፒታልና የመደበኛ ወጪ በጀት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለካፒታል ወጪ ከተያዘው በጀት ብር 218,836,739.00 ውስጥ ብር 103,184,814.37 ብቻ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ብር 115,451,924.63 (53%) ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መሆኑ፣
- ለመደበኛ ወጪ ከተያዘው በጀት ብር 2,327,151,431.00 ውስጥ ብር 1,990,350,722.07 ብቻ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ብር 336,800,708.93 (14%) ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ሲኖሩ በአጠቃላይ በባለስልጣን መ/ቤቱ በድምሩ ብር 452,252,633.56 (19%) ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡/አባሪ 33/

በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ በበጀት አጠቃቀም ላይ በበጀት አዋጅ እና መመሪያ መሠረት ተገቢውን ጥንቃቄ እና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የዕቃና ንብረት አስተዳደር

7.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት

የንብረት አስተዳደርን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት ተገዝተው ወደ መ/ቤቶች የገቡ ንብረቶችን በትክክል መግባታቸውን፣

ወጪ መደረጋቸውን እና ምዝገባ መኖሩን የሚያሳይ መዝገብ መቋቋሙን እንዲሁም ንብረቶቹ በአግባቡ መጠበቃቸውን አና ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ንብረት ቆጠራ ተደርጎ የመንግስት ንብረት ለመጠበቅ የተሟላ የቁጥጥር ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በየቅ/ጽ/ቤቶ የንብረት አያያዝ ክፍተቶች የታዩ መሆናቸው በሚከተለው ሁኔታ ተዘርዝረዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም፤ ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	3
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	4
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	4
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	4
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች(ተሽከርካሪን ጨምሮ) በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	14
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	2
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎች የሚገኙባቸው	4
የተወረሱ፣ የተተዉ እና በህግ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶች ቆጠራ ያልተደረገባቸው	ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች

መሆናቸው ታውቋል፡፡አባሪ 34(ሀ-ነ)

የሚወገዱ ንብረቶችን በአግባቡ እንዲወገዱ ጥረት ማድረግና የንብረት አያያዙም መመሪያን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ አስተማማኝ የሆነ የንብረት አያያዝ ስርዓት እንዲኖር መስራት ያለባቸው መሆኑን በላክነው ሪፖርት ገልጸናል፡፡

7.2 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

ቅ/ጽ/ቤቶች በሚቆጣጠሯቸው መጋዘኖች ውስጥ አዋጁ በሚያዘው መልኩ የተሽከርካሪና ሌሎች ማሽኖች ቁጥጥሩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የአሰራር ክፍተቶች በየቅ/ጽቤቶች ተመልክተናል፡፡

መግለጫ	ቅ/ጽ/ ቤቶች	የተሽከሪካሪዎች ብዛት
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ3	52-ተሽከርካሪና 1 ማሽነሪ
የተተዉ፣ የተወረሱ እና ያልተወረሱ በህግ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶች አስተዳደር እና ቁጥጥር ስር ያሉ	በ12	181 ተሽከርካሪ
በጉድለት የተገኙ ንብረቶች/ተመላሽ ያልተደረጉ ንብረቶች	በ1	1 ላፕቶፕና 1 ሞባይል
ያለአገልግሎት ወይም በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	በ3	15 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	በ2	6 ተሽከርካሪ
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	በ2	30 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ያሌው ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	በ1	2 ተሽከርካሪዎች

ናቸው፡፡

በመሆኑም ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ሙሉ መረጃው ተመዝግቦ ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ለጥፋት እና ለብልሽት እንዳይዳረጉ የሚወገዱበትን መንገድ በማመቻቸት አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል በማለት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት የተሰጠበት አጠቃላይ ገንዘብ፣ እርምጃ ተወስዶ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠንና ተመላሽ ያልተደረገ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ አባሪ 36 ተመልክቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፣ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፣ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት

ሀ/ የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	20,118,500.00		20,118,500.00
2	ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት	385,401,306.43		385,401,306.4
3	ብሄራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት	31,813,675.14		31,813,675.14
4	የፌዴራል ህብረት ስራ ማህበር	40,548,770		40,548,770
5	የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት	205,677,144.90	3,333,334.00	209,010,478.9
6	የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል	30,260,400.00	16,469,300.00	46,729,700.00
7	የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	42,816,266.00	51,484,300.00	51,484,300.00
8	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	87,092,273.47		87,092,273.57
9	የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስ/ ኤጀንሲ	13214341.00		13214341.00
10	የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	20,158,700.00		20,158,700.00
11	የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	58,508,861.01		58,508,861.01
12	የመንግስት ግ/ን/ማ/አገልግሎት	180,802,490.71		180,802,490.7
13	ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	52,487,064.94	24,355,500.00	76,842,564.94
14	ብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን	53,379,189.73		53,379,189.73
15	የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	26,771,131.00	41,535,612.68	68,306,743.68
16	የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት	13,885,516.26		13,885,516.26
17	የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ	44,033,255.00		44,033,255.00

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
18	የመንግስት ልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ	10,891,503.00		10,891,503.00
19	የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	36,870,130.00		36,870,130.00
20	ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን	7,187,481,111.04		7,187,481,111.04
21	ፌዴሬሽን ምክር ቤት	58,424,131.13	632,500.00	59,056,631.13
22	ገንዘብ ሚኒስቴር	451,746,484.40	297,735,644.81	749,482,129.21
23	ቡናና ሻይ ልማትን ግብይት ባለስልጣን	63,126,476.27		63,126,476.27
24	የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	64,289,447.20		64,289,447.20
25	የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	73,166,500.00	34,142,310.00	107,308,810.00
26	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር	29,481,110.00		29,481,110.00
27	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከል ባለስልጣን	25,103,698.00		25,103,698.00
28	የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል	25,610,200.00	33,077,740.00	58,687,940.00
29	የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅት ኤጀንሲ	16,302,440.00	-	16,302,440.00
30	ብሮድካስት ባለስልጣን	41,225,699.61	65,060,000.00	106,285,699.61
31	የሴቶች፣ሕጻናትና ወጣቶችሚ/ር	48,490,933.58		48,490,933.58
32	መለስ ዜናዊ ስራ አመራር አካዳሚ	339,518,102.90	10,000,000.00	349,518,102.90
33	ፕሬዚደንት ጽ/ቤት	84,404,893.18		84,404,893.18
34	የኢትዮጵያ ጂኦስፓሽያል ኢንፎርሜሽን ኢንስቲትዩት	32,819,956.00	21,000,000.00	53,819,956.00
35	ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ	49,760,070.00	96,000,000.00	145,760,070.00
36	የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	473,012,420.00	160,000,000.0	633,012,420.00
37	ቱሪዝም ኢትዮጵያ	65,960,000.00		65,960,000.00
38	ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት	35,775,435.00		35,775,435.00
39	ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ	168,604,047.90	2,077,560,269.60	2246164317.50
40	የኢትጵያ ፕሬስ ድርጅት	131,030,100.00		131,030,100.00
41	የከፍተኛ ትም/ አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ	23,987,650.00		23,987,650.00
42	ቤተመንግስት አስተዳደር	204,010,121.27	525,000,000.0	729,010,121.27

ለ/ <u>የተሰጠው የኦዲት አስተያየት</u>

በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኦዲት ለተደረጉት 42 መ/ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከ ሲሆን ቀጥሎ የተመለከተው የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

- ነቀፌታ የሌለበት (Clean Opinion)10 መ/ቤቶች፣
- በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) 28 መ/ቤቶች፣
- የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ(Adverse opinion) 1 መ/ቤት
- ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቸለባቸው መ/ቤቶች(Disclaimer opinion)3 መ/ቤቶች ናቸው፡፡

<u>ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች</u>

1 የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ

1.1 በሂሳብ መግለጫና በሂሳብ እንቅስቃሴ ሌጀር መካከል የታየ ልዩነት

የሂሳብ እንቅስቃሴ ሌጀር የሚታየው ከወጪ ቀሪ በትክክል ወደ ሪፖርት መተላለፉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ቱሪዝም ኢትዮጵያ (ሂሳብ መደብ 4103) በባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ላይ ከወጪ ቀሪ ዜሮ የሚያሳይ ቢሆንም በሂሳብ መግለጫ ብር 5,987.41 ከወጪ ቀሪ እንደነበር ሪፖርት ተደርጓል፡፡

ስለሆነም ጉዳዩ ተጣርቶ ማስተካከያ እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

1.2 የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ የማያስገቡ

በየቀኑ የሚሰበሰበው ገቢ በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ፕሬስ ድርጅት ……………………………… ብር 675,988.01
- የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ ብር 39,561.00

የሰበሰቡትን ገቢ ወዲያውኑ ባንክ ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፤

ስለሆነም በየቀኑ የሚሰበሰበው ገቢ በዕለቱ ወደባንክ ገቢ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

2 ተሰብባሰቢ ሂሳብ

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል (መ) ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በተገለጸው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ ፡

- ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት የቆየ .... ብር 69,331,161.72
- ከ 1 ዓመት እስከ 5 ዓመት .... ብር 709,921,353.69
- ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት .... ብር 8,521,190.64
- ከ 10 ዓመት በላይ .... ብር 644,600.50
- በቆይታ ዕድሜው ያልተተነተነ .... ብር 21,495,758.41

ስለሆነም በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ በወቅቱ እንዲወራረድ አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች

- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሂሳብ መደብ 4253 ከሰኔ 23/2010 ጀምሮ የህትመት ታሳቢ በማለት ብር 39,000,000.00 አለአግባብ ቅድሚያ ክፍያ ወይም ብድር የሰጠ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በርካታ የተሰብሳቢ ሂሳብ በዕድሜ እየተተነተነ ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፤
- የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር82,787,021.72 ተቀጽላ ሌጀር ያልተከፈተለት ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ወቅት ተገኝቷል፡፡

ማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባ እና በግለሰቦች እና በድርጅቶች የሚታዩ ተሰበሳቢ ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

3 <u>የገቢ ሂሣብ</u>

በፌዴራል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ፣ ደንብና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ግብር እና ታክስ መቀነሱንና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

3.1 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ የተገኘባቸውመ/ቤቶች ዝርዝር

- የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ብር 121,420.05
- የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 51,914,759.49
- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት………… ብር 1,425,745.80

3.2 በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ

- የስራ ግብር ……………………. ብር 262,558.82
- ተጨማሪ እሴት ታክስ/VAT/ …… ብር 11,287,247.11
- ቅድመ ግብር (withholding tax) ብር <u>1,508,385.39</u>

በድምሩ ብር **<u>13,058,191.32</u>**

ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የዱቤ አገልግሎት ተሰጥቶ ያልተሰበሰበው የገቢ ሂሳብ በአፋጣኝ እንዲሰበሰብ እንዲሁም በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ከሚመለከታቸው ላይ እርምጃ በመውሰድ ገንዘቡ እንዲሰበሰብ ተደርጎ ፈሰስ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

3.3 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ

- ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 2,429,645.38

3.4 በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች

- ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ተመላሽ/ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ-

የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት

ብር	USD
379,831.22	156,536.17

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በውል መሰረት ባልፈጸሙት ላይ ተገቢው እርምጃ በመውሰድ ገንዘቡ እንዲተካ አሳስበናል፡፡

3.5 የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ/ዴቢት/መሆኑ

- ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት ብር 1,066,610.91

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን ሊያሳይ የቻለበት ሁኔታ ተጣርቶ ማስተካከያ እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

3.6 <u>ከታቀደው በታች የተሰበሰበ ገቢ</u>

	<u>እቅድ</u>	**<u>ክንውን</u>**
የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	500,000,000.00	308,411,294.02

ክንውን በማነስ ብር 191,588,705.98 ወይም 38% (በመቶ) ማሳየቱ፡-

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለወደፊቱ የገቢ ዕቀዱ በጥናት እና በማስረጃ የተደገፈ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

3.7 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብና በሪፖርት መካከል የታየ ልዩነት

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ)- የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ አለበት፣ (ለ)- ትክክለኛነቱ የተረጋገጠው የሌጀር ሚዛን ሂሳብ ወደ ገቢ፣ ወጪ፣

ዝውውር ተከፋይና ተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ላይ በትክክል መተላለፍ እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ብር 579,108.65 በመብለጥና ብር 18,946,356.96 በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

3.8 መነሻ ሰነድ የሌለው የማስተካከያ ምዝገባ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

የገቢ ሂሳብ በዴቢት ብር 11,276,751.43 በክሬዲት ብር 23,863,034.48 የተመዘገበ ሲሆን፤ አስቀድሞ የተደረገው ስህተትም ሆነ የትኛውን ሂሳብ ለማስተካከል የተደረገ የሂሳብ ማስተካከያ እንደሆነ የሚገልጽ ሰነድም ሆነ መግለጫ የሌለው የሂሳብ ምዝገባ መሆኑ፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

አስቀድሞ የተደረገው ስህተት እንዲሁም የትኛውን ሂሳብ ለማስተካከል የተደረገ የሂሳብ ማስተካከያ እንደሆነ የሚገልጽ ሰነድ እንዲዘጋጅ አሳስበናል፡፡

3.9 በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ሊደረግ ሲገባው በገቢ ሂሳብ ሪፖርት የተደረገ

- የቤተ መንግስት አስተዳደር ብር 280,000.00

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የገቢ ሂሳብ አላግባብ በብልጫ እንዲያሳይ የተደረገ በመሆኑ የሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

3.10 በገቢ አርስት በዝርዝር መመዝገብ ሲገባው በጥቅል የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ

እያንዳንዱ የገቢ ዓይነት በገቢ ምንጩ እና ለሂሳቡ በተፈቀደው የገቢ አርዕስት መሰረት መመዝገብ ያለበት ቢሆንም ሂሳቡ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የቤተ መንግስት አስተዳደር ብር 8,874,003.6 በጥቅል ተመዝግቦ መገኘቱ፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

እያንዳንዱ የገቢ ዓይነት በገቢ ምንጩ እና ለሂሳቡ በተፈቀደው የገቢ አርዕስት መሰረት ተለይቶ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

3.11 በገቢ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ

- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 1,067,807.58

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ማናቸውም የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በአግባቡ ተሰብስቦ እየተመዘገበ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4 <u>የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን፣ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙንና የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

4.1 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ የተገኘባቸው

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 የመደበኛና የካፒታል ሥራ ማስኬጃ ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ሊረጋገጥ እንደሚገባ የተገለጸ ቢሆንም በ9 መ/ቤቶች ብር 850,678,819.23 የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ (አባሪ 17 ይመልከቱ)

4.2 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

ማንኛውም ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት የተሟላ ደጋፊ ሰነዶች መቅረብ እንዳለባቸው የተደነገገ ቢሆንም፣ በ6 መ/ቤቶች ብር 7,317,427.33 በቂ ደጋፊ ሰነዶች ሳይቀርቡ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ አባሪ 18 ይመልከቱ፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በመንግስት ታምኖባቸው በወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት የተፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ 23 መ/ቤቶች ብር 2,777,149.94 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡ (አባሪ 19 ይመልከቱ)

ስለሆነም ማንኛውም ሂሳብ የመንግስት መመሪያን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.4 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች

ማንኛውም ክፍያ በአዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት፡- የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ብር 50,173.40 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያ መፈጸሙ ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ሂሳብ የመንግስት መመሪያን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.5 የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

የዕቃና አገልግት ግዥ በመንግስት በወጣው የግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት መፈጸም እንዳለበት የተደነገገ ቢሆንም፡-

- መ/ቤቶች ጨረታ ሳያወጡ በብር 573,398,548.31 የእቃና አገልግሎት ግዥ የፈጸሙ መሆኑ፣
- 19 መ/ቤቶች የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበስቡ በብር **6,121,722.93** የእቃና አገልግሎት ግዥ የፈጸሙ መሆኑ፣
- 3 መ/ቤቶች የግዥ ስርዓትን ሳይከተሉ በብር 1,312,580.31 ግዥ የፈጸሙ መሆኑ፣ (አባሪ 21 ይመልከቱ)

ስለሆነም ማንኛውም ግዥ የግዥ መመሪያን ተከትሎ እንዲፈጸም የስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

4.6 ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች

ማንኛውም ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ዕቃው ለመድረሱ የገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት የሚገባ ቢሆንም:- በ4 መ/ቤቶች ብር 1,939,546,380.97 ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መሆኑ፤

ስለሆነም ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ደረሰኝ እንዲቀርበ አሳስበናል፡፡

4.7 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው

ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ከቀረጥ ነጻ የገቡ ዕቃዎች የንብረት ደረሰኝ ሳይቀርብ ብር 1,311,908,803.11 የቀረጥ ሂሳብ በወጪ የመዘገበ መሆኑ፣ ንብረቶቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡

4.8 ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተመዘገበ ወጪ የተገኘባቸው

ማንኛውም ሂሳብ በበጀት ዓመቱ መመዝገብ ያለበት ቢሆንም:- በ3 መ/ቤቶች ብር 66,690,494.85 ከበጀት ዓመቱ ውጭ የመዘገቡ መሆኑ፤ (አባሪ 24 ይመልከቱ)

ስለሆነም ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳሰስበናል፡፡

4.9 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ (አባሪ 24 ይመልከቱ)

ማንኛውም ወጪ በተፈቀደው የበጀት አርዕስት መሰረት ተከትሎ መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:- 13 መ/ቤቶች ከተፈቀደው የበጀት አርዕስት ውጭ ብር 7,261,257.66 መዝግበው መገኘታቸው ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳሰስበናል፡፡

4.10 አግባብ ባለው ባለሥልጣንና ቦርድ ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

ማንኛውም ክፍያ ደንብና መመሪያ ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:- የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ለተለያዩ ሰራተኞች አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ በየወሩ ብር 25,075.00 በዓመት ብር 300,900.00

ወጪ በማድረግ የሞባይል ካርድ ግዥ መፈጸሙ፤አግባብ ባለው ቦርድ ሳይፈቀድ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.11 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

(አባሪ 28 ይመልከቱ)

የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች ማስረጃ ቀርቦላቸው እሲኪወራረዱ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ብር 259,507.71 የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

ቅድመ ክፍያው በወጪ መመዝገቡ አግባብ ባለመሆኑ ማስተካከያ እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

4.12 ውል በተገባበት ጊዜ ያልተጠናቀቁና የተቋረጡ የፕሮጀክት ሥራዎች(አባሪ 28 ይመልከቱ)

ግንባታዎች በታቀደላቸው ጊዜ ተጠናቀው የሚፈለገውን አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ቱሪዝም ኢትዮጵያ ብር 5,358,309.71 ለግንባታ ስራዎች ቅድሚያ ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በውል መሰረት ካለመጠናቀቃቸው በተጨማሪ የግንባታ ስራው የተቋረጠ መሆኑ፤ በውል መሰረት ባልፈጸሙት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

4.13 ያልተመዘገበ ወጪ

ማስረጃ የቀረበላቸው ሂሳቦች በወቅቱ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ብር 1,914,716.08 የወጪ ሂሳብ ያልመዘገበ መሆኑ፤

4.14 ውል ውስጥ ያልተካተተ የእህል የማቅረቢያ/የአገልግሎት ማስፈፀሚያ/ ቀን-ገደብ

የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የእህል የማቅረቢያ/የአገልግሎት ማስፈፀሚያ/ ቀነ ገደብ በስምምነት ውል ሳይካተት ብር109,190,155.09 ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፡ የእህል የማቅረቢያ/የአገልግሎት ማስፈፀሚያ/ ቀነ ገደብ በስምምነት ውል ላይ እንዲካተት አሳስበናል፡፡

4.15 የውል ስምምነት ወይም ህጋዊ ውክልና ሳይኖር የተፈጸመ ቅድመ ክፍያ (አባሪ 28 ይመልከቱ)

ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ደጋፊ የሂሳብ ሰነዶች መቅረባቸው የሚረጋገጥ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የውል ስምምነት ወይም ህጋዊ ውክልና ሳይኖር ብር 18,053,139.69 ቅድመ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

ለቅድመ ክፍያው የውል ስምምነት እንዲፈጸም ለወደፊቱም አስቀድሞ የውል ስምምነት ሳይደረግ ማንኛውም ክፍያ እንዳይፈጸም አሳስበናል፡፡

4.16 የባንክ ዋስትና ሳይቀርብ የተሰጠ ቅድመ ክፍያ

ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ደጋፊ የሂሳብ ሰነዶች መቅረባቸው የሚረጋገጥ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የባንክ ዋስትና ሳይቀርብ ብር 12,341,755.57 ቅድመ ክፍያ የተሰጠ መሆኑ፤

ለቅድመ ክፍያው የባንክ ዋስትና እንዲቀርብ ለወደፊቱም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.17 በብልጫ የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎች/

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ለሂሳብ ማወራረጃነት በቀረቡት ማስረጃዎች መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ12 መ/ቤቶች ለተለያዩ አገልግሎቶች ብር 2,591,994.59 በብልጫ ክፍያ ፈጽመው ተገኝተዋል፡፡ (አባሪ 20 ይመልከቱ)

በብልጫ የተከፈሉ ገንዘቦች እንዲመለሱ አሳስበናል፡፡

4.18 የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ለሂሳብ ማወራረጃነት በቀረቡት ማስረጃዎች መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የቤተ መንግስት አስተዳደር ለኦዲት ስራ ከሰጠው የስልክ ዝርዝር ውስጥ የሌሉና ስልክ ቁጥራቸው ሳይጠቀስ በሚስጥር ኮድ በመጠቀም ብር 297,042.76 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

ጉዳዩ ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

4.19 አለአግባብ የተፈጸመ የኮንትራት ቅጥር

ማንኛውም ክፍያ በመንግስት በወጣው መመሪያ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳያስፈቅድ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር ብር 284,404.00 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.20 ከመ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ያልተቀነሰ የህክምና መዋጮ

ማንኛውም ሂሳብ በመንግስት ታምኖባቸው በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ተከትሎ የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የበላይ ኃላፊዎች ላይ ብር 10,622.36 የህክምና መዋጮ ያልተቀነሰ መሆኑ፤ (አባሪ 20/4 ይመልከቱ)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ማንኛውም ክፍያ በመንግስት ታምኖባቸው በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት እንዲፈጸም ስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

5 <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

5.1 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ</u>

የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛ እዳና በወቅቱ የሚከፈል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ 24 መ/ቤቶች፡-

➢ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት የቆየ	ብር	6,121,523.93
➢ ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት የቆየ	ብር	172,053,313.29
➢ ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት የቆየ	ብር	52,186,623.57
➢ ከ 10 ዓመት በላይ የቆየ	ብር	51,870.32
➢ የቆይታው ጊዜ የማይታወቅ	ብር	1,461,299.68
በአጠቃላይ በድምሩ	ብር	**231,874,492.83**

በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑን ታውቋል፡፡ (አባሪ 30 ይመልከቱ)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ማንኛውም የተከፋይ ሂሳብ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብና መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች

5.2.1 መደበኛ የመነሻ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ (ዴቢት ሚዛን) የተከፋይ ሂሳብ:-

ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ብር 114,823.52 መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

ተከፋይ ሂሳቡ መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ሊያሳይ ያልቻለበት ምክንያት ተጣርቶ ማስተካከያ እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

5.2.2 ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው

የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 214,765,890.99 ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

5.2.3 በብልጫ ሪፖርት የተደረገ የተከፋይ ሂሳብ

ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት በመዝገብ የተመዘገበው ሪፖርት ከተደረገው ጋር ሲነጻጸር ብር 192,046.79 በብልጫ ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም ከላይ በተጠቀሱት የአሰራር ክፍተቶች ላይ የስራ አመራሩ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

6 የበጀት አጠቃቀም

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 ክፍል 6 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 30 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 እስከ 26 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከተው የመንግስት መሥሪያ ቤት እንዲከፈል በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈጸም እንደማይቻል በተገለፀው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

6.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ

በ2 መ/ቤቶች ለመደበኛ በጀት ከተደለደለው በላይ ብር 125,402.73 አንድ መ/ቤት ደግሞ ለካፒታል በጀት ከተደለደለው በላይ ብር 459,773.95 ተጠቅመው ተገኝቷል፡፡

6.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት /ከ10% በላይ ልዩነት ያለው፡-

- በ36 መ/ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር 792,793,684.59
- በ16 መ/ቤቶች ካፒታል በጀት ብር 1,474,225,114.96

በድምሩ ብር 2,267,018,799.55

ሥራ ላይ አለመዋሉ ታውቋል፡፡

6.3 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች

በ6 መ/ቤቶች አስቀድሞ በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ብር 8,856,243.77 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

7. <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር</u>

7.1 የንብረት አስተዳደር ችግሮች

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት በታዘዘው መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	13	
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	6	
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	4	
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው (4 ላፕቶፕ፣1ኤልሲዲ፣5ፕሪንተር)	3	
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	20	

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	2	
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (በርካታ ንብረቶችና በገንዘብ ብር 1,582,623.22 በዋጋ ያላቸው)	7	
የንብረት ጉድለት የተገኘባቸው ፤ዋጋቸው ብር 20,346.01 እና 18 የላቦራቶሪ ዕቃዎች	2	

7.2 በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ወጪ ሆነው በንብረት ክፍል የተገኙ ንብረቶች

- በአንድ መ/ቤት ብር 1,354,918.81 ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ወጪ ሆነው ነገር ግን ንብረቶቹ በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የተገኙ መሆኑ፤

7.3 ውድ የሆኑ ጌጣጌጦች እና ቅርሳ ቅርሶች

በቤተመንግስት አስተዳደር ውስጥ ለሚገኙ ውድ የሆኑ ጌጣጌጦች እና ቅርሳቅርሶች ለእያንዳንዳቸው የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ የተመዘገቡ መሆኑ እንዲሁም በየዓመቱ ቆጠራ እየተደረገ በውጤቱ መሰረት እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ውድ ለሆኑ ጌጣጌጦች እና ቅርሳቅርሶች ምዝገባ የተደረገ መሆኑ እና በየዓመቱ ቆጠራ እየተደረገ በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ የሚወሰድ ለመሆኑ ማስረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ፤

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የመ/ቤቶቹ ሥራ አመራር በተጠቀሱት የአሠራር ክፍተቶች ላይ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.4 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የተገዙ ተሽከርካሪዎች ተገቢው ጥበቃና ክለላ የሚደረግላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ተገኝቷል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	መ/ ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	9	72	2
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	6	35	3
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	4	12	
በኃላፊ ተወስዶ ተመላሽ ያልተደረጉ ተሽከርካሪዎች	2	3	
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1	5	
ድምር	22	127	5

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የተጠቀሱት መ/ቤቶች ሥራ አመራር በታየው የአሠራር ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስገንዝበናል፡፡

8 **ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት የተሰጠበት አጠቃላይ ገንዘብ፤ እርምጃ ተወስዶ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠንና ተመላሽ ያልተደረገ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ አባሪ-36 ተመልክቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ
መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

ሀ/ ኦዲት ዳይሬክቶመሬቶች ዕቅድና ክንውን

የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር፣

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የወልቂጤዩኒቨርስቲ	437,987,539.03	410,000,100.00	847,987,639.03
2	የመቱ ዩንቨርስቲ	304,263,126.00	-------	304,263,126.00
3	የቦንጋ ዩኒቨርስቲ	93,285,335.00	-------	93,285,335.00
4	የአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	603,999,350.00	611,000,000.00	1,214,999,350.00
5	የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ	438,700,325.76	500,000,000.00	938,700,325.76
6	የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	50,021,080.00	185,500,000.00	235,521,080.00
7	የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	357,207,457.91	521,152,015.61	879,359,473.52
8	የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ	319,472,989.27	541,761,840.80	861,234,830.07
9	የወልድያ ዩኒቨርሲቲ	371,270,036.56	636,602,755.37	1,007,872,791.93
10	የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	47,748,830.00	65,070,650.00	112,819,480.00
11	የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር	211,235,300.00	-----	211,235,300.00
12	አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	517,624,510.00	594,382,970.00	1,112,007,480.00
13	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	425,190,429.00	450,000,000.00	875,190,429.00
14	ወራቤ ዩኒቨርሲቲ	83,939,100.00	--	83,939,100.00
15	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን	55,646,818.64	--	55,646,818.64
16	ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ	397,023,900.00	--	397,023,900.00
17	ፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል	31,003,550.00	--	31,003,550.00
18	እንስሳት መዲሀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን	67,324,947.21	--	67,324,947.21
19	የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት	153,632,600.00	176,473,600.00	330,106,200.00
20	የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	44,128,740.00	6,049,440.00	50,178,180.00
21	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	267,348,946.00	154,614,172.00	421,963,118.00
22	አዲግራት ዩኒቨርሲቲ	438,700,325.76	500,000,000.00	938,700,325.76

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
23	የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት	116,523,334.19	---------	116,523,334.19
24	ማይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር	144,030,160.00	425,247,130.00	569,277,290.00
25	የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት	76,891,582.41	15,000,000.00	91,891,582.41
26	አሶሳዩኒቨርሲቲ	295,083,975.00	350,230,000.00	645,313,975.00
27	የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር	89,500,850.00	444,609,800.00	534,110,650.00
28	የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	29,646,497.96	23,205,653.00	52,852,150.96
29	የፍትሕና የህግ ሥርዐት ምርምር ኢንስቲትዩት	15,594,901.76	-----	15,594,901.76
30	ብሔራዊየቆላዝንብናየገንዲበሽታመከላከያናማ ጥፊያኢንስቲትዩት	79,829,423.85	10,000,000.00	89,829,423.85
31	የምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	50,508,174.00	-------	50,508,174.00
32	ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	344,824,696.38	-----	344,824,696.38
33	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር	49,309,127.16	----	49,309,127.16
34	የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚ/ር	108,021,220.12	----	108,021,220.12
	ድምር	7,116,519,178.97	6,620,900,126.78	13,737,419,305.75

<u>ማስገንዘቢያ</u>፣

- **የደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ በተከሰተው ወቅታዊ ችግር ምክንያት የኢንተሪም ኦዲት ተደርጎ የመጨረሻው ኦዲት አልተደረገም፡፡**

ለ/ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት፣

በአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኦዲት ለተደረጉትና ኦዲታቸው ለተጠናቀቁት 34 መ/ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት የተሰጠው የኦዲት አስተያየት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት ለ18 መ/ቤቶች፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ13 መ/ቤቶች እና አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 3 መ/ቤቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡(አባሪ 1 ይመልከቱ)

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ፣

1.1 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፣

በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያን ተከትለው የሚሠሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በስድስት መ/ቤቶች ብር 3,697,634.57 በቼክ ወይም በባንክ በማስተላለፊ መከፈል ሲገባው በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መሆኑን፡-(**አባሪ 2 ይመልከቱ**)
- የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት በድምሩ ብር 1,870,261.44 ስለጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ሂሳቡ ዝርዝር ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት አለመቻሉን፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የመንግስት ገንዘብ ከጥፋት ለመከላከል እንዲቻል የክፍያ አፈፃጸም መመሪያውን ተከትሎ መፈፀም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

1.2 የባንክ ሂሳብ በተመለከተ

ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርስቲ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ለመደበኛ በጀት የተፈቀደው በሰኔ 30 ላይ ሚዛኑ ዜሮ መሆን ሲገባው የሰኔ 30/2010 ሂሳብ ሪፖርት በባንክ ያለ ገንዘብ /cash at Bank 4103/ ብር 9,072,477.15 የሚታይ ሲሆን በአንፃሩ በሰኔ 30/2010 የባንክ ስቴትመንት ላይ ምንም ገንዘብ የማይታይና ዜሮ ሚዛን በመሆኑ በሪፖርቱ እና ባንክ ስቴትመንቱ በዚሁ ገንዘብ መጠን ልዩነት ያለው መሆኑን፣
- የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ቋት ሚዛን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ መዘጋጀት ቢኖርበትም ተዘጋጅቶ የማይመዛዘን መሆኑን፣
- በሳጥን የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ በየጊዜው ተቆጥሮ በሂሳብ ክፍል ከሚያዘው የጥሬ ገንዘብ ቋት ጋር መመዛዘን ቢገባውም ተቆጥሮ የማይመዛዘን መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው የውስጥ የቁጥጥር ስርዓትን በመዘርጋት በባንክ ያለውና በቋት ያለ ገንዘብ ማመዛዘን እንዳለበት አሳስበናል፡፡ በባንክ የሌለው ገንዘብ እንዳለ ተደርጎ ሪፖርት የተደረገውም ተጣርቶ የማስተካከያ እርምት ሊወሰድ እንደሚገባ ያለበትና ለወደፊትም እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይፈጠር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.3 ***የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ የማያስገቡ፣***

የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ የገቢ ማመንጫ የሰበሰበውን የውስጥ ገቢ በድምሩ ብር 6,416,448.24 በዕለቱ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ የማይደረግ እና በበጀት ተይዞ ሳይፈቀድ በቀጥታ የሚጠቀም መሆኑን

የማሻሻያ ሀሳብ፣

መንግስት ባውጣው በውስጥ ገቢ መመሪያ መሰረት የተሰበሰበው ገቢ በየዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ እና ለመጠቀም የሚቻለው በበጀት ሲጸድቅ ብቻ መሆን እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

1.4 ***የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ/ዴቢት/መሆኑ፣***

የምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በሰኔ 2010 ዓ/ም በቀረበው የሂሳብ ሪፖርት የተገለፀው የተጣራ ሀብት ብር 924,528.06 በክሬዲት መመዝገብ ሲገባው፣ በዴቢት ሚዛን ተመዝግቦ መገኘቱ፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የመንግሰት ደንብና መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ የተጣራ ሃብት በመደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ጠብቆ መመዝገብ ስለሚኖርበት ሂሳቡ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

1.5 ***በባንክ ሂሳብ መግለጫ(bank statement) እና በሂሳብ ሪፖርት መካከል ልዩነት፣***

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሰኔ 30/2010 ዓ.ም በባንክ ሂሳብ መግለጫ (bank statement) መሰረት በውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ላይ

ዜሮ የሚታይ ሆኖ ሳለ በሂሳብ ሪፖርቱ ብር 336,216.95 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት የሚታይ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የባንክ ሂሳብ መግለጫው ከአጠቃላይ የቋት ሚዛን ጋር በማየት ማስተካከያ ማድረግ እንዳለበት ማሳሰቢያ ሰጥተናል፡፡

1.6 <u>መደበኛ ሚዛን ያልጠበቀ የተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች፣</u>

በሦስት ዩኒቨርስቲዎች በተሰብሳቢ መክፈቻ ሂሳብ ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ብር 23,173,587.37 የተገኘባቸው መሆኑን፤-(**አባሪ 3 ይመልከቱ**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ቋቶች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይደረግ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባ እና ለሂሳቡ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

1.7 <u>መደበኛ ሚዛን ያልጠበቀ የተከፋይ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

በሦስት መ/ቤቶች በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተከፋይ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋቶች /ሌጀሮች/ ብር 35,379,403.15 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት የሚታይ መሆኑን፣ (**አባሪ 4 ይመልከቱ**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ቋቶች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይደረግ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባ እና ለሂሳቡ ተገቢው ማስተካከያ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል (መ) ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በተገለጸው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ፣</u>

በ31 መ/ቤቶች

- የቆይታ ግዜው ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት የሆነው፣ ብር 40,213,221.41
- ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሆነው፣ ብር 911,144,235.14
- ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የቆየ፣ ብር 217,784,852.27
- ከአስር ዓመት በላይ የሆናቸው ብር 100,544,615.01

በድምሩ ብር 1,269,686,923.83

የተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ **አባሪ 6 ይመልከቱ**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባ እና በግለሰቦች እና በድርጅቶች የሚታዩ ተሰበሳቢ ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

2.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣</u>

በሦስት መ/ቤቶች ብር 57,248,527.33 በቅድሚያ የተከፈለ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 27 ይመልከቱ**)

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት የተሰብሳቢ ሂሳብ በአጠቃላይ በተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ብር 2,816,009.92 የሚይታይ ቢሆንም በዝርዝር መነሻ ቋት የሚታየው ግን ብር 2,892,774.07 በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፣ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት እና ኢንስቲትዩቱ ተሰብሳቢ ሂሳብን በዕድሜ ለይቶ መያዝ ያለበትና የሂሳቡንም ትክክለኛ መጠን ማስረጃ በማስደገፍ መመዝገብ እንደሚገባው እና በተሰብሳቢ የተያዙት

ሂሳቦች ያሉበት ደረጃ እና ያለው ልዩነት ተጣርቶ በተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት ላይ የቀረበው ማስረጃ ሊታረቅ እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሣብ፣</u>

3.1 <u>በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የገቢ ግብር አዋጅ፣ ደንብና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ግብር እና ታክስ መቀነሱንና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአስራ አራት መ/ቤቶች፣

- የስራ ግብር ብር 8,015,835.26
- ተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ 1,203,942.71
- ቅድመ ግብር (withholding tax) 628,546.38
- የተለያዩ ሌሎች ገቢዎች 714,413.75

በድምሩ ብር 10,562,738.10 ያልተሰበሰበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡(**አባሪ 7 ይመልከቱ**)

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

ማናቸውም የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በአግባቡ ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

3.2 <u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ፣</u>

የውስጥ ገቢ ሂሳቦች በመመሪያው መሰረት ተሰብስበው ስለመመዝገባቸው እና ሪፖርት ስለመደረጋቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሁለት መ/ቤቶች ብር 5,622,517.20 በመመሪያው መሰረት ገቢ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ (**አባሪ 10 ይመልከቱ**)

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ**</u>፣

የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተመዝግቦ ሪፖርት ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.3 ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ፣

በአራት መ/ቤቶች ብር 3,389,765.45 የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡(**አባሪ 11 ይመልከቱ**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲዎቹ በበጀት ዓመቱ የሰበሰበቡትን ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት በማካተት ለሚመለከተው አካል ፈሰስ እንዲደረግ እና በፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት እንዲገለፅ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

3.4 የተለያዩ የገቢ አያያዝና አመዘጋገብ ችግር የሚታይባቸው መ/ቤቶች፣

በሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ብር 3,723,182.76 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት (ያልተቆረጠለት) የተሰብሳበ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡(**አባሪ 12 ይመልከቱ**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከአቅራቢ ድርጅቶች በቅጣት መልክ ለሚሰበሰበው ገቢ ተከታታይ ቁጥር ያለው በሚኒስትሩ ወይም በሚኒስትሩ በተሰጠ ውክልና መሠረት የተዘጋጀ ሕጋዊ ደረሰኝ መሰጠት እንዳለበት እና ሪፖርትም ሊደረግ የሚገባው ከገቢ ደረሰኞቹ ማስረጃነት በመነሳት መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.5 የሱቅና የቢሮ ኪራይና በሌሎች በውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ፣

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከሱቅ ከቢሮ ኪራይና በሌሎች ውል ስምምነት መሠረት ብር 366,991.00 ያልተሰበሰበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው ለመንግሥት ገቢ መሆን የነበረበትን ያልተሰበሰበውን የቤት ኪራይ ገንዘብ በውሉ መሰረት ከድርጅቱ ተሰብስቦ ገቢ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.6 የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ፣

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 6,878,172.01 የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ መኖሩን ተረጋግጧል፡፡

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ለእያንዳንዱ ኮርስ በክሬዲት ሰዓት የተተመነ የማስከፈያ ዋጋ ተመን /ታሪፍ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ዩኒቨርሲቲው ከማታ እና ከርቀት ተማሪዎች ገቢ የሚሰበስብ መሆኑን፣ እንዲሁም

ከመመዝገቢያ፣ ከትራንስክሪፕት ክፍያ፣ ከጊዚያዊ ሠርተፊኬት ክፍያ እና ከተለያዩ ቅጣቶች ወዘተ የሚሰበሰብው በሚመለከተው አካል የተተመነ ዋጋ /ታሪፍ/ ሳይወሰን የሚሰበስብ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ባለፉት የበጀት ዓመታት የተሰበሰበውን ገቢ እና የሚኖሩ ለውጦችን ታሳቢ በማድረግ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከመማር ማስተማር ሊሰበስብ የሚችለውን የገቢ መሰረተ ግምት ወይም የገቢ ዕቅድ ሊዘጋጅ እንደሚገባ እና ከተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም የሚሰበሰብ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ሠነድ ተዘጋጅቶ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ ማድረግ እንደሚኖርባቸው አሳስበናል፡፡

3.7 <u>ትክክለኛውን ሚዛን ጠብቆ ሪፖርት ያልተደረገ የገቢ ሂሳብ፣</u>

በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የገቢ ሂሳቦች ትክክለኛ ሚዛን ክሬዲት ቢሆንም ከተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም የተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ብር 5,136,774.99 እና ከልዩ ልዩ የተሰበሰበ የመደበኛ የውስጥ ገቢ ብር 3,451,973.31 በድምሩ ብር 8,588,748.3 ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ ሪፖርት በመደረጉ፣ የዩኒቨርስቲው የሰኔ 30/2010 ዓ.ም የውስጥ ገቢ ሂሳብ በብር 8,588,748.30 ዝቅ እንዲልና የዩኒቨርስቲው ሂሳብ እንዲዛባ መደረጉ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም ሂሳብ ተጠቃሎ ሪፖርት ከመደረጉ በፊት የምዝገባው ትክክለኛነት መረጋገጥ አለበት፡፡ ከሂሳብ ሚዛኑ ውጭ የተመዘገበ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.8 <u>የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ የገቢ ሂሳብ</u>

ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ፣

- በድምሩ ብር 5,564,022.00 በገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረገው ገንዘብ በገቢም ሆነ በወጪ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበና ሪፖርትም ያልተደረገ በመሆኑ ገቢ የሆነው ገንዘብ በትክክል ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በተለያየ ጊዜ እና የገቢ መሰብሰብያ ቁጥር በድምሩ ብር 686,616.70 ገቢ የሆነው በሰኔ 30/2010 በሂሳብ መዝገብ የተመዘገበውና ለገንዘብና ኢኮኖሚ

ልማት ትብብር ሚ/ር ሪፖርት የተደረገው ብር 631,336.50 ብቻ በመሆኑ ብር 55,280.20 በሂሳብ መዝገብ ያልተመዘገበና ሪፖርትም ያልተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማናቸውም የገቢም ሆነ የወጪ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተመዝግቦ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ እና በገቢም ሆነ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ ሂሳብ ተጣርቶ ምክንያቱ መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.9 <u>የውስጥ ገቢን ከመደበኛ ሂሳብ ጋር በመቀላቀል ሪፖርት የተደረገ መኖሩን</u>

በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ከውስጥ ገቢ ማመንጫነት ከሚሰበሰበው ገቢዎች እንደ ሸቀጥ አገልግሎት፣ ፎቶ ኮፒ እና የጽህፈት አገልግሎት፣ ከካፍቴሪያዎች፣ ከሻይ ቡና ከውበት ሳሎን እና ፋስትፉድና ሱፐርማርኬት ከኪራይ የሚያገኘውን የውስጥ ገቢ በድምሩ ብር 902,254.56 ከመደበኛ ሂሳብ ጋር በመቀላቀል ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በውስጥ ገቢ አርዕስቶች የተሰበሰበው ወደ ውስጥ ገቢ ተመላሽ በማድረግ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ እንደሚኖርበት እና በ1489 ሂሳብ መደብ (ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎች) የተያዘውና የተመዘገበው ገቢ ወደ 1444 ሂሳብ መደብ (የመዝናኛ ገቢዎች) ተስተካክሎ ሪፖርት ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.10 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች፣</u>

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣

- ዩኒቨርሲቲው ለገቢ ማመንጫነት ከሰራቸው ቤቶች ውስጥ ከኪራይ ገቢ መሰብሰብ ሲገባው ለተለያዩ ባለሀብቶች በነጻ ወይም ያለ ምንም ክፍያ የተሰጠ መሆኑን እና ከዩኒቨርስቲው መብራትና ውሃ በነጻ እየተጠቀሙ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይከፍሉ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በ2010 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደው የገንዘብ መጠን ወይም የገቢ መሰረተ ግምት፣ የሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነትና አገልግሎቱን በመስጠት ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ መጠን በዝርዝር የሚገልጽ የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን፣ የገቢ ዕድ ከክንውን ጋር

በማነጻጸር ለመገምገም እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብሰብ በሚገባው መጠን የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፣

- ዩኒቨርስቲው የሚሰበስበው ገቢ በሚመለከተው አካል የገቢ ተመን /ታሪፍ ሳይወሰን የሚሰበስብ መሆኑን፣ የገቢ ዕቅድ የማያዘጋጅ (የሌለው) መሆኑን እና በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምርት ዘመን፣ ሴሚስተር በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ መሆኑን፣
- በዩኒቨርሲቲው ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምርት ዘመን፣ ሴሚስተር በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

<u>**በመቱ ዩኒቨርስቲ፣**</u>

- በሂሳብ መደብ 1489 በድምሩ ብር 6,200.00 የውስጥ ገቢ መሰብሰብ ከነበረበት ግዜ (ወቅት) ዘግይቶ የተሰበሰበ መሆኑን እና የውስጥ ቁጥጥሩ ክፍተት ያለው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- ከሙያና ትምህርት ተቋሞች የሰበሰበውን ገቢ ብር 294,886.00 በሂሳብ መደብ 1443 መመዝገብና ሪፖርት ማድረግ ሲገባው በሂሳብ መደብ 1441 ምዝገባው የተከናወነና ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣

በወልቂጤ የዩኒቨርስቲ፣

- ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባካሄደው ስብሰባ ላይ ለግቢው ማህበረሰብ ለሻይ ቡና አገልግሎት በተዘጋጁ አምስት (5) ቦታዎች ላይ አለአግባብ ገቢ ለመሰብሰብ ሥልጣን ባልተሰጣቸው በተማሪዎች ህብረት በነጭ ወረቀት የሚሰበሰብ መሆኑን እና የገቢውም መጠን ለማወቅ ያልተቻለ መሆኑንን፣

ኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ፣

- የተከታታይ ትምህርት አጠቃላይ ወጪው የሚሸፈነው አገልግሎቱን ከሚያገኙት ተማሪዎች በሚሰበስበው ገቢ መሆን ሲገባው ብር 166,714.00 የተከታታይ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተባበሩ ኃላፊዎችና ትምህርቱን ላስተማሩ መምህራን ከመደበኛ በጀት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

በአዲግራት ዩኒቨርሲቲ፣

- በግቢው ውስጥ አምስት (5) ማህበራትና ግለሰቦች ኪራይ ሳይከፈሉ፣ እንዲሁም የመብራትና ውሃ በነጻ እየተጠቀሙ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይከፍሉ መሆኑን

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ባለፉት የበጀት ዓመታት የተሰበሰበውን ገቢ እና የሚኖሩ ለውጦችን ታሳቢ በማድረግ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከመማር ማስተማርና ከተለያዩ ገቢ ማመንጫዎች ሊሰበስብ የሚችለውን የገቢ መሰረተ ግምት ወይም የገቢ ዕቅድ ሊዘጋጅ እንደሚገባ እና በገቢ ሂሳብ አያያዝ፣ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ላይ የተከሰቱ ችግሮች ላይ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4 <u>የወጪ ሂሳብ፤</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን፤ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙንና የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎችች ተገኝተዋል፡፡

4.1 <u>የሂሳብ ማስተካከያ ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ፤</u>

የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኤጀንሲ ብር 5,684,887.92 ለትምህርት የሚሆኑ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ከAZT የህንፃ መሣሪያዎች መሸጫ ድርጅት ለተገዛው በችሮታ ጊዜ ይከፈላል በሚል በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም በጀት ባለመኖሩ ክፍያ ያልተፈጸመ እና የሂሳብ ማስተካከያም ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፤

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ኤጀንሲው በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ክፍያ ለፈጸመው ወጪ ብቻ ምዝገባ ማከናወን እንደሚኖርበት እና ለሂሳቡም ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.2 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣

በሃያ አምስት መ/ቤቶች ብር 85,007,096.62 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤-አባሪ 17 **ይመልከቱ**

አዲግራት ዩኒቨርሲቲ የውሎ አበል ሲከፍል ማወራረጃው ላይ ሰራተኞች በጉዞ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ በትክክል ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት እና ለአልጋ የተመደበው ሳይሞላ በጥቅሉ ሰራተኞች ሂደው በሚቆዩባቸው ቦታዎች ብቻ የተመደበውን ቀን ብዛት በማሰብ አበል የተወራረደ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የወጪ ትክክለኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ደጋፊ ሰነዶች ለኦዲት መቅረብ እንደሚኖርበት እና መረጃው ካልቀረበ የወጣው ወጪ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣

በሃያ ስድስት መ/ቤቶች ብር 44,848,365.62 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፤- **አባሪ 19 ይመልከቱ**

የአ/አ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 164,749.96 በግዥ ባለሙያ ባልሆኑ ሰራተኞች ወይም ለተመራማሪዎች ለምርምር ቁሳቁሶችና ግብአቶች ተብሎ በቀጥታ ገንዘብ በመስጠት ግዥ የተፈፀመ መሆኑን ተረጋግጠናል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውንም ክፍያ ሲፈፅም መንግስት ባወጣው የአከፋፈል መመሪያዎች እና ህጎች መሠረት መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.4 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች

በስምንት ዩኒቨርሲቲዎችና መ/ቤቶች ብር 10,842,100.91 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡**አባሪ 19/1 ይመልከቱ፡፡**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በመመሪያው ከተፈቀደው ተመን በላይ የተከፈለው የቤት ኪራይ አግባብነት እንደለሌው ታውቆ በልዩነት የተከፈለው ተመላሽ መደረግ እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

4.5 <u>በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ፣</u>

በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በሚመለከተው አካል ቀርቦ ሳይፈቀድ ከመመሪያው ውጭ በቋሚ የሥራ መደብ ማሰራት ሲገባው አለአግባብ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ቅጥር በመፈጸም በ2010 የበጀት ዓመት ውስጥ በድምሩ ብር 384,000.00 ደመወዝ የተከፈለ መሆኑን፣

<u>የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ</u> በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ለቋሚ የስራ መደብ የተፈቀደለትን የስራ መደቦች የምግብ ቤት ሰራተኞች፣ የፅዳት ሰራተኞች፣ የጉልበት ሰራተኞች በቋሚ ቅጥር መሸፈን የሚገባቸው ያለአግባብ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ቅጥር የተፈጸመ ሲሆን በተደጋጋሚ በየወሩ በቀን ሰራተኞች ምንዳ /6114/ በሚል ብር 5,979,752.29 የተከፈለ መሆኑን እና ከዚሁ ውስጥ ብር 817,275.20 በ6114 መመዝገብ ሲገባው በ6116 ያለአግባብ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር የሥራ መደቦቹን በማስፈቀድ በቋሚ ቅጥር ማሰራት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.6 <u>በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የትርፍ ሰዓት ክፍያ</u>

በአራት ዩኒቨርሲቲዎች ብር 883,627.97 ሚኒስቴር መ/ቤቱን ሳያስፈቅድ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡**አባሪ 28 ይመልከቱ**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴርን የትርፍ ሰዓት ክፍያን በማስፈቀድ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ መሆን እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

4.7 የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

በሃያ አምስት መ/ቤቶች

• ያለጨረታ በቀጥታ የተገዛ	ብር	42,932,766.72
• መስፈርቱን ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ	ብር	3,966,694.43
• በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ	ብር	22,899,607.18
• የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ	ብር	1,683,565.36
• ሌሎች የግዥ ሂደትን ያልተከተሉ	ብር	20,211,436.97
በጠቅላላው	ብር	91,694,070.66

የግዥ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ **አባሪ 21 ይመልከቱ፡፡**

4.8 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ እና በሪፖርት ያልተካተተ፣

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ብር 15,022,530.54 ወጪው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ እና በሪፖርት ያልተካተተ ወጪ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርስቲው ከያንዳንዱ ስራ ተቋራጮች ላይ ቀንሶ ያስቀረዉን ሂሳብ በተከፈይ ሂሳብ መዝግቦ በመያዝ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ስራ ተቋራጮች ተቀጽላ ቋት በመክፈት መቆጣጠር እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4.9 በናሙናው መሠረት ለመግባቱና አገልግሎት ለመሰጠቱ ያልተረጋገጠ፣

በአስር መ/ቤቶች በብር 21,299,443.25 ተገዝተው የገቡ ዕቃዎች በቴክኒክ ኮሚቴ ማረጋገጫ ሳይደረግባቸው ገቢ መሆናቸውን ተረጋግጧል፡፡ አባሪ 22 **ይመልከቱ፡፡**

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የግዥ ዘዴዎች ተገዝተው ገቢ የሚደረጉ ዕቃዎችን ጥራት እንደየዕቃው ተፈላጊ እውቀት ደረጃ የጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ በማቋቋም የዕቃው ደረጃ በመስፈርቱ መሰረት መሆኑ እየተረጋገጠ ገቢ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4.10 <u>የገቢም ሆነ የወጪውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ፣

- የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከተለያዩ የህክምና አገልግሎት የሰበሰበውን የውስጥ ገቢ ሂሳብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ የተመዘገበ ገቢ ብር 16,160,671.10 ከተሰበሰበው ገቢ ያወጣው ወጪ ብር 19,346,385.96 እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከተሰበሰበው ገቢ በላይ በመብለጥ ብር 3,185,714.86 ወጪ የሆነ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሰረት አንድ ላይ አጠቃሎ ሪፖርት ማድረግ ሲገባው የወጪውም ሆነ የገቢው ሂሳብ ሪፖርት ያልተደረገ በመሆኑ የገቢም ሆነ የወጪውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ የሚታየው ወጪ በዋና ግቢ ብር 787,631,246፣ በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 73,969,833.75 እና በዱራሜ ካምፓስ ብር 12,987,615.00 በድምሩ ብር 874,588,694.75 ሲሆን፣ በተመዘገበው የወጪ መጠን ሪፖርት መደረግ ሲገባው ተጠቃሎ ሪፖርት የሆነው ብር 869,888,465.58 በመሆኑ በልዩነት በብር 4,700,229.17 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ከተመዘገበው ወጪ በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፤

ዩኒቨርሲቲው የሁሉንም ኮሌጆች የአጠቃላይና የተቀጽላ ቋት ሚዘን ትክክለኛነት አረጋግጦ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት እና የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሂሳብ ቋት እና ተቀጽላ ቋቶች ሚዘን ትክክለኛነት ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4.11 <u>በድጋሚ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፣</u>

በሦስት ዩኒቨርሲቲዎች ብር 565,592.46 ሁለት ጊዜ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ **አባሪ** 24 ይመልከቱ

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የተፈጠረው ስህተት ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.12 **<u>ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ ፀድቆ ስለመገኘቱ፣</u>**

በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እስከ 100,000.00 ብር የመፍቀድ ጣሪያ የተሰጠው የፋይናንስና በጀት ዳይሬክተር በጠቅላላው ብር 4,172,688.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍያዎች በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ኃላፊዎች ከተሰጣቸው የመፍቀድ ሥልጣን ገደብ መሠረት መፈጸም እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

4.13 **<u>የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ፣</u>**

4.13.1 **<u>ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ፤</u>**

በኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 5,106,668.90 ያልተሰበሰበ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ኢንስቲትዩቱ ክፍያዎችን ሲፈጽም ስለ ትክክለኛነቱ ማረጋገጥ እንዳለበት፣ ከውስጥ ኦዲት ጋር በመሆን በተቀሩት የግንባታ ስራዎች ላይ ያሉትን ክፍያዎች ማረጋገጥ እንደሚኖርበት እና ያልተሰበሰበውም ገንዘብ እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

4.13.2 **<u>የጉዳት ካሳ ክፍያ ያልሰበሰቡ መ/ቤቶች በተመለከተ፣</u>**

በአስራ አንድ መ/ቤቶች ከዕቃ አቅራቢዎች የሚፈለግ ብር 2,248,991.08 እና ከስራ ተቋራጮች ብር 30,757,958.53 በድምሩ ብር 33,006,949.61 የጉዳት ካሳ ያልተሰበሰበሰ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ **አባሪ 8 ይመልከቱ፡፡**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የተጠቀሰው ገንዘብ ተሰብስቦ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.13.3 **<u>ያለአማካሪ ድርጅት የጸደቀ የክፍያ ሂሳብ፣</u>**

በአራት ዩኒቨርሲቲዎች ብር 114,959,683.05 በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል /በኮንስትራክሽን ሚ/ር/ የተረጋገጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል ሰርተፊኬትና ፍቃድ ሳይኖራቸው በአማካሪ ባልጸደቀ የምስክር ወረቀት ክፍያ እንደሚፈጸም በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ **አባሪ 20/1 ይመልከቱ፡፡**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም ግንባታ ሲከናውን የግንባታው የክፍያ የምስክር ወረቀት/Payment Certificate/ መጽደቅ ያለበት ወይም የማማከር ስራው መሰራት ያለበት ፈቃድ ባለው አማካሪ መሃንዲስ መሆን እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

4.13.4 <u>ከግዥ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ ያልተመዘገበ ሂሳብ፣</u>

በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የጉደር ወንዝ የውሃ ጉድጓድ መልሶ የግንባታ ስራ ለማሰራት ከሆሳዕና ከተማ ውሃ አገልግሎት ኢንተርፕራዝ ጋር ውል በመግባት ክፍያ የፈጸመ ቢሆንም የመያዣ ሂሳብ ብር 82,017.32 በክፍያ ሰርተፊኬት ላይ ተቀንሶ የሚታይ ቢሆንም በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ መያዝ ሲገባው ያልተያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከሥራ ተቋራጮች ጋር ውል ተገብቶ ለሚሰሩ ስራዎች በውሉ መሰረት የመያዣ ሂሳቦች ከእያንዳንዱ የክፍያ ሰርተፊኬት ላይ ተቀንሶ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ ቋት እና ተቀጽላ ቋቶች ተከፍቶለት መመዝገብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.13.5 <u>ሌሎች ከግንባታዎች ጋር የተያየዙ ችግሮች፣</u>

- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በመከናወን ላይ ያሉ የኮንስትራክሽንና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቀው ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን ወይም አገልግሎት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ግንባታዎች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ37 እስከ 188 ቀናት የዘገዩ መሆኑን፣
- **በመቱ ዩኒቨርሲቲ** ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት የፈርኒቸር ዕቃዎች ግዥ ብር 14,765,020.84 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ የውሉ አንድ አካል ሆኖ በግልፅ በውሉ ያላስቀመጠ በመሆኑ በውል ክፍተት ምክንያት የጉዳት ካሳ ለማስላትና ለመጠየቅ የማያስችል መሆኑን፣

- ➢ **አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ፣**
  - ያስገነባቸውን ግንባታዎች (ህንፃዎች) እንደቋሚ ንብረት በመዝገብ የማይመዘግብ መሆኑን፣
  - በመከናወን ላይ ያሉ የኮንስትራክሽንና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው (በተቀመጠለት) የጊዜ ገደብ መሰረት ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣
  - በድምሩ ብር 2,291,218.30 የሚያወጣ ሲሚንቶ በተቋራጮቹ በቀረበ መረጃ ብቻ የተቀነሰ ለመሆኑ እና በእያንዳንዱ ተቋራጭ የተወሰደው የሲሚንቶ ዕዳ በተሰብሳቢ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) የማይያዝ (የማይመዘገብ) መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት፣ የግንባታ ውል ሲዘጋጅ የዩኒቨርስቲውን ጥቅም የሚያስጠብቁ ሁኔታዎች በውል እንዲካተቱ፣ በቅድሚያ የሚሰጡ ስሚንቶና ሌሎች ዕቃዎች በተሰብሳቢ ሊያዙና በወቅቱ እንዲወራረዱ መደረግ የሚገባው እና ሕንጻዎች በተሰጣቸው ቁጥር መሠረት በንብረትነት መመዝገብ እንደሚገባቸው አሳስበናል፡፡

4.14 <u>ስልጣን ባለው አካል ሳይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያዎች፣</u>

በአስር መ/ቤቶች ስልጣን ባለው አካል ሳይፈቀድ ብር 10,513,986.23 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ አባሪ 29/1 ይመልከቱ፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በደንቡና መመሪያው መሠረት በሚመለከተው ሥልጣን በተሰጠው አካል የተፈቀደ ለመሆኑ ተጣርቶ መከፈል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.15 <u>ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ ሰነድ፣</u>

በአራት መ/ቤቶች የወጣው ወጪ ብር 142,840,824.60 ሰነዶቹ ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣- አባሪ 18 ይመልከቱ፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውን የመንግሥት ተቋም ለኦዲት የሚጠየቁ ሠነዶችን በወቅቱ በማቅረብ ኦዲት ማስደረግ እንዳለባቸው እና ያልቀረቡት ሠነዶች በውስጥ ኦዲት ተጣርተው ሪፖርት መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4.16 **በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ፣**

በአሰራ ዘጠኝ መ/ቤቶች ብር 73,116,748.19 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ **አባሪ 25 ይመልከቱ፡፡**

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በአዋጅ የተፈቀደ በጀት በተፈቀደበት በጀት ዓመት ውስጥ መፈጸም እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

4.17 **በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የበጀት ዝውውር የፈፀሙ፣**

በአምስት መ/ቤቶች ብር 26,195,153.19 በሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኙ የበጀት ዝውውር የፈፀሙ መሆኑ ተረጋገጧል፡፡ **አባሪ 20/2 ይመልከቱ፡፡**

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የበጀት ዝውውር ከመደረጉ በፊት አግባብ ባለው ሚ/ር መ/ቤት ፍቃድ ለመገኘቱ ተረጋግጦ ወጪ መደረግ እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

4.18 **በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣**

በስድስት መ/ቤቶች ብር 7,581,154.48 ወጪ በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ **አባሪ 33/1 ይመልከቱ፡፡**

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በደንቡ መሠረት ወጪ ከመደረጉ በፊት በበጀት ክፍል በጀት ስለመኖሩ መረጋገጥ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4.19 **በብልጫ የተከፈሉ ወጪዎች፣**

በአስራ አምስት መ/ቤቶች ለግንባታ እና የተለያዩ የግዥ ወጪዎች ብር 203,476.00 ለውሎ አበል ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች ብር 5,483,510.85 በድምሩ ብር 5,686,986.85 ያለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ **አባሪ 20 ይመልከቱ፡፡**

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ

- የጤናና ሳይንስ ኮሌጅ በአጠቃላይ ብር 62,118,693.08 ከዩኒቨርስቲው በተቀበለው የገንዘብ መጠን ወጪ ማድረግ ሲገባው፣ በተለያየ ሂሳብ መደብ መዝግቦ በድምሩ ብር 73,969,833.75 ወጪ ያደረገ ሲሆን፣ ብር **11,851,140.67** በብልጫ ወጪ ያደረገ መሆኑን፣
- የመክፈቻ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 4201 (ልዩ ልዩ ቅድምያ ክፍያዎች) የሰኔ 30/2009 ሪፖርት ላይ የሚታየው ሚዛን ብር 571,180.26 ሲሆን በሐምሌ 1/2009 የመክፈቻ ሂሳብ ሚዛን ብር 859,952.54 በልዩነት ብር 288,772.28 በብልጫ የሚታይ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 5059 (የመያዣ ሂሳብ) የሰኔ 30/2009 በሪፖርት ላይ የሚታየው ሚዛን ብር 265,419.55 በሐምሌ 1/2009 የመክፈቻ ሂሳብ ሚዛን ብር 435,662.76 በልዩነት ብር 170,243.21 በብልጫ የሚታይ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የተለያዩ ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት ከማስረጃዎች ጋር ተመሳክረው ክፍያ ሊፈጸም እንደሚገባ፣ ከተሰጠው የገቢ ሂሳብ በላይ ወጪ ማድረግ አግባብ አለመሆኑን፣ የመክፈቻ ሂሳቦች ወደሚቀጥለው ዓመት ሲዞሩ በልዩነት መተላለፍ እንደሌለባቸው እና አለአግባብ የተከፈለው ተመላሽ እንዲደረግ እና ለሂሳቦቹ የማስተካከያ እርምጃ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.20 <u>የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ፣</u>

በሃያ ሦስት መ/ቤቶች ብር 41,897,945.59 ተገቢ ባልሆነ የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ **አባሪ 26 ይመልከቱ**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የወጪ ሂሳቦች በወጪ ከመመዝገባቸው በፊት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመያዛቸው ሊረጋገጥ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.21 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ ሂሳብ፣</u>

በስምንት መ/ቤቶች ብር 5,113,574.43 ንብረቱ ገቢ መሆኑን የሚያረጋግጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ **አባሪ 23 ይመልከቱ**

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

ክፍያ በወጪ መመዝገብ የሚገባው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ከወጪው ማስረጃ ጋር ለመያዙ መረጋገጥ እንደሚገባው እሳስበናል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

የተከፋይ ሂሣቦችን በተገባው ግዴታ መሠረት እና በህግ በተቀመጠው አግባብ መሰረት በወቅቱ የሚከፈል መሆኑን እንዲሁም የተከፋይ ሂሣቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

5.1 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

በሃያ አራት መ/ቤቶች የቆይታ ግዜያቸው፡-

- ከአንድ ወር እስከ አንድ አመት የሆናቸው ብር 18,897,655.93
- ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሆናቸው ብር 34,549,832.46
- ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የሆናቸው ብር 140,392,138.44
- ከአስር ዓመት በላይ የሆናቸው …………… ብር 3,593,996.88
- የቆይታ ጊዜው ያልተተነተነ .... ብር 1,138,393.27

በአጠቃላይ በድምሩ …………................... ብር 198,572,016.98

የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ሳይወራረድ የሚገኝ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ **አበሪ 30 ይመልከቱ፡፡**

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

ማንኛውም የተከፋይ ሂሳብ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብና መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በውስጥ ገቢ መያዝ ሲገባው በተከፋይ የተያዘ</u>

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብር 31,900,513.31 በውስጥ ገቢ መያዝ ሲገባው በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ያለአግባብ እንደ ፕሮጀክት ሂሳብ ገቢ የሚደረገው ስልጠና፣ እንዲሁም ወደ ፕሮጀክት ሂሳብ ገቢ የተደረገው የስልጠና ገቢ በደንቡ መሠረት በውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ መደረግ እንዳለበት፣ ያለአግባብ ከውስጥ ገቢ መመሪያ እና ፀንቶ ከሚሰራባቸው ህጎችና መመሪያ ውጭ የአከፋፈሉ እና የስሌቱ መጠን ባልታወቀበት ክፍያ የተፈጸመው ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.3 **በተከፋይ መያዝ ሲገባው በወጪ የተያዘ፣**

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲው በዕቅድ ያልተያዘ እና በጀት ያልተፈቀደለት የመያዣ ሂሳብ በድምሩ ብር **3,126,737.51** በተከፋይ ሂሣብ (5061) መያዝ ሲገባው በሂሳብ መደብ 6322፣ 6323 እና 6324 በወጪ ተይዞ ለተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች የተከፈለ መሆኑን፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ለወጪው በጀት መያዙን እና የሂሳብ አያያዝ ተከትሎ በተገቢው የሂሳብ መደብ መመዝብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6. **የበጀት አጠቃቀም፣**

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 ክፍል 6 የመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 30 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 እስከ 26 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ በበጀት አዋጁ ለተመለከተው የመንግስት መሥሪያ ቤት እንዲከፈል በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ክፍያ መፈጸም እንደማይቻል በተገለፀው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

6.1 **ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ፣**

በሃያ አራት መ/ቤቶች በተለያዩ የወጪ አርእስቶች፣

- ከመደበኛ በጀት በአስራ ሰባት መ/ቤቶች ብር 104,467,892.41
- ከካፒታል በጀት በስድስት መ/ቤቶች ብር 186,032,496.76
- ከውስጥ ገቢ በአንድ መ/ቤት ብር 9,901,951.39

በድምሩ ብር 300,402,340.56

ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ **(አባሪ 33 ተያይዟል)**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማናቸውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት አስቀድሞ የተፈቀደ ወይም በዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ የተስተካከለ በቂ በጀት ለመኖሩ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አስገንዘበናል፡፡

6.2 <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት (ከ10% በላይ ልዩነት ያለው) ሂሣብ፣</u>

በሃያ ዘጠኝ መ/ቤቶች በተለያዩ የወጪ አርእስቶች ከ10% በላይ ያልተጠቀመባቸው፡-

• ከውስጥ ገቢ ሂሳብ በአራት መ/ቤቶች	ብር	16,494,391.50
• ከመደበኛ በጀት በሃያ ስምንት መ/ቤቶች	»	1,208,159,902.32
• ከካፒታል በጀት በአስራ ሰባትመ/ቤቶች	»	2,079,452,069.02
በድምሩ	ብር	3,304,106,362.84

ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ **(አባሪ 33 ይመልከቱ)**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የበጀት አጠቃቀሙን በተመለከተ የተመደበለትን በጀት በአግባቡ መጠቀም እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

7 <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር፣</u>

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 5 የመመሪያው አላማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት በታዘዘው መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	7
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	15
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	7
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	4
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢንካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	9
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	22
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	14
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	10
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	8
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋዉ (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለጹ እና ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ በዋጋቸው ብር 284,004.47 የሆኑ ይገኙበታል)	3

7.1 <u>ለንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፣</u> ከአባሪ 34/1 እስከ 34/10 ይመልከቱ

በሦስት መ/ቤቶች የለቀቁ ሰራተኞች (ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶችን ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ ተረጋግጧል፡፡በተለይም **በቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ** ብር 284,004.47 የሚያወጡ ንብረቶችን የለቀቁ ሠራተኞች ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆናቸው፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የመ/ቤቶቹ ሥራ አመራር በተጠቀሱት የአሠራር ክፍተቶች ላይ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.2 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም፣ ከአባሪ 35/1 እስከ 35/8 ይመልከቱ

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	1	1	
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	4	34	
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	1		5
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	1		15
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	3	3	
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው /ጌጅ የማይሰራ	2	8	
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	1		

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተጠቀሱት መ/ቤቶች ሥራ አመራር በታየው የአሠራር ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስገንዝበናል፡፡

8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት የተሰጠበት አጠቃላይ ገንዘብ፤ እርምጃ ተወስዶ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠንና ተመላሽ ያልተደረገ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ አባሪ-36 ተመልክቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

9. <u>ልዩ ልዩ ጉዳዮች፣</u>

<u>የውስጥ ኦዲት በተመለከተ፣</u>

በሰባት መ/ቤቶች *የውስጥ ኦዲት የስራ ክፍል በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል ያልተሟለ መሆኑን እና ለዳይሬክቶሬቱ ለብቻው ቋሚ የሆነ ቢሮ የሌላቸው በመሆኑ ስራቸውን በነፃነት ለመስራት እየተቸገሩ እንደሆነ እና ለኦዲት ስራ መገልገያ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ያልተማላቸው መሆኑን፣* **አባሪ 35/9 ይመልከቱ**

ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ *የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመመሪያው በተቀመጠው የሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የኦዲት ሪፖርቱን ለበላይ ኃላፊ ያላቀረበ መሆኑ፤*

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ
መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 30 ዩኒቨርስቲዎችና 1 መሥሪያ ቤት በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡

በዕቅድ የተያዙት መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የኦዲት ሥራቸው ተጠናቋል፡፡

ሀ/ የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 30 ዩኒቨርሲቲዎችና 1 መሥሪያ ቤት የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ ነው፡፡

በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2010 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት እና የበጀት ዓመቱን ሂሳብ የዘጉበትን ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

አባሪ -1

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	1,093,006,410.71	790,736,631.53	1,883,743,042.24
2	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	1,183,637,033.20	510,000,000	1,693,637,033.20
3	ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ	1,025,470,843.90	650,000,000.00	1,675,470,843.90
4	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	429,666,695.93	380,000,000	809,666,695.93
5	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	645,151,216.59	461,790,966.16	1,106,942,182.75
6	ሰመራ ዩኒቨርሲቲ	559,645,260.00	655,231,565.08	1,214,876,825.08
7	መቅደላ ዩኒቨርሲቲ	81,202,500	0.00	81,202,500
8	መዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ	507,960,483.60	462,696,423.16	970,656,906.76
9	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	1,139,972,484	501,971,825.11	1,641,944,309
10	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	1,069,554,731.61	1,001,729,451.41	2,071,284,183.02
11	ሚዛንቴፒ ዩኒቨርሲቲ	572,264,028.29	317,964,076.72	890,228,105.01
12	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	1,275,435,514.97	1,038,741,325.97	2,314,176,840.94
13	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	554,481,535.46	462,743,500.00	1,017,225,035.46
14	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	764,173,103.55	797,100,300.19	1,561,273,403.74
15	ጂንካ ዩኒቨርሲቲ	83,132,999.81	0.00	83,132,999.81
16	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	82,890,000	0.00	82,890,000
17	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	123,484,100.34	492,968,311.00	616,452,411.34
18	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ	718,400,288.94	491,967,088.25	1,210,367,377.19

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
19	ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ	83,895,000.00	0.00	83,895,000.00
20	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	449,623,500.00	500,000,000.00	949,623,500.00
21	ትምህርት ሚኒስቴር	3,295,090,193.55	2,878,896,570.00	6,173,986,763.55
22	ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ	156,425,300.00	0.00	156,425,300.00
23	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	1,192,483,917.29	983,925,964.42	2,176,409,881.71
24	ራያ ዩኒቨርሲቲ	81,683,327.54	0.00	81,683,327.54
25	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	1,143,755,792.96	936,975,806.18	2,080,731,599.14
26	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	697,182,071.82	428,059,343.00	1,125,241,414.82
27	አርሲ ዩኒቨርሲቲ	444,093,354.30	420,000,000.00	864,093,354.30
28	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	658,004,360.80	420,000,000	1,078,004,360.80
29	ቀብሪድሃር ዩኒቨርሲቲ	90,539,000.00	0.00	90,539,000.00
30	ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	440,920,609.75	422,000,000.00	862,920,609.75
31	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	1,093,006,410.71	790,736,631.53	1,883,743,042.24
		21,736,232,069.62	16,796,235,779.71	38,532,467,849.22

ለ/ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ15 መሥሪያ ቤቶች፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ14 መሥሪያ ቤቶችና አስተያት መስጠት ያልተቻለባቸው 2 ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ-1 ተመልክቷል፡፡

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች፤

በዳይሬክቶሬቱ የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶትችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ</u>

1.1 <u>ግኝት</u>፣

የጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ የገንዘብ መጠን ከብር 30,000.00 ወደ ብር 100,000.00 ከፍ እንደተደረገ በቁጥር ክሂመ39/7/9 በቀን 30/07/2007 በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በተጻፈ ደብዳቤ የተገለጸ ቢሆንም በሰኔ 30/2010 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ መግለጫ መሠረት ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር256,734.02 በጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ብር 437,376.00 በድምሩ ብር 694,110.02 በገንዘብ ያዥ ካዝና ተገኝቶ በጥሬ ገንዘብ የተቆጠረ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.2 **<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣**

የመንግሥትን ገንዘብ ከጥፋትና ከጉድለት ለመከላከል እንዲቻል ዩኒቨርሲቲው በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አንደሚገባው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.3 **<u>ግኝት</u>፣**

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 123,599.00 በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 27,173.28 በድምሩ ብር 150,772.28 በጀት ዓመቱ በሂሳብ መደብ 4202 በጥሬ ገንዘብ ጉድለት ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም እስከ ሰኔ 30/2010 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

1.4 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የዩኒቨርሲቲው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በልዩነት የታየው ገንዘብ በዩኒቨርስቲው አካውንት ገቢ ተደርጎ የገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ፤

2.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በአንድ ሚኒስቴር መ/ቤት እና በ24 ዩኒቨርሲቲዎች በጠቅላላው ብር 1,394,657,718.74 ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/

2.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ፤

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

2.2 ያልተሰበሰበ የገቢ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ቅድመ ግብር ክፍያና የጉዳት ካሣ

2.2.1 ግኝት፤

- ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓም ጀምሮ ተግባራዊ በተደረገው የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም ስለፌደራል የገቢ ግብር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 410/2009 መሰረት፣ ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሥራ ግብር ብር **17,996,743.81** ፤የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር **171,442.99** ፤ የቅድመ ግብር ክፍያ (withholding tax) ብር **549,097.52** እና

- የጉዳት ካሣ ከዕቃ አቅራቢዎች ብር 4,343,955.07 እና ከተቋራጮች ብር 253,617.01 በድምሩ ብር **4,597,572.08** ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 9/

2.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ተቀናሽ ያልተደረገው (ያልተሰበሰበው) የሥራ ግብር፤የተጨማሪ እሴት ታክስ፤የቅድመ ግብር ክፍያ (withholding tax) እና የጉዳት ካሣከሚመለከታቸው ሠራተኞችና ድርጅቶች ተመላሽ ተደርጎ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ እንዲደረግና ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.3 የግንባታ ቅድመ ክፍያ፤ የሱቅና የቢሮ ኪራይና በሌሎች ውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ሂሳብ ወለድና ቅጣት፤

2.3.1 ግኝት፣

ከክፍያው ላይ ያልተቀነሰ የቅድመ ክፍያ ሂሳብ እና ውሉን በመቋረጡ በዩንቨርሲቲው ለደረሰው ኪሳራ ብር ውሉን ባቋረጠው ህንጻ ተቋራጭ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ባህዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 11,347,814.34 እና ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,346,047.54 በድምሩ ብር 15,693,861.88 እና የሱቅና የቢሮ ኪራይና በሌሎች ውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 3,267,497.76 በጠቅላላ ድምር ብር 18,961,359.64 ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ከተቋራጮቹ የሚፈለገው የመንግሥት ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን፤ ያልተሰበሰበ ገቢ ከሚመለከታቸው ሠራተኞችና ድርጅቶች ተመላሽ ተደርጎ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ እንዲደረግና ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ሪፖርት ያልተደረገ የገቢ፣የወጪና የፕሮጀክት ሂሣብ፤

3.1 ግኝት፤

የገቢና ወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት ለመደረጉ ኦዲት ሲደረግ ፤ በ3 ዩኒቨርሲቲዎች ብር 99,255,715.83 የውስጥ ገቢና ብር 32,919,007.37 ከፕሮጀክት ገቢ ሂሳብ፤ እንዲሁም ብር 29,250,885.20 የወጪ ሂሳብ የሚታይ ቢሆንም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ የሰውነት መብት ያላቸው) ኢንተርፕራይዞች (ዙቴ የግብርና ምርት፤ ኩላኖ ማተሚያ እና ኩይሌ የእንጨት ብረታ ብረት ኮንስትራክሽን) የተቋቋሙ ሲሆን የትርፍና ኪሳራ (Income Statement) እና የሃብትና ዕዳ (Balance Sheet) የሂሳብ ሪፖርት ከተሟላ የሰነድ ማስረጃ ጋር ለኦዲት ሥራ እንዲቀርብልን በተደጋጋሚ ተጠይቆ ያልቀረበ በመሆኑ ኦዲት ለማድረግ አልተቻለም፡፡

3.1.1 የማሻሻያ ሃሳብ፤

የዩኒቨርሲቲዎቹ በመመሪያው መሠረት ሂሳቦቹን መዝግበው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት እንዲያደርጉ የኢንተርፕራይዞቹ የገቢና ወጪ ሂሳብ እንቅስቃሴ በዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ እየተመዘገበ ወቅታዊ የሂሣብ ሪፖርት እየተዘጋጀ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የስራ አመራሩ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.1.2 ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበን ሂሳብ በጀት ሳያስፈቅዱ ወጪ ያደረጉ፤

3.1.2.1 ግኝት፣

በበጀት ዓመቱ በዩኒቨርስቲው ቦርድም ይሁን በሌላ በሚመለከተው አካል ለመታወጁም ሆነ መፈቀዱን የሚገልፅ ማስረጃ ሳይኖር ከውስጥ ገቢ ብር 66,822,097.15 በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የተደረጎ ተገኝቷል፡፡

3.1.2.2 **የማሻሻያ ሃሳብ፤**

ከውስጥ ገቢ ወጪ ለማድረግ በየበጀት ዓመቱ የፀደቀ በጀት እንዲኖራቸው እና በሚመለከተው አካል ሲፈቀድ ብቻ ጥቅም ላይ ሊያውል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.3 በድጋሚ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ብር 177,440.00 መኖሩ፤

3.3.1 **ግኝት፤**

በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ በድጋሚ የተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ብር 177,440.00 መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.3.2 **የማሻሻያ ሃሳብ፤**

ያለአግባብ ያለማስረጃ ሁለት ጊዜ ተመዝግቦ የተገኘውን ሂሳብ ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግበት እንደሚገባ፤ በቀጣይ ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፤

4.1.1 **ግኝት፤**

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁምየገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው እና ከታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-21 ተመልክቶል/

1. በአስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች ጨረታ ሳይወጣ በብር 83,596,148.54 የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ
2. በአስራ ሦስት ዩኒቨርሲቲዎች ተከፋፍሎ በዋጋ ማወዳደሪያ ብር 44,925,016.48 ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
3. በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በብር 1,214,441.17መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ፣ የተገዛ መሆኑ፤
4. በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ቀደም ሲል ከተገዛው ከ25% በላይ በድምሩ ብር 9,001,699.77 ተጨማሪ ግዥ ተፈፅሞ የተገኘ መሆኑና የተጨማሪ ግዢ ትዕዛዝ መስጠት ከሚቻልበት ጊዜ ገደብ ውጭ (ከ6 ወር ጊዜ በላይ) ግዢው የተፈጸመ መሆኑ፤
5. በትምህርት ሚኒስቴር የተጨማሪ ሥራ እና ተለዋጭ ሥራ ውል ሥምምነት የተፈረመበት ማስረጃ ያልቀረበለት ብር ያልተፈረመ ብር 18,629,884.49 ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤
6. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የግንባታ ተለዋጭ ስራ /variation Order/ 30% መሆን ሲገባው ከመመሪያ ውጭ 37.846% እንዲጸድቅ በማድረግ ብር 1,270,586.85 ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤

4.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

- ዩኒቨርስቲዎቹ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲፈጽሙ፤
- በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት በማድረግ እንዲሁም በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ከተሳተፉት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ያቀረበው ዋጋ ጋር ተመሳክሮ ዋጋው የተጋነነ መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ግዥውን መፈጸም እንዳለባቸው፤
- የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት በመሆኑ አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እድል እንዲኖራቸው በዙር ሁሉም ሊሳተፉ የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበትና የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን እናሳስበናል፡፡

4.2 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>፤

4.2.1.<u>ግኝት፤</u>

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ (በውጪ ሀገር ለተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተከፈለ ክፍያ ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ዕቃዎች በተፈላጊው ባህሪ መሰረት መግባታቸው በጥራት ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ፤የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ፤ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ፤በእርዳታ ለመጡ የተለያዩ ዕቃዎች የቀረጥ ሂሳብ፤የተከፈለ በሚል በወጪ ለተመዘገበው ሂሣብ የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት፤ ፤ተማሪዎች በመስክ ልምምድ ለማድረግ በሄዱበት ወቅት ለተፈጸመው ክፍያ ማስረጃ ያልቀረበለት፤ በድምሩ ብር 516,299,420.06 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/

4.2.2. <u>የማሻሻያሃሳብ</u>፣

የተሟላ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ የወጪ ሂሣብ እንዳይወራረድ ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ እና ያለበቂ ማስረጃ በወጪ ለተመዘገበው ሂሣብ በአስቸኳይ ተገቢ ማስጃ እንዲቀርብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.3_ <u>ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>፤

4.3.1 <u>ግኝት፤</u>

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ከፋይናንስ ደንብና መመሪያ ውጭ (በዩኒቨርሲቲዎች ቦርድ ውሳኔ ለስፔሻሊስት ሐኪሞች ቶፕአፕ እና ክሊኒካል አበል፤ በዩኒቨርሲቲዎች ሥራ አመራር ውሳኔ ለሐኪሞች ማበረታቻ/ቶፕአፕ እና ለሌሎች ሰራተኞች አበል፤ ለተለያዩ የኮሚቴ አባላት ለማበረታቻ በሚል የተከፈለ፣ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ለትርፍ ሰዓት ሥራና ለትራንስፖርት የተከፈለ፤የአካዳሚክ ባለሙያዎች እና ሌሎች የንግድ ቤቶች ለተጠቀሙበት የተፈጸመው የመብራት ክፍያ ከሚመለከታቸው ተመላሽ (Refund) ያልተደረገ፤ ለደንብ ልብስ ማሰፊያ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ መፈጸሙ፤በአስተዳደር ቦታዎች (የሥራ መደቦች) ላይ የአካዳሚክ ባለሙያዎችን

በተደራቢነት በመመደብ በስራ አመራር ውሳኔ መሠረት የአንዋላይዜሽን እና የኃላፊነት አበል መፈጸሙ፤የመሬት ካሳ ክፍያ ለባለመብቶቹ ለመድረሱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ ....) በድምሩ ብር 94,092,844.08 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 19 ተመልክቷል/

4.3.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ክፍያዎችን ከደንብና መመሪያ ውጭ መፈጸም ተገቢ አለመሆኑን ገልጸን በመንግስት የፋይናንስ መመሪያ ያልተደገፉ ክፍያዎች እንዲቋረጡና ለቤት አበል አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ያልተፈቀደ የቀንና ኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር፤</u>

4.4.1 <u>ግኝት፤</u>

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው የሚገኙ ሰራተኞችን ቋሚ ለማድረግ በወጣው አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ቅጥር እንደማይፈፀም እንዲሁም ቅጥር ፈጽሞ የተገኘ የስራ ሃላፊ በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንደሚደረግ ይገልጻል፡፡ ሆኖም ግን በስድስት ዩኒቨርሲቲዎች ዘላቂነት ባላቸውና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኛ በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባቸው ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንን ሳያስፈቅዱ የቀንና የኮንትራት ሠራተኞችን በመቅጠር በበጀት ዓመቱ ብር 13,235,951.05 የደመወዝ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ- 19/1 ተመልክቷል/

4.4.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀንና የኮንትራትሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በቋሚ ሰራተኞች እንዲያዙ እንዲደረግ፤

ለቀንና ኮንትራትሰራተኞች እየተከፈለ ያለው ክፍያም እንዲቆም እና ለወደፊቱም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.5 <u>የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>፤

4.5.1.1<u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር (ተመራማሪዎች ጥናት ላቀረቡበት፣ ለድህረ ምረቃ (Msc and Phd) ተማሪዎች ፈተና ለፈተኑበት/ለገመገሙበት (Internal and External Examiner/Session) እና የማማከር አገልግሎት ለሰጡበት (Supervision) በጥቅሉ የHonorarium ክፍያ ከሚመለከተው አካል የጸደቀ የክፍያ ተመን ሳይኖረው በአስተዳደር ካውንስል በተወሰነው ተመን መሰረት፤ የመመረቂያ ጽሑፍ ለሚያማክሩ አማካሪ መምህራን፤ ፈተና ለማረም፣አሳይንመንት ለማረም፣ ፈተና ለማዘጋጀት፣ፈተናሱፐር ቫይዝ ለማድረግ፣ለሞጁል ዝግጅት እና ለሞጁል ኤዲተር፤ ለተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ የሚያዘጋጁበት የፋይናንስ ድጋፍ፤ የተማሪዎች የመመረቂያ ፅሁፍ ለገመገሙበት፤ ሞጁል ላዘጋጁ፣ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ላስተማሩ፣ፈተና ለፈተኑ እና ላማከሩ፤ …ወ.ዘ.ተ) በድምሩ ብር 27,100,320.16 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-19/2 ተመልክቷል/

4.5.2 <u>የማሻሻያሃሳብ</u>፣

በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ማስፈፀሚያ ተመን ውስን በመሆኑና ሁሉንም የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች የተማሪ ምርምር ስራን ማማከር፤ ፈተና ማውጣት፤ ፈተናና አሳይመንት ማረም፤ ሞጁል ማዘጋጀትና ኤዲት ማድረግ፤ የክትትል ስራ መስራትና ለመሳሰሉት በመንግስት የወጣ ተመን ባለመኖሩ ወይንም ባለመካተቱ ክፍያው በአብዛኛው ዩኒቨርስቲዎች የአከፋፈል ስርዓቱና የክፍያ መጠኑ የተለያየ በመሆኑ ለዩኒቨርቲው ተገቢነት ካለው ለከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በማቅረብ ሲፈቀድ ብቻ ሊከፈል ይገባል፡፡ ክፍያዎች በደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.6. በብልጫ የተከፈለ፤

4.6.1.ግኝት፤

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ለውሎ አበልና ትራንስፖርት እና ለዕቃና አገልግሎት ግዢዎች እንዲሁም ከተመን በላይ በ9 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 4,411,595.57 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

4.6.2 ማሻሻያ ሀሳብ፤

በብልጫ የተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ ክፍያዎች በጥንቃቄ እንዲፈጸሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.7. በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ፤

4.7.1 ግኝት፤

የገንዘብ ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደብ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ ብር 24,640,359.14 የወጪ ሂሣብተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-25 ተመልክቷል/

4.7.2 የማሻሻያ ሃሳብ፤

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ማንኛውም ሂሳብ በትክክለኛ የሂሳብ መደብ (ኮድ) መመዝገቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.8. በተሰብሣቢ መያዝ የሚገባው ሂሣብ ያላግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ

4.8.1 ግኝት፤

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 14 ቁጥር 4 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢውን የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል። በዚሁ መሰረት ክፍያዎች ህጋዊ የሆነ የወጪ ማስረጃ ቀርቦላቸው በወጪ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በአዲስ አበባ እና በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 117,484,486.39 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው አላግባብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል።

4.8.2 ማሻሻያ ሃሳብ፤

የወጪ ሂሳብ በሚመዘግብበት ወቅት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ማረጋገጥ እና የውል ማስከበሪያ እና የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዋናው ሰነድ ከክፍያ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ እንደሚኖርበት፡፡ ክፍያዎችም በአማካሪው ድርጅት ሊረጋገጡ እንደሚገባ እና ለተፈጠረው ስህተት ተገቢውን ማስተካከያ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4.9 ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገበ መሆኑ

4.9.1 ግኝት፤

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 35,020,535.36 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

4.9.2 ማሻሻያ ሃሳብ፤

የወጪ ሂሳብ በሚመዘግብበት ወቅት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ማረጋገጥ እና የውል ማስከበሪያ እና የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዋናው ሰነድ ከክፍያ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ እንደሚኖርበት፡፡ ክፍያዎችም በአማካሪው ድርጅት ሊረጋገጡ እንደሚገባ እና ለተፈጠረው ስህተት ተገቢውን ማስተካከያ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4.10 የበጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ ፤

4.10.1 ግኝት፤

በአምስት ዩኒቨርሲቲዎች በድምር ብር 115,253,819.67 ከ2010 በጀት ዓመት በፊት ለተከናወኑ የአገልግሎቶች ክፍያዎች ለ2010 በጀት ዓመት ከተመደበ በጀት ላይ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

4.10.2 ማሻሻያ ሃሳብ፤

የሚመደብለት በጀት በበጀት ዓመቱ ለሚያከናውኗቸው ተግባራት በመሆኑ በጀት አመቱን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ መመሪያን የጣሰ ከመሆኑ በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎች በበጀት እጥረት ምክንያት ላይሰሩ ስለሚችሉ ለወደፊቱ ሁሉን ክፍያዎች በተያዘለት የበጀት ዓመት በመክፈል ማስተካከል እንደሚኖርባቸው አሳስበናል፡፡

4.11 አግባብ ባለው ባለሥልጣንና ቦርድ ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

4.11.1 ግኝት፤

በአራት ዩኒቨርሲቲዎች በድምር ብር 13,808,161.80 አግባብ ባለው ባለሥልጣንና በቦርድ ሳይፈቀድ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡/ለዝርዝሩ በአባሪ-26/

4.11.2 ማሻሻያ ሃሳብ፤

ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ደንብና መመሪያ መሰረት ያደረገ ሊሆን እንደሚገባ እዲሁም ያለአግባብ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ ሆኖ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.12 በዩኒቨርሲቲው የግንባታና የመሰረተ ልማት ፅ/ቤት ያልተረጋገጠ የግንባታ ክፍያ

4.12.1 ግኝት፤

በአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ በግንባታና የመሰረተልማት ክትትል ፅ/ቤት ሳይረጋገጥ በአማካሪ መሐንዲስ በሚቀርበው ምስክር ወረቀት ብቻ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 218,132,618.33 መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.12.2 የማሻሻያ ሃሳብ ፣

የግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በተቋሙ ባለሙያዎች መረጋገጥ ወይም መጽደቅ ይኖርበታል፤ በግንባታ ፅ/ቤት ሳይፀድቅ/ሳይረጋገጥ/ የተከፈለውም የግንባታ ሂሳብ አግባብነት ሊጣራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.13 በግንባታ አማካሪ ድርጅት ባልተዘጋጀና ባልጸደቀ የክፍያ ሰርቲፍኬት የተከፈለ ክፍያ ብር 36,238,839.25 መኖሩ፤

4.13.1 ግኝት፤

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የማማከር ፈቃድ ሣይኖረው በግንባታና የመሰረተ-ልማት ክትትል ፅ/ቤት የክፍያ የምስክር ወረቀቶች ፀድቆ የተከፈለ የግንባታ ሂሳብ ብር 36,238,839.25 መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

4.13.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

የግንባታ ክፍያ ምስክር ወረቀት የግንባታ ማማከር ፈቃድ በተሰጠው አማካሪ መሀንዲስ እንዲፀድቅ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.14 <u>ለሥራ ተቋራጮች የብረትና ሲሚንቶ ቅድሚያ የተሰጠ ቢሆንም መከታተያ ሌጀር የሌለ በመሆኑ</u>

4.14.1 <u>ግኝት፤</u>

በትምህርት ሚኒስቴር ለአዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ለሥራ ተቋራጮች የብረትና ሲሚንቶ ቅድሚያ ብር 53,130,865.05 የተሰጠ ቢሆንም መከታተያ ሌጀር የሌለ በመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

4.14.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፤

ለእያንዳዱ ሥራ ተቋራጭ የተሰጠው የብረትና የሲሚንቶ ቅድመ ክፍያ መከታተያ ሌጀር እንዲከፈትለት አሳስበናል፡፡

4.15. <u>በድጋሚ፤ በብልጫ እና በማነስ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ</u>፤

4.15.1 <u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሳብ በተከፈለውና ማስረጃ በቀረበለት መሰረት በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በድጋሚ የተመዘገበ ብር4,296,258.42፤ በብልጫ የተመዘገብ ብር 57,945.00 እና በማነስ የተመዘገበ ብር 389,549.42 ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- ተመልክቷል/

4.15.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፤

ያለአግባብ ያለማስረጃ ሁለት ጊዜ ተመዝግቦ የተገኘውን ሂሳብ ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግበት እንደሚገባ፡፡ በተጨማሪ በቀጣይ ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.16. <u>አላግባብ የተከፈለ የግብር መቀጫ፤የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በወቅቱ ባለመክፍሉ ምክንያት አለአግባብ የተከፈለ የወለድ ቅጣት፣</u>

4.16.1.<u>ግኝት</u>

- በትምህርት ሚኒስቴር ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የግብር ቅድመ ክፍያ በወቅቱ ባለመክፈሉ ቅጣት ብር 8,580,063.06 እና ለዩናይትድ ኢንጅነርስ ኃ/የተ/የግ/ማ 2004 የተፈረደበትን ፍርድ በወቅቱ ባለመክፈሉ የ5ዓመት ከ91 ቀን ወለድ ብር 1,893,654.84 በድምሩ ብር 10,473,717.90 የተከፈለ መሆኑ፤
- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የግብር ቅድመ ክፍያ በወቅቱ ባለመክፈሉ በመቀጣቱና ቅጣቱንም በወቅቱ መክፈል እያለበት ባለመክፈሉ ምክንያት በድምሩ ብር 14,872,854.40 የቅጣት ወለድ የተከፈለ መሆኑ፤ በአጠቃላይ ድምር ብር **25,346,572.30** መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ መሆኑ፤

4.16.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፤

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የግብር ቅድመ ክፍያ እንዲሁም ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት መከፈል ያለባቸው ክፍዎች ወቅቱን ጠብቀው ሊከፈሉ ይገባል፡፡የመ/ቤቱ የበላይ ኃፊዎችም ሥራውን ለሚሰሩት ሰዎች እና የሥራ ክፍል ክፍያዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ ማስጠንቀቂያ መስጠት እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5. <u>የግንባታ ሂሳብ</u>

5.1 <u>በውላቸው መሰረት ሳይጠናቀቁ የተቋረጡ 12 ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤</u>

5.1.1 <u>ግኝት፤</u>

በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ሶስት ግንባታ

- በዋናው ግቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ቀሪ የግንባታ ሥራ ለማከናወን ከሼድ ኮንስትራክሽን ጋር የብር 50,028,180.56 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሠረት እስከ 10/01/2010 መጠናቀቅ ሲገባው ውሉ የተቋረጠ ሲሆን ግንባታው ያለበት ደረጃ 99% መሆኑ፤

- በዋናው ግቢ የወጥ ቤት የግንባታ ሥራ ለማከናወን ከታደሰ አደም ኮንስትራክሽን ጋር የብር 3,575,288.72 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሠረት መጠናቀቅ ሲገባው ውሉ የተቋረጠ ሲሆን ግንባታው ያለበት ደረጃ 70% መሆኑ፤
- በተርጫ ካምፓስ የስታፍ ላውንጅ፤ ሻውርና ሽንት ቤት የግንባታ ሥራ ለማከናወን ከማርቆስ መንገሻ ኮንስትራክሽን ጋር የብር 6,816,308.79 የግንባታ ሥራ ውል የተገባ ሲሆን በውሉ መሠረት እስከ 21/12/2009 መጠናቀቅ ሲገባው ውሉ የተቋረጠ ሲሆን ግንባታው ያለበት ደረጃ 40% መሆኑ፤

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ አንድ ግንባታ

- ተቋሙ በዘንዘልማ ግቢ ዓለማየሁ ከተማ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ሕንፃዎች ግንባታ ለማሰራት ተዋውሎ የሕንፃ ሥራው ተቋርጦ ይገኛል፡፡ በዋናው ውል ብር 151,577,813.58 ለተለዋጭ ሥራ /variation Order/ ብር 6,155,754.00 በድምሩ ብር 157,733,567.58 ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 69,690,121.60 የተከፈለው ሲሆን ከተቋሙ የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ተረጋግጦ በተሰጠን ማስረጃ ሥራው የደረሰበት ደረጃ 79.09% መሆኑና ከቀን 08-02-2010 ዓ.ም ጀምሮ በደብዳቤ ቁጥር 2-4240-2261 የሥራ ተቋራጩ የግንባታ ሥራውን ያቋረጠ መሆኑ፤
- **በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ** ስምንት ግንባታ ፕሮጀክቶች በጠቅላለው የገንዘብ መጠን ብር 47,528,485.17 የሆኑ ከ8 ወር እሰከ ከሁለት ዓመት በላይ የዘገዩ እና ያልተጠናቀቁ መሆኑ፤

በአጠቃላይ በሶስት ዩኒቨርሲቲዎች 12 የግንባታ ፕሮጀክቶች በውላቸው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳይጠናቀቁ የተቋረጡ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

5.1.2 **የማሻሻያ ሃሳብ፤**

- የግንባታ ሥራውን ካቋረጡ ኮንትራክተሮች ላይ የሚፈለግ ቅደመ ክፍያ በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲደረግና በመመሪያው መሰረት የጉዳት ካሳ በአግባቡ ተሰልቶ እንዲቀጡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.2. <u>ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ</u>፤

5.2.1 <u>ግኝት</u>፤

ግንባታ ፕሮጀክቶች በውሉና በተያዘላቸው ጊዜ ተጠናቀው ለታለመለት ዓለማ የዋሉ ለመሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 ዩኒቨርሲቲዎች የተለያየ የገንዘብ መጠንና አፈጻጸም ደረጃ ላይ ያሉ፤ ነገር ግን በወቅቱ ያልተጠናቀቁ 55 የግንባታ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤/ዝርዝራቸው በአባሪ- 20/5 ተመልክቷል /

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፤

የግንባታ ሥራዎች በታቀደው መሠረት እንዲከናወኑ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርትአሳስበናል፡፡

6. <u>በጀት</u>

6.1 <u>የበጀት አጠቃቀም</u>፤

6.1.1 <u>ግኝት</u>

ኦዲት በተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2010 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን ከመደበኛና ካፒታል በጀት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ ከመደበኛ በጀት ብር 184,926,854.41 እና ከካፒታ በጀት ብር1,101,707.81 በድምሩ ብር 186,028,562.22 እና ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ከመደበኛ ብር 2,073,124,990.27 እና ከካፒታል ብር 889,777,977.07 በድምሩ ብር 2,962,902,967.34 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 33 ተመልክቷል/

6.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፤

- ዩኒቨርሲቲዎችበዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ፤የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸውም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡
- ዩኒቨርሲቲዎቹየተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7 ተከፋይ ሂሳብ፤

7.1 ግኝት፤

የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 709,413,387.68 ውዝፍ የተከፋይ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል/

7.2 የማሻሻያ ሃሳብ፤

ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ ለባለመብቶች አለመክፈል ተጠያቂነትን ሊያስከትል እንደሚችል ጠቁመን ውዝፍ ተከፋይ ሂሳቦች እንዲወራረዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8 የዕቃና ንብረት አስተዳደር፤

8.1.ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፤

8.1.1.ግኝት፤

የዩኒቨርሲቲዎች የንብረት አያያዝና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተመለከቱት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች
ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	8
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	5
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	4
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	7
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	17
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	16
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	10
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	16
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	6
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	6
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ ፤	2

8.1.2. የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዕቃዎች በአግባቡ እንዲመዘገቡና በወቅቱ ሥራ ላይ እንዲውሉ፤ በግምጃ ቤት ውስጥ በአግባቡ እንዲጠበቁ፤ የተበላሹ ዕቃዎች በወቅቱ እንዲጠገኑና መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

9. የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም፤

9.1 ግኝት፤

የዩኒቨርሲቲዎች የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ የተመለከቱት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	1	4	
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	4	10	3
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣			
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	1	19	
ሊብሬው ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ/ ትራክተር	1	2	
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	2	7	11

9.2 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በብልሽት ምክንያት የቆሙት ተሸከርካሪዎች እንዲጠገኑ እና የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) የሌላቸው ሊብሬ እንዲወጣላቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10 በባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት የተሰጠበት አጠቃላይ ገንዘብ፤ እርምጃ ተወስዶ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠንና ተመላሽ ያልተደረገ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ አባሪ-36 ተመልክቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2010 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ
መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2010 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የ37 መሥሪያ ቤቶችንና ለቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት፣ ለቀድሞው የእንስሳትና ዓሣ ሀብት፣ ለቀድሞው የጤና ጥበቃና ለቀድሞው የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ 11 መሥሪያ ቤቶችን በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡

በዕቅድ የተያዙት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ መሥሪያ ቤቶች እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የኦዲት ሥራቸው ተጠናቅል፡፡

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

1.1. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የሰላሳ አምስት መሥሪያ ቤቶችን የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

1.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2010 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተቁ	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት		
		ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
1.	የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት	1,018,183,535.25	2,688,980,574.74	3,707,164,109.99
2.	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	91,828,325.37	19,500,000.00	111,328,325.37
3.	የኢትዮጵያ ጤናመድኅን ኤጀንሲ	173,621,340.00		173,621,340.00
4.	የቀድሞው ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርናገፈርሳ የአዕምሮ ማገገሚያ ማዕከል	171,317,293.57	1,133,864,390.89	1,305,181,684.46
5.	የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	124,241,601.36	31,903,367.18	156,144,968.54
6.	የቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	92,876,498.22	6,027,000,247.07	6,119,876,745.29
7.	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	30,984,000.00		30,984,000.00
8.	የቀድሞው የማዕድን፣ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	76,581,312.01	19,753,983.11	96,335,295.12
9.	የቀድሞው የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን	69,649,380.29		69,649,380.29
10.	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ	868,865,477.38	614,723,189.70	1,483,588,667.08
11.	የኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን	107,024,260.00	11,455,350.00	118,479,610.00
12.	የቀድሞው የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	55,000,000.00	80,000,000.00	135,000,000.00
13.	የቀድሞው የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት	131,188,634.24	1,254,773,982.27	1,385,962,616.51
14.	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	115,802,724.00	13,571,340.08	129,374,064.08
15.	የብሔራዊ የሜቲሮዎሮሎጂ ኤጀንሲ	75,000,000.00	62,786,214.47	137,786,214.47
16.	የቀድሞው የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	29,373,103.00	30,000,000.00	59,373,103.00
17.	የቀድሞው የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚ/ርና ተጠሪ ተቋማት	258,980,727.82	22,548,200.00	281,528,927.82
18.	የአለርት ማዕከል	148,749,545.58	115,000,000.00	263,749,545.58

ተቁ	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት		
		ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
19.	የቀድሞው የወጣቶችና ስፖርት ሚ/ር	161,915,673.61	1,020,000,000.00	1,181,915,673.61
20.	የቀድሞው የስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	86,544,479.11	520,232,000.00	606,776,479.11
21.	የቀድሞው ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	96,629,511.94		96,629,511.94
22.	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	12,682,486.00	6,700,000.00	19,382,486.00
23.	የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት	58,949,690.00		58,949,690.00
24.	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	9,556,000.00	50,000,000.00	59,556,000.00
25.	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	193,532,815.68	105,000,000.00	298,532,815.68
26.	የመንገድ ፈንድ የጽህፈት ቤት	8,100,460.00		8,100,460.00
27.	የፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ	38,915,000.00	9,000,000.00	47,915,000.00
28.	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት	26,150,170.00		26,150,170.00
29.	የቀድሞው ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	117,029,396.00	15,000,000.00	132,029,396.00
30.	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንትኢንስቲትዩት	58,956,174.00	7,000,000.00	65,956,174.00
31.	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	42,505,535.83	94,649,200.00	137,154,735.83
32.	የቀድሞው የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣንን	17,704,950.00	18,295,050.00	36,000,000.00
33.	የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ	231,670,850.79		231,670,850.79
34.	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	127,001,497.12		127,001,497.12
35.	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	61,559,349.45		61,559,349.45
36.	የኢትዮጵያ እስፔስ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት	39,421,586.24	21,500,000.00	60,921,586.24
37.	የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት	17,336,000.00	85,000,000.00	102,336,000.00
	ጠቅላላ ድምር	**5,045,429,383.86**	**14,078,237,089.51**	**19,123,666,473.37**

1.3. የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ6 መሥሪያ ቤቶች፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ11 መሥሪያ ቤቶች፣ ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት ደግሞ ለ14 መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ-1 ተመልክቷል፡፡

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በልማትና ማኀበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2010 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2. የገቢ ሂሳብ

2.1 በገቢ ግብር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ፤

2.1.1 ግኝት

ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች መንግሥት ገቢን ለመሰብሰብ ባወጣቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ገቢን የሚሰበስቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በገቢ አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል 2 አንቀጽ 12 እና ክፍል 6 አንቀጽ 25 እንዲሁም በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410//2009 ክፍል ሰባት አንቀጽ 54 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ….ወዘተ) ከወር ደመወዝ ጋር እተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ዘጠኝ መሥሪያ ቤቶችና አንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ከፈጸሙት የተለያዩ ክፍያዎች ላይ ብር 1,881,516.69 የሥራ ግብር ያልሰበሰቡ መሆኑ፤

2. በገኘሯው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም በወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ማንኛውም ወኪል በሚፈጽመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ ለገቢው ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ተገቢ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ሁለት መሥሪያ ቤቶችና አንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ከፈጸሙት የተለያዩ ክፍያዎች ላይ ብር 109,001.57 የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልሰበሰቡ መሆኑ፤

3. በገቢ አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል 10 አንቀጽ 92 (1) መሰረት የቅድሚያ ግብር ተቀናሽ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከአንድ መሥሪያ ቤት ብር 109,001.57 የቅድሚያ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

4. የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች የውጪ ሀገር ህክምና አገልግሎት በነፃ እንዲያገኙ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተፈቀደበትን መመሪያ ጠቅሶ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ጥቅምት 19 /1997 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር በጠ1/6/76 ባስተላለፈው መመሪያ መሰረትከወር ደመወዛቸው ላይ (2%) መዋጮ እንዲቀነስ የተላለፈው መመሪያ እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሚመሩ ዋና ዳይሬክተሮች እና ምክትል ዳይሬክተሮች የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅሞች አሰጣጥ በተመለከተ ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር መ30-899/4 በተላለፈው መመሪያ መሰረት ዋና ዳይሬክተሮች እና ምክትል ዳይሬክተሮች እንዲሁም ቤተሰቦቻቸው በጦር ኃይሎች ሆስፒታል የነጻ ህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ለዚሁም ከወር ደሞወዛቸው ላይ 1% የህክምና መዋጮ እንዲቀነስ የተላለፈው መመሪያ ተፈጻሚ መሆኑ ሲጣራ ከሁለት መሥሪያ ቤቶች ብር 5,459.48 የህክምና መዋጮ ያልተቀነሰ መሆኑ፤

በጠቅላላው ብር 2,258,290.32 ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ታውቋል፡፡
(ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)

2.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት በወጣው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ገቢን ያለመሰብሰብ ለመንግስት ገቢ መቀነስ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪም ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ስለሚችል መሥሪያ ቤቶቹ ያልተሰበሰበውን ገቢ መሰብሰብ እንዳለባቸው አሳሰበናል፡፡

2.2 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ላይ ያልተመዘገበ በሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ ፤

2.2.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 መሠረት ማንኛውም የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሂሳቦች በእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ እና በሂሳብ ሌጀር ላይ የሚወራረሱ መሆኑን በናሙና ለማረጋጥ የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ከተለያዩ ገቢዎች በሂሳብ መደብ 1489 ሰብስቦ ጥቅምት 9 ቀን 2010 ዓ.ም የገቢ ሂሳብ ማጠቃለያ ደረሰኝ (ሞዴል 64) ቁጥር 42478 ያዘጋጀለትን ሂሳብ ብር 11,467.00 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ላይ ያልመዘገበ እና በሂሳብ ሪፖርት ውስጥም ያላካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የገቢ ሂሳቡ ተመዝግቦ ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ የሂሳብ ምዝገባውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ ሳይሆን ሊቀር ስለሚችል ኮሌጁ የገቢ ሂሳቡን በመመዝገብ ሪፖርት እንዲያደረግ፤ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.3 በመንግሥት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ፤

2.3.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል አራት አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ይኸውም:-

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች አዳዲስ ዋጋን እንዲሁም በነባር ክፍያዎች ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስቴሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማጸደቅ እንዳለባቸው፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለኅብረተሰቡ የሚያቀርቡት ዕቃና የሚሰጡት አገልግሎት በመደበኛነት የሚከናወን ካልሆነ ወይም ለዕቃው እና ለአገልግሎቱ የሚጠየቀው የተናጥል ዋጋ ከብር 50.00 (ሃምሳ ብር) የማይበልጥ ከሆነ የክፍያው ልክ በሚኒስትሩ ሊጸድቅ እንደሚችል፤

ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሰረት ኦዲት የተደረጉ ገቢ የሚሰበስቡ መሥሪያ ቤቶች ለሰበስቡት ገቢ በመንግሥት የጸደቀ ታሪፍ መኖሩን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ሶስት መሥሪያ ቤቶችና አንድ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለሰበሰቡት ገቢ ብር 5,496,343.70 በመንግስት በጸደቀ ታሪፍ መሰረት አለመሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ- 13 ተመልክቷል/

2.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት የጸደቀ ታሪፍ ሳይኖር ገቢ መሰብሰብ የተሰበሰበውን ገቢ ለመለካት ካለማስቻሉም በተጨማሪ በአሰራርና በውስጥ ቀጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ስለሚችል መሥሪያ ቤቶቹ ለሚሰበስቡት ገቢ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 21 መሰረት ታሪፍ አውጥተው በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ማስደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

2.4 በትክክለኛው (በተገቢው) የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ የገቢ ሂሳቦች፤

2.4.1 ግኝት

የገቢ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ስስት መሥሪያ ቤቶች ከተለያዩ ገቢዎች የሰበሰቡት ገቢ በተለያዩ ብር 2,390,798.60 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝራቸውም በአባሪ- 15 ተመልክቷል/፡-

2.4.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የገቢ ሂሳቦች የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ላይ በተመለከቱት የሒሳብ መደቦች (ኮዶች) መሰረት የማይመዘገቡ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹ ትክክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆኑ ከመቻላቸውም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫው ለተጠቃሚዎች የተሳሳተ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቶች የገንዘብ ሚኒስቴር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን መሰረት አድርገው የገቢ ሂሳቦችን በተገቢው የሂሳብ መደብ መመዝገብ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

2.5 በጀት ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ወጪ የተደረገ ሂሳብ፤

2.5.1 ግኝት

ታህሳስ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር በጠ2/6/64 የገንዘብ ሚኒስቴር ያስተላለፈው መመሪያ ቁጥር 39/2006 የፌዴራል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎችም ከጥር 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲያውሉ የተፈቀደ ሲሆን በዋንኛነት በመመሪያው አንቀጽ 5(2) መሰረት ከዓመት ወደ ዓመት ቀጣይ ከሆኑና ሊታቀዱ ከሚችሉ ሥራዎች የሚገኘው የውስጥ ገቢ፡-

ሀ. የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በጤና ተቋማቱ ቦርድ የሚወሰን መሆኑ፣

ለ. ከላይ በፊደል "ሀ" ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተገኘው የገቢ መጠን የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ሙሉ ወጪ ሸፍኖ ተራፊው ገንዘብ የጤና ተቋማቱ ከዓመታዊ የበጀት ጥያቄ ጋር አቅርበው የውስጥ ገቢው በመንግሥት ሲታወጅ ለፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ማዋል ያለባቸው መሆኑ፣

ተመልክቷል፡፡

ሆኖም የአለርት ማዕከል በ2010 በጀት ዓመት ከሰበሰበው የውስጥ ገቢ ውስጥ ብር 9,096,740.32 በመመሪያው መሰረት በቅድሚያ የበጀት ጥያቄ አቅርቦ በመንግሥት እንዲታወጅ ሳያደርግ ሥራ ላይ ያዋለና በሂሳብ መግለጫ ውስጥ አካቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.5.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በመመሪያው መሰረት የውስጥ ገቢን ለመጠቀም የበጀት ጥያቄ ቀርቦ በመንግሥት እንዲታወጅ ሳይደረግ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል ስለሆነ ማዕከሉ ከውስጥ ገቢ የሰበሰበውን ገቢ መጠቀም እንዲችል በቅድሚያ በወጣው መመሪያ መሰረት የውስጥ ገቢው በበጀት እንዲታወጅ ማስደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

2.6 ተገቢ የሆነ ማስተካከያ ያልተሰራለት የገቢ ሂሳብ፤

2.6.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የሚሰሩት የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባዎች ትክክለኛና የፋይናንስ ህጉን የተከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ የጤና መድኅን ኤጀንሲ ከዚህ በጀት ዓመት በፊት በተደረጉ ኦዲቶች ከመመሪያ ውጪ በብልጫ የከፈለው የውሎ አበል ተመላሽ እንዲያስደርግ በተሰጠው አስያየት መሰረት በዚህ በጀት ዓመት ብር 106,987.17 ተመላሽ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ሆኖም ገንዘቡ ተመላሽ ሲደረግ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ (4103/4101) በዴቢት የተጣራ ሃብት (5601) ክሬዲት ተደርጎ ምዝገባ ተከናውኖ ገንዘቡ ፈሰስ መደረግ ሲገባው አጀንሲው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብን (4103/4101) ዴቢት የገቢ ሂሳብን (1489) በክሬዲት በመመዝገብ እንደ በጀት ዓመቱ ገቢ አድርጎ የመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.6.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ በተገቢው ሁኔታ ካልተሰራ በሂሳብ መግለጫው ላይ በየሂሳብ መደቡ የተመለከቱት ሂሳቦች ትክክለኛውን ሒሳብ እንዳያሳዩ ምክንያት ሊሆኑ ከመቻላቸውም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቱ የሒሳብ ማስተካከያ ምዝገባ ሲያከናውን በፋይናንስ ሥርዓቱ መሰረት በአመዘጋገብ ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

3.1 <u>በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ</u>፤

3.1.1 <u>ግኝት</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በሃያ መሥሪያ ቤቶች እና በስምንት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር **410,241,540.57** ከ1994 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን፤ የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ/ በአባሪ- 6 /ቀርቧል፡፡

ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰብ (ሳይወራረድ) ከቆየው ሂሳብ ከፍተኛውን መጠን ከያዙት ውስጥ :-

1. ከቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 282,965,014.42፣
2. ከቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ በሚገኙት ተጠሪ ተቋማት ብር 84,303,107.08 ፣
3. ከቀድሞው የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ሚኒስቴር 7,394,836.88፣ በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

2.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡት ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው በተደጋጋሚ አሳስበናል፡፡

2.2 መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፤

2.2.1 ግኝት

በተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery Ledger) ላይ የተመለከቱት ተሰብሳቢ ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በስድስት መሥሪያ ቤቶች እና በአራት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በተለያዩ የሂሳብ ኮዶች የተመለከቱት የተቀጽላ ሌጀሮች ሚዛን በጠቅላላው ብር **28,833,240.44** መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን ሳይጠብቁ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ መሆናቸው ታውቋል፡፡ መደበኛ ሚዛናቸውን ካልጠበቁት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ :-

1. በቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ በሚገኙት ተጠሪ ተቋማት ብር 26,279,003.85፣
2. በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 2,400,711.24 ፣

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ (ለዝርሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

2.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ አጠቃላይ ሌጀሮቹ ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን እና የሂሳብ ምዝገባውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ስለሚችል የጥሬ ገንዘብና ተሰብሳቢ ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና፤ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.3. ከግንባታ ክፍያዎች ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ፤

2.3.1. ግኝት

የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በውሉና በህጉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና የአመዘጋገብ ሥርዓቱም የገንዘብ ሚኒስቴር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ኤፍ.ኤ.ዋይ.ኦ ክንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ከውል ውጪ በብድር ከሰጠው ውስጥ ብር 20,000.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.3.2. የማሻሻያ ሃሳብ

መሰብሰብ የሚገባው ገንዘብ ካልተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ ባክኖ እንዲቀር ምክንያት ሊሆን ስለሚችል የቅድሚያ ክፍያው ሂሳብ እንዲሰበሰብ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3 ተከፋይ ሒሳብ

3.1 ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ ሂሳብ፤

3.1.1 ግኝት

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል በተገባው ውልና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአሥራ ሁለት መሥሪያ ቤቶች እና በሰባት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች

በጠቅላላው ብር 15,496,255.70 **ከ1994 ዓ.ም** ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝ ሲሆን፣ የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ለረጅም ዓመታት ከፍተኛውን የተከፋይ ሂሳብ መጠን ከያዙት ውስጥ፡-

1. በቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴርና በሥሩ በሚገኙት ተጠሪ ተቋማት ብር 7,430,548.54 ፣
2. ከአለርት ማዕከል ብር 3,139,791.63፣
3. ከቀድሞው የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 1,470,665.61 ፣

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 30 ተያይዟል)

3.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ስለሚችሉ መሥሪያ ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳቦቹን ሁኔታ በማጣራት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

3.2 መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተከፋይ ሂሳብ፤

3.2.1 ግኝት

በተከፋይ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery Ledger) ላይ የተመለከቱት ተከፋይ ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በስድስት መሥሪያ ቤቶች በተለያዩ የሂሳብ ኮዶች የተመለከቱት የተቀጽላ ሌጀሮች ሚዛን በጠቅላላው ብር **8,835,775.39** መደበኛ የክሬዲት ሚዛናቸውን ሳይጠብቁ ዴቢት ሚዛን የሚያሳዩ መሆናቸው ታውቋል፡፡ ዝርዝራቸው በአባሪ- 32 ቀርቧል፡፡

3.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የተከፋይ ሂሳቦች መደበኛ የክሬዲት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ አጠቃላይ ሌጀሮቹ ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆኑ እና የሂሳብ ምዝገባውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ስለሚችል ተከፋይ ሂሳቦች መደበኛ የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና፤ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.3 ከግዥ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብና ያልተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ፤

3.3.1 ግኝት

ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም እንደገና ለማሻሻል ባወጣው መመሪያ መሰረት ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸዉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ከብር 5,000.00 በላይ ከሚፈጸም ግዥ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያዉን በመቀነስ እና ለተጨማሪ እሴት ታክሱ ደረሰኝ በመቁረጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸዉ በተመለከተው መሰረት መሥሪያ ቤቶች ታክሱን ቀንሰው ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ከፈጸመው ግዥ ላይ ብር 7,880.94፤
2. በቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ከፈጸመው የግንባታ ክፍያ ላይ ብር 63,630.09፤

በድምሩ ብር 71,511.03 የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተቀነሰ መሆኑ፤

3. በቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር ከገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ደግሞ ከፈጸመው የግንባታ ክፍያ ላይ የተቀነሰው የመያዣ ሂሳብ ብር 358,235.44 ያልተመዘገበ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በወጣው መመሪያ መሰረት ገቢን ያለመሰብሰብ መንግሥት ከታክስ ማግኘት የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ስለሚችል መሥሪያ ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክሱን በመሰብሰብ ለገቢው ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው እንዲሁም ተቀንሶ ያልተመዘገበው ገቢ እንዲመዘገብ መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

3.4 ተገቢ ያልሆነ የማስተካከያ ምዝገባ የተሰራለት ተከፋይ ሂሳብ፤

3.4.1 ግኝት

በገንዘብ ሚኒስቴር የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተለያዩ ምክንያቶች ለተፈጸሙ የምዝገባ ስህተቶች የማስተካከያ ምዝገባ እንዲሰራላቸው የሚደረግ ሲሆን የማስተካከያ ምዝገባ የተሰራላቸው ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

1. <u>የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት</u>

   1.1. ከ1998 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ለየኮሌጆቹ ለሥራ ማስኬጃ የላከው ሂሳብ በአጣሪ ኮሚቴው ተጣርቶ ሰኔ 30 ቀን 2010 ዓ.ም በጆርናል ቫውቸር ቁጥር 176459 የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ በመዝገብ አልተመዘገቡም ተብለው የማስተካከያ ምዝገባ ከተደረገለት ሂሳብ ብር 3,296,230.79 ውስጥ ብር 1,263,383.55 በ1997,1999 እና በ2000 በጀት ዓመት በመዝገብ ተመዝግበው የተገኙ መሆኑ፤

   1.2. በአጣሪ ኮሚቴው በመዝገብ አልተመዘገቡም ተብለው ሰኔ 30 ቀን 2010 ዓ.ም በጆርናል ቫውቸር ቁጥር 176458 እና 176459 ለደመወዝ ተከፋይ የማስተካከያ ምዝገባ ከተሰራለት ሂሳብ 17,893,459.62 ውስጥ ከላይ በተራ ቁጥር 1.2 የተመለከተው ብር 1,263,383.55 ተቀንሶ ቀሪው ብር 16,630,076.07 በ1997,1999 እና በ2000 ዓ.ም በመዝገብ አልተመዘገቡም ተብለው በዴቢት 5004 (የደመወዝ ተከፋይ ሒሳብ) በክሬዲት ደግሞ 4210 (ተሰብሳቢ ሂሳብ) እንዲሁም 5601 የተጣራ ሀብት ክሬዲት ተደርጎ ማስተካከያ ምዝገባ የተደረገ ቢሆንም የማስተካከያ ምዝገባ ለተሰራላቸው ሂሳቦች ቀደም ብሎ ተሰብሳቢ ሂሳቡ እና የወጪ ሂሳቡ ዴቢት ተደርጎ የተመዘገበ ምዘገባ እንዲሁም የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ክሬዲት ተደርጎ የተመዘገበ ምዝገባ አለመኖሩ፤

2. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በ2010 በጀት ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ለሰራተኞች ላልተከፈሉ የደመወዝ ጥቅል፣ የተጣራ ተከፋይና ተቀናናሽ ሒሳቦች ማስተካከያ የተሰራላቸው ቢሆንም ማስተካከያው በተሟላ ሁኔታ ባለመሰራቱ ለብር 81,074.67 በዴቢትና በክሬዲት ተገቢው ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፤

ታውቋል፡፡ በመሆኑም የተከፋይ ሂሳቡ የማስተካከያ ምዝገባ አግባብ ነው ብሎ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለሂሳቦች የማስተካከያ ምዝገባ ሲከናወን የሂሳቡ ሁኔታ በሚገባ ተጣርቶና በተገቢው ማስረጃ ካልተደገፈ ለተጨማሪ ስህተት ሊዳርግ ከመቻሉም በተጨማሪም ለጥፋትና ለጉድለት መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡ ስለሆነም የሂሣብ ማስተካከያው ሲሰራ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት እንዲሁም ስህተቱ በየትኛው የገቢና የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈጸመ በግልጽ መታወቅና በተገቢው ማስረጃ መደገፍ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4 <u>የወጪ ሂሳብ</u>

4.1 <u>የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>፤

4.1.1 <u>ግዥት</u>

በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለወጪ ሂሳቦች ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው ለመሆኑ እንዲሁም የቀድሞው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ነሀሴ 2001 ዓ.ም ባወጣው የደረሰኝ አያያዝ አጠቃቀምና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 28/2001 ክፍል 4 ተራ ቁጥር 3 ላይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ያልተመዘገበ ግብር ወይም ታክስ ከፋይ የሚጠቀምበት ደረሰኝን በተመለከተ በቀረበው ዝርዝር መሰረት መሥሪያ ቤቶች የግዥና የአገልግሎት ግዥ ፈጽመው ያቀረቡት ደረሰኞች አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በቀድሞው የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን በመስክ ሥራ ወቅት በብር 8,351.11 ነዳጅና የመሳሰሉት ግዥዎች ተፈጽመው የቀረቡት ደረሰኞች ፤

2. በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የባህርዳር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የነዳጅ፣ የሲሚንቶ እና የድንጋይ ግዥ በብር 18,294.10 ተፈጽመው የቀረቡት ደረሰኞች፤

3. በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የተጠቀሱት መረጃዎች ባልተሟላና ለመኪና ጥገና ተከናወኖ ለብር 77,000.00 ክፍያ የቀረበው ደረሰኝ፤

በጠቅላላው ለብር 103,645.21 የቀረቡት ደረሰኞች ተዓማኒነት የሌላቸውና አጠራጣሪ መሆናቸው ታውቋል፡፡

4.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

1. የግዥና የአገልግሎት ግዥ ተፈጽመው ህጋዊ ደረሰኞች ካልቀረቡ አቅራቢው ታክስን ለመሰወር ሊጠቀምበት ከመቻሉም በተጨማሪ ለገንዘብ ብክነትና ጥፋት መንገድ ሊከፍት ስለሚችል በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ካልተመዘገቡ ግብር ወይም ታክስ ከፋይ አቅራቢዎች ግዥ ተፈጽሞ መቅረብ ያለበት ደረሰኝ የቀድሞው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው የደረሰኝ አያያዝ አጠቃቀምና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 28/2001 ክፍል 4 ተራ ቁጥር 3 ላይ በዝርዝር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ያሚሉ መሆን እንዳለባቸው፤

2. የውሎ አበል ክፍያና የነዳጅ ግዥ የተፈጸመበት ቦታ ከተለያየ የክፍያውን አግባብነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በላይ በክትትልና የቁጥጥር ሥራው ላይ ክፍተት መኖሩን ከማመላከቱም በተጨማሪ ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ ሁኔታው ተጣርቶ ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፤

እናሳስበናል፡፡

4.2 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፤

4.2.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት መሥሪያ ቤቶች የፈጸሙት ክፍያዎች በወጪ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰባት መሥሪያ ቤቶች እና በሁለት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በጠቅላላው ለብር 19,133,218.94 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ የተመዘገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው ከመዘገቡት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ከፍተኛውን መጠን የያዙት፡-

1. የቀድሞው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 13,456,488.42፣
2. የቀድሞው የእንስሳትና ዓሣ ሃብት ሚኒስቴር ብር 3,261,263.28፣
3. የቀድሞዉ የማዕድን ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ብር 1,519,399.18፣

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 18 ተያይዟል)

4.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለክፍያዎች የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም በተጨማሪ የወጪ የሂሳቡን ተዓማኒነት ሊያሳጣ የሚችል በመሆኑ መሥሪያ ቤቶቹ የወጪ ማስረጃ ላልቀረበላቸው ክፍያዎች የወጪ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው፤ የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ ደግሞ በተሰብሳቢ ሂሳብ በመያዝ ገንዘቡ ተመላሽ ማስደረግ እንዳለባቸው እናሳስበናል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ወጪ የፈጸሙ መሥሪያ ቤቶች፤

4.3.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የፈጸሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መሰረት አድርገው የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአምስት መሥሪያ ቤቶች የወጡትን ህጎች ሳይከተሉ በጠቅላላው ብር 1,125,120.38 ክፍያ የፈጸሙ መሆኑ ታውቋል፡፡
ዝርዝራቸውም በአባሪ- 19 ቀርቧል፡፡

4.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች የፈጸሚቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ካልተከተሉ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ያለውን ክፍተት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቶች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.4 በመንግሥት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች፤

4.4.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች ለሚፈጽሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የተፈቀዱ እንዲሁም ክፍያዎቹም የተፈጸሙት በተፈቀደው መመሪያና የክፍያ ታሪፍ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አምስት መሥሪያ ቤቶች የፈጸሚቸው ክፍያዎች በመንግሥት ሳይፈቀድ እና በመመሪያ ከተፈቀደው የክፍያ ታሪፍ በላይ በጠቅላላው ብር 3,181,130.68 ክፍያ የፈጸሙ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝራቸውም በአባሪ-19/3 ቀርቧል፡፡

4.4.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች ክፍያዎችን በመንግሥት በተፈቀደው መመሪያና የክፍያ ታሪፍ መሰረት የማይፈጽሙ ከሆነ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን ተገንዝበው ክፍያውን በተፈቀደው መመሪያና የክፍያ ታሪፍ (ተመን) መሰረት ብቻ መፈጸም እንዳለባቸው፤ ክፍያው በመንግሥት ያልተፈቀደ ከሆነ ደግሞ እንዲፈቀድ ማስደረግ ያለባቸው ለመሆኑ እና ነገር ግን ክፍያውን ለመፈጸም የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይኖር ክፍያ መፈጸም ግን ተገቢ ስላልሆነ አሰራሩ እንዲስተካከል እና አለአግባብ የተፈጸመው ክፍያም ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.5 በብልጫ (አለአግባብ) የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎች፤

4.5.1 ግኝት

ለውሎ አበል፣ ለደመወዝና ለመሳሰሉት ሌሎች ወጪዎች እንዲሁም ለግንባታና ለተለያዩ ግዥዎች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግሥት የወጣውን ደንብና መመሪያ ተከትለው የተፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በአንድ መሥሪያ ቤት ግዥ ሲፈጸም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት እያለ ያለምንም ተጨባጭ ምክንያት ክፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥው በመፈጸሙ እና በግዥ ውል ሥምምነት ከተደረገበት የገንዘብ መጠን በላይ በመከፈሉ ምክንያት ብር 232,982.50 አለአግባብ መፈጸሙ፤
2. በአሥራ አምስት መሥሪያ ቤቶችና በሶስት መሥሪያ ቤቶች ለውሎአበል ለደሞወዝና ሌሎች ክፍያዎች ብር 18,713,232.00 አለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ፡-

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 20 ተያይዟል)

4.5.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለውሎ አበል፣ ለደመወዝና ለመሳሰሉት ሌሎች ወጪዎች እንዲሁም ለግንባታና ለተለያዩ ግዥዎች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግሥት የወጣውን ደንብና መመሪያ ተከትለው ካልተፈጸሙ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ከመሆናቸውም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ያስከትላሉ፡፡ በመሆኑም የወጣውን ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ፤ ለወደፊቱም ክፍያዎች በመንግሥት በተፈቀደው ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.6 በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ያልተፈጸሙ ግዥዎች፤

4.6.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣው የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በሁለት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በብር 1,406,092.18 ግዥው በቀጥታ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

2. በሶስት መሥሪያ ቤቶችና በሁለት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በብር 10,091,368.73 በዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

3. በአራት መሥሪያ ቤቶች የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በብር 980,086.13 ግዥው በቀጥታ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

4. ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣው መመሪያ ክፍል 5 አንቀፅ 25 ተራ ቁጥር 7 መሠረት ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 5,000.00 ያልበለጡ ዕቃዎችን ውይም አግልግሎቶችን ወይም በጉዞ ወቅት የሚያጋጠሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ የቀጥታ ግዥ መፈፀም ይችላሉ፡፡

ሆኖም በዚህ አይነት የሚፈጸሙ ጥቃቅን ግዥዎች ድምር በበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 75,000.00 መብለጥ እንደሌለበት በግዥ መመሪያው ላይ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ሶስት መሥሪያ ቤቶች በግዥ መመሪያው ከተፈቀደው በላይ በበጀት ዓመቱ በብር 714,877.98 የቀጥታ ግዥ የፈጸሙ መሆኑ፤

5. አንድ መሥሪያ ቤት ግዥ የፈጸመበት ድርጅት ብቸኛ አቅራቢ ለመሆኑ ማረጋገጫ ሳያቀርብ ብቸኛ አቅራቢ ነው በሚል በብር 183,317.48 ግዥውን በቀጥታ የፈጸመ መሆኑ፤

6. በአንድ መሥሪያ ቤት በብር 114,792.98 ለተፈጸመው የአፈር ምርመራ አገልግሎት የሥራ ውል ሥምምነት ያልተፈጸመ (ያልቀረበለት) መሆኑ፤

ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 21 ተያይዟል)

4.6.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ግዥዎች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው የማይፈጸሙ ከሆነ፡-

- በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤
- የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል የሚያደርግ መሆኑ፤
- ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን የሚችል በመሆኑ፤
- ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ፤

መሥሪያ ቤቶች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 ቀረጥ የተከፈለላቸው ዕቃዎች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ስለመሆኑ፤

4.7.1 ግኝት

በፋይናንስ መመሪያው መሠረት በግዥና በዕርዳታ ለሚገቡ ዕቃዎች የሚከፈለው የቀረጥ ሂሳብ ለሂሳብ አሰራር እንዲያመች ጥሬ ገንዘብ ነክ ባልሆነ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች በናሙና ሲጣራ ኦዲት ሲደረግ አምስት መሥሪያ ቤቶች በ2010 በጀት ዓመት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጻፈለቸው ደብዳቤ መሠረት የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ አከናውኗል፡፡ ሆኖም በ5 መ/ቤቶች ብር **49,150,561.33** ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያያዝ (እንዲቀርብ) ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝራቸው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

4.7.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ቀረጥ የተከፈለባቸው ንብረቶች ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኞቹ (ሞ/19) ቀርበው ከክፍያ ሰነዱ ጋር እንዲያያዙ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.8 በድጋሚና በብልጫ የተመዘገበ እና ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤

4.8.2 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት ነሐሴ 1999 ዓ.ም የገንዘብ ሚኒስቴር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

1. በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ስርቬይ ብር 200,527.67 እንዲሁም በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ 29,850.00 በድምሩ ብር 230,337.67 በድጋሚ የተመዘገበ መሆኑ፤
2. በቀድሞው የእንስሳትና የዓሣ ሃብት ሚኒስቴር ብር 27,420.55 እንዲሁም

በገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ብር 506,414.89 በድምሩ ብር 533,835.44 በብልጫ የተመዘገበ መሆኑ፤

3. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ብር 120,193.48 ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ መኖሩ፤

ታውቋል፡፡

4.8.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የገንዘብ ሚኒስቴር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ ምዝገባ ያለማከናወን የተዘጋጀዉን የሂሳብ መግለጫ ታዓማኒነት ሊያሳጣዉ እንዲሁም ለመንግሥት ገንዘብ አላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን የሚችል በመሆኑ በሂሣብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ላይ በድጋሚና በብልጫ የተመዘገበው ሂሳብ ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራለት እንዲሁም ያልተመዘገበው ሂሳብ እንዲመዘገብ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.9 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ የወጪ ሂሳቦች፤

4.9.2 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአሥራ ዘጠኝ መሥሪያ ቤቶችና በአራት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች የተፈጸሙት ክፍያዎች ብር 13,950,444.23 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 25 ተያይዟል)

4.9.3 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የሒሳብ መደቡን (ኮዱን) ጠብቀው የማይመዘግቡ ከሆነ የተዘጋጀዉን የሂሳብ መግለጫ ታዓማኒነት ሊያሳጣው ስለሚችል በሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት የሒሳብ መደቡን (ኮዱን) ጠብቀው መመዝገብ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.10 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የግንባታ ክፍያ፣

4.10.1 ግኝት

የገንዘብ ሚኒስቴር ነሐሴ 1999 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ለግንባታ ሥራ የሚፈጸሙ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች በየደረጃው የክፍያ ሰርተፊኬት እየቀረበ በወጪ እስኪመዘገብ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የቀድሞው እንስሳትና ዓሣ ሃብት ሚኒስቴር ነሐሴ 15 ቀን 2009 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 427705 ብር 3,253,520.61 የሱማሌ ክልል ወሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በሱማሌ ክልል ለሚገነባው የኳራንቲን ጣቢያ የውሃ መስመር ዝርጋታ ሥራ ለፈጸመው የቅድሚያ ክፍያ የክፍያ ሰርተፊኬት ቀርቦለት በወጪ እስኪመዘገብ ድረስ ክፍያውን በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4251 መመዝገብ ሲገባው የቅድሚያ ክፍያው እንደተፈጸመ በወጪ ሂሳብ መደብ 6323 በወጪ እንዲመዘገብ ያደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.10.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለግንባታ ሥራ የሚፈጸሙ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የክፍያ ሰርተፊኬትና የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገብ ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን የሚችል በመሆኑ የክፍያ ሰርተፊኬትና የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ ተደርጎ የክፍያ ሰርተፊኬትና የክፍያ ደረሰኝ ሲቀርብ በወጪ እንዲመዘገብ መደረግ እንዳለበት እሳስበናል፡፡

4.11 የተጨማሪ እሴት ታክስ በወቅቱ ባለመከፈሉ መቀጫ እና ወለድ ክፍያ መፈጸሙ፣

4.11.1 ግኝት

የገንዘብ ሚኒስቴር የካቲት 2002 በገቸው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም ባወጣው መመሪያ ቁጥር 27/2002 ክፍል 6 ተራ ቁጥር 4 ወኪሉ በወሩ ውስጥ ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ቀንሶ የያዘውን ታክስ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ገቢ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ሆኖም የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል መመሪያውን ተከትሎ ባለመፈጸሙ ከ2005 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ቀንሶ የያዘውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በወቅቱ ባለመክፈሉ ብር 88,621.89 መቀጫ እና ብር 76,975.00 ወለድ በድምሩ ብር 165,596.89 የከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.11.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ሆስፒታሉ በመመሪያው መሰረት የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በወቅት ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ካላደረገ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ከመሆኑም በተጨማሪ መንግሥት ለተጨማሪ ክፍያ እንዲዳረግ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ሆስፒታሉ ቀንሶ ያስቀረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በመመሪያው መሰረት ወቅቱን ጠብቆ ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ ማድረግ እንዳለበት እና ለቅጣትና ለወለድ ክፍያ ተብሎ የሚፈቀድ በጀት ሳይኖር ክፍያ መፈጸሙ ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች በጉዳዩ ላይ ሊጠየቁበት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.12 ተገቢነት የሌለው የስልክ ክፍያ፤

4.12.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የሚፈጽሟቸው የአገልግሎት ክፍያዎች በትክክል ለተቋሞቹ ጥቅም የዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤ በቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር ብር 8,634.78 እና በየቀድሞው ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 31,829.68 ለኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ከፈጸሙት ክፍያዎች ውስጥ በድምሩ ብር 40,464.46 ለሌላ (በጊፍት ፓኬጅ) በስጦታ የተላለፈ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.12.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የመንግሥት ገንዘብን በጊፍት መልክ ለሌላ በስጦታ ማስተላለፍ ለመንግሥት ገንዘብ አላግባብ መውጣት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ በስልክ አገልግሎት ክፍያ ላይ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡

በመሆኑም አላግባብ የተከፈለው የመንግሥት ገንዘብ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ክፍተት እንዳይፈጠር የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አሳሰበናል።

5 <u>በጀት</u>

5.1 <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት</u>፤

5.1.1 <u>ግኝት</u>

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ በ2010 በጀት ዓመት በየፕሮግራሞቹ ለመደበኛና ለካፒታል እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው የበጀት አጠቃቀም ሲመዛዘን ከ10% በላይ:-

- በሰላሳ ሰባት መሥሪያ ቤቶችና በዘጠኝ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር **671,605,097.90**፤
- በሃያ አራት መሥሪያ ቤቶችና በስምንት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከካፒታል በጀት ብር **2,830,281,457.21**፤
- በአምስት መሥሪያ ቤቶችና በሶስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከውስጥ ገቢ የወጪ በጀት ብር **78,566,535.87**፤

በድምሩ ብር 3,580,453,090.98 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 33 ተያይዟል)

5.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የመሥሪያ ቤቶቹን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ስለሚችል መሥሪያ ቤቶች ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደረጉ እንደሚገባ እና በተጨማሪም መሥሪያ ቤቶቹ የበጀት አጠቃቀማቸው ላይ ተገቢ የሆነ ክትትል በማድረግና የማይጠቀሙበትን በጀት ለይተው በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለባቸው አሳስበናል።

5.2 ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ፤

5.2.1 ግኝት

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ በ2010 በጀት ዓመት በየፕሮግራሞቹ ለመደበኛና ለካፒታል እንዲሁም ከውስጥ ገቢ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው የበጀት አጠቃቀም ሲመዛዘን:-

- በሰባት መሥሪያ ቤቶችና በአራት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር 6,431,375.28፤
- በሁለት መሥሪያ ቤቶች ከካፒታል በጀት ብር 244,918.50 ፤
- በአንድ መሥሪያ ቤት ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 775,032.57፤

በድምሩ ብር **7,451,326.01** ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶቹ) ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 33 ተያይዟል)

5.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትለው የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

6. ንብረት

6.1 የመሥሪያ ቤቶች የንብረት አስተዳደር መንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

6.1.1 ግኝት

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	8	1
ለአላቂ ንብረቶች እስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ያላቋቋሙ	5	2
ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	5	1
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	5	

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
በየስራ_ክፍሉ ለተሰጡ ቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ	5	2
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው(4 ላፕቶፕ፣1ኤልሲዲ፣5ፕሪንተር)	11	6
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	18	6
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	5	1
የለቀቁ ሰራተኞች(ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (በርካታ ንብረቶች በዋጋ ያላቸው)*	16	6

* በስምንት መሥሪያ ቤቶች ከሥራ ከለቀቁ ሰራተኞች (ኃላፊዎች) ብር **1,077,056.83** የሚያወጡ ንብረቶችን እንዲሁም በስድስት መሥሪያ ቤቶችና በሁለት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከሥራ የለቀቁ 110 ሰራተኞች (ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶችን ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 34 ተያይዟል)

በተጨማሪም የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ለአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በ2004 በጀት ዓመት ለተማሪዎች ቀለብ አገልግሎት የሚውል 50 ኩንታል ዛላ በርበሬ አንዱን ኩንታል በብር 4,000.00 ሂሳብ በጠቅላላው ብር 200,000.00 የሚያወጣ ዛላ በርበሬ በዱቤ የሸጠለት ቢሆንም ገዥው ገንዘቡ ያልከፈለ መሆኑ ከዚህም በተጨማሪ የአጋርፋ ኮሌጁ ከኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የግብርና መካናይዜሽን ዘርፍ አገልግሎት ጋር በ2007፣ 2008 እና በ2009 ዓ.ም በገባው ውል መሰረት ኮሌጁ ለድርጅቱ በብድር ከሰጠው ነዳጅ ውስጥ ብር 10,220.76 የሚያወጣ ነዳጅ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የአሰራር ክፍተቶቹ የመንግሥት ንብረቶችን ለብክነት የሚያጋልጡ እና ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት መስተካከል እና መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6.2. የመሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

6.2.1. <u>ግኝት</u>

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት			
	የመ/ቤቶች /ቅርንጫፍ	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች	ሌሎች*
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	8/7	43	19	1
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	12/4	238	33	20
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	14/4	215	6	
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	2/5	2	11	62
የሻንሲ ቁጥር የሌለው	1	1		
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ	2	2		
ድምር				

*ሌሎች፤- ሎቤድ፤ትራክተሮች፤ባጃጅ፤ቦክሰር፤ጂያንሺ፤ዞንግሽን ይጨምራል፡፡

(ለዝርዝራቸው አባሪ 35 ተያይዟል)

6.2.2. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- በወጣው የተሽከርካሪዎች መመሪያ መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ስለሚችል፣
- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሆኑ እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች የመሥሪያ ቤቶቹ ንብረቶች ናቸው ብሎ ለመቀበል ሊያስቸግር ስለሚችል፣

- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ካልተደረገ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ካልተደረገ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ ስለሚችል፣

መሥሪያ ቤቶቹ በተሽከርካሪዎቹ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ላይ የታዩትን ክፍተቶች በመመሪያው መሰረት ማስተካከል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

7. ልዩ ልዩ

7.1 እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት የተሰጠበት አጠቃላይ ገንዘብ፤ እርምጃ ተወስዶ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠንና ተመላሽ ያልተደረገ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ አባሪ-36 ተመልክቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2010

በጀት አመት ሂሳብ ኦዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

ሀ/የኦዲት ዳይሬክቶሬቶች ዕቅድና ክንውን

የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር፣

ተቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	12,842,622,949.23		12,842,622,949.23
2	ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት	628,166,550.00	50,315,456.00	678,482,006.00
3	ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	405,866,118.55		405,866,118.55
4	የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ	64,961,013.70		64,961,013.70
5	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ	107,376,450.00		107,376,450.00
6	የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	11,660,340.00		11,660,340.00
7	የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ	326,390,863.65	200,156,900.00	526,547,763.65
8	ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	100,935,303.00	-	100,935,303.00
9	የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን	29278310.00		29,278,310.00
10	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	849,405,877.00	981,710,111.14	1,831,115,988.14
11	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	633,963,821.50	600,000,000.00	1,233,963,821.50
12	የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ	42,420,471.00	----	42,420,471.00
13	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	2,463,937,836.06	670,000,000.00	3,133,937,836.06
14	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	42,442,040.73	134,472,633.18	189,122,673.18
15	የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ም/ ቤት	14,773,793.88	-------	14,773,793.88
16	ንግድ ሚኒስቴር	99,803,232.73	2,855,000.00	102,658,232.73
17	የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	129,610,902.27	3,653,555.55	133,264,457.82
18	የውጭጉዳይ ሚኒስቴር	2,753,938,771.58	253,336,332.06	3,007,275,103.64
19	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	311,939,995.12	27,024,413.60	338,964,138.72
20	የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	56,054,560.00	-----	56,054,560.00

ተ ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
21	የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት	14,909,260.00	----	14,909,260.00
22	የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	62,876,140.00	----	62,876,140.00
23	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	57,886,324.00	---	57,886,324.00
24	የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት	20,236,250.00	----	20,236,250.00
25	የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን	29,178,129.89	----	29,178,129.89
26	የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	27,263,350.00	157,324,750.00	184,588,100.00
27	የቀድሞው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር	91,892,604.50	-----	91,892,604.50
28	የፌዴራል የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ	62,445,470.00	-----	62,445,470.00
29	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ	63,120,622.47	65,771,000.00	128,891,622.47
30	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	28,988,376.00	39,422,000.00	68,410,376.00
		22,374,345,726.86	3,186,042,151.53	25,560,387,878.39

ለ/ የ2010 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ለተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች፣

በንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ኦዲት ለተደረጉትና ኦዲታቸው ለተጠናቀቁት 30 መ/ቤቶች የኦዲት ሪፖርቶች የተላኩ ሲሆን፣

- ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት /Adverse opinion/ የተሰጣቸው 8 መ/ቤቶች፣
- ከጥቂት ስህተቶች ወይም ጉደለቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሂሣባቸው አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት(Except for opinion) የተሰጣቸው 16 መ/ቤቶች
- ነቀፌታ የሌለበት ኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 2 መ/ቤቶች
- አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 4 መ/ቤቶች **(ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተመልክቷል)**

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. **የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ፤**

1.1 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፤

የጥሬ ገንዘብ በመመሪያው መሰረት በአግባቡ የሚያዝ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- **በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤** ብር 810,060.38 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት መገኘቱ ታውቋል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች የታዩባቸው መ/ቤቶች

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

- ብር 309,000.00 በቼክ ወይም በባንክ በማስተላለፊ መከፈል ሲገባው በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መሆኑን ፤-(**አባሪ 2**)

1.3 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ (4101) የመነሻ ሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገባቸው

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

- በ2009 በጀት ዓመት የመዝጊያ ሂሳብ (Closing Balance) ሆኖ የሚታይ በሂሳብ መደብ 4101 የተያዘ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ብር 10,037.61 እና በሂሳብ መደብ 5601 የተያዘ የተጣራ ሀብት ብር 67,785.40 በ2010 በጀት ዓመት የመነሻ ሂሳብ (Opening Balance) ሆኖ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡(**አባሪ 3**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር የቁጥጥር ስርዓትን በማጠናከር በመመሪያው መሠረት ክፍያ ሊፈፀም እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

1.4 የተጣራ ሀብት ሂሳብ፤

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

በ2009 በጀት ዓመት የመዝጊያ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 5601 የተያዘ የተጣራ ሀብት ብር 67,785.40 በ2010 በጀት ዓመት የመነሻ ሂሳብ (Opening Balance) ሆኖ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 4**)

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤

የተጣራ ሀብት ብር 3,389,217.65 ከመደበኛ ሚዛን ውጭ በዴቢት ሪፖርት መደረጉ ታውቋል፡፡ (**አባሪ 4/1**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የመነሻ ሂሳቦች በአግባቡ እንዲያዙ እና ተገቢው የማስተካከያ ምዝገባ እንዲከናወን ክትትል መደረግ እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

1.5 የሌተር ኦፍ ክሬዲት ሂሳብ፤

በሀገር መከላከያ ሚ/ር

በሰኔ 30/2010 ተጠቃሎ በቀረበው የሂሳብ ሪፖርት በተገለጸው መሠረት በሂሳብ መደብ 4104 የተያዘ ብር 2,800,963,673.52 ሌተር ኦፍ ክሬዲት እንዲከፈት የተፈቀደበት ደብዳቤ፣ ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተላቸው ድርጅቶች ዝርዝር እና ከድርጅቶቹ ጋር የተገባው ውሉ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በሂሳቡ የሚታየው ከፍተኛ ገንዘብ ክትትል ተደርጎበት እንዲወራረድ እና በሪፖርት እንዲገለፅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.6 የባንክ ሂሳብ፤

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት፤

- ከተለያዩ አካላት ገቢ የተደረገ እና በሰኔ 30/2010 በባንክ ሂሳብ የሚታይ ብር 74,913,188.22 በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫ እንዲካተት አለመደረጉ ታውቋል፡፡
- ከተለያዩ አካላት ገቢ የሚደረገው የአደራ ገንዘብ በባንክ ሂሳብ መደብ "D" ብቻ ማንቀሳቀስ ሲገባው ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የበጀት ማንቀሳቀሻ በተከፈተው በባንክ ሂሳብ መደብ ‹‹B›› አለአግባብ ገቢና ወጪ የሚያደርግ መሆኑን፣ (አባሪ 6)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በየወሩ በሚቀርበው የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መሰረት ገቢው እንዲመዘገብ እና በሂሳብ ሪፖርት እንዲካተት መደረግ እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

1.7 ሌሎች የባንክ ሂሳብ አያያዝ ችግሮች

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት

ከተለያዩ አካላት ገቢ የሚደረገው የአደራ ገንዘብ በባንክ ሂሳብ መደብ "D" ብቻ ማንቀሳቀስ ሲገባው ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የበጀት ማንቀሳቀሻ በተከፈተው በባንክ ሂሳብ መደብ ‹‹B›› አለአግባብ ገቢና ወጪ የሚያደርግ መሆኑን፤-(**አባሪ 6/1**)

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ በፊደል (መ) ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባው እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ፣</u>

በ19 መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት የቆየ፣ ብር 111,228,104.53
- ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሆነው፣ ብር 252,700,940.22
- ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የቆየ፣ ብር 1,497,321.29
- ከአስር ዓመት በላይ የሆናቸው ብር 308,163.30
- በቆይታ እድሜው ያልተተነተነ ብር 3,848.00

በድምሩ ብር 365,738,378.14 የተሰብሳቢ ሂሳብ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ (**አባሪ 7**)

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

ተሰበሳቢ ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት ተገልጿል፡፡

2.2 <u>ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

በ8 መ/ቤቶች ብር 1,271,954,606.21 ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 7/1**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በተሰብሳቢ ተይዞ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብለት እና እንዲወራረድ፣ ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.3 **<u>ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የተያዘ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>**

<u>በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤</u>

በሂሳብ መደብ 4253 ለዕቃ አቅራቢዎች የቅድመ ክፍያ በተቀጽላ ሌጀር (001) የተያዘ ብር 21,597.00 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡(**አባሪ 7/1**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በተሰብሳቢ ተይዞ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብለት እንዲወራረድ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.4 **<u>ያለ አግባብ የተሰረዘ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>**

<u>በሀገር መከላከያ ሚ/ር</u>

በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተሰብሳቢ ተይዞ የቆየ ብር 9,712,330.24 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር እንዲሰረዝ ቢደረግም ማስረጃው ባለመቅረቡ በመመሪያው የተገለፁት መስፈርቶች መሟላታቸው ተረጋግጦ ሂሳቡ መሰረዙን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (**አባሪ 7**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ከመዝገብ የተሰረዙት ተሰብሳቢ ሂሳቦች በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ መሠረት በተገቢው ማስረጃ ሊደገፉ ይገባል፡፡ በመሆኑም የተሰረዙ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ማስረጃው ለኦዲት እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.5 **<u>የተቀፅላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>**

በ2 መ/ቤቶች ብር 278,956,906.64 ተቀፅላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተሰብሳቢ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 7**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በተሰብሳቢ ለተያዘው ሂሳብ የተቀፅላ ሌጀር እንዲዘጋጅ በማድረግ ሂሳቡ ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

2.6 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በተጣራ ሀብት የተመዘገበ

በንግድ ሚኒስቴር፤

ለውሎአበል እና ለመጠባበቂያ በቅድሚያ የተከፈለ ብር 60,574.43በሚመለከታቸው ኃላፊ ስም በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በተጣራ ሀብት እንዲመዘገብ መደረጉን፤ (**አባሪ 4**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በተጣራ ሂሳብ መመዝገቡ አግባብ ባለመሆኑ ለሂሳቡ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

3 የገቢ ሂሣብ፣

3.1 ያልተሰበሰበ ገቢ፣

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት

- የታላቁ ህዳሴ ግድብ 7ኛ ዓመት የምስረታ በዓልን አስመልክቶ በተዘጋጀው "ስለ አባይ እሮጣለሁ" የገቢ ማሰባሰቢያ የሩጫ ውድድር ተሳታፊዎች ለሽያጭ ከቀረቡ ቲሸርቶች ገቢ መደረግ የሚገባው ብር 10,652,490.00 የአደራ ገቢ አለመደረጉን እና በሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑን፤
- ለፅ/ቤቱ ኃላፊዎች ከተከፈለው የቤት አበል ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ብር 13,650.00 ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር፤

ከመ/ቤቱ ኃላፊ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የመንግሥት የህክምና መዋጮ ብር 1,404.72 በመመሪያው መሰረት ገቢ አለመሰብሰቡ፤

በድምሩ ብር 10,667,544.72 ያልተሰበሰበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡(**አባሪ 9**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማናቸውም የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በአግባቡ ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

3.2 የተለያዩ የገቢ አያያዝና አመዘጋገብ ችግር የሚታይባቸው መ/ቤቶች

<u>የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት ወይም ያልቀረበለት የገቢ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

<u>በንግድ ሚኒስቴር፤</u>

- ብር 14,318,571.95 በገቢ ማጠቃለያ ደረሰኝ (ሞ/64) የተጠቃለለ ሲሆን ገቢ የተሰበሰበበት የገቢ ደረሰኝ ለኦዲት አለመቅረቡ
- የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር 6311531.90 ገቢ ለመደረጉ የባንክ ገቢ ደረሰኝ ያቀረበለት በመሆኑ፣

በድምሩ ብር 20,630,103.85 የገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ገቢው የተሰበሰበበት ደረሰኝ ባለመቅረቡ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡በመሆኑም ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ የሥራ አመራሩ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ (አባሪ 9/1)

3.3 <u>የማስከፈያ የዋጋ ተመን /ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ፣</u>

<u>በፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር</u>

ብር 158,805.00 ከተለያዩ አገልግሎቶች ገቢ የተደረገ ቢሆንም የገቢ ተመን ካልወጣላቸው አገልግሎቶች የተሰበሰበ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ ታውቋል፡፡ (አባሪ 9/2)

3.4 <u>በተመኑ መሠረት ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ፤</u>

ተመን ከወጣላቸው አገልግሎቶች መሰብሰብ የሚገባው ገቢ ብር 31,400.00 ሲሆን ተመኑን ሳይጠብቅ በተለያየ የገንዘብ መጠን ብር 19,125.00 ገቢ በመደረጉ ብር 12,900.00 በተመኑ መሠረት ሳይሰበሰብ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ (አባሪ 9/3)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ያልተሰበሰበው ገቢ በተመኑ መሰረት ገቢ እንዲደረግ እና የክፍያ ተመን ያልወጣላቸው የአገልግሎት አይነቶች ተመን እንዲወጣላቸው በማድረግ እና ተገልጋዮች ለተመሳሳይ የአገልግሎት አይነቶች ተመሳሳይ ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ ተገቢው የገቢ አሰባሰብ ሥርዐት ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.5 አለአግባብ በገቢ የተመዘገበ ሂሳብ፤

ብር 19,495.27 ከአበል ቅድሚያ ክፍያ እንዲሁም ብር 134,233.92 ከተለያዩ ቅድሚያ ክፍያዎች ተመላሽ የሆነ በድምሩ ብር 153,729.19 በገንዘብ ገቢ ደረሰኝ በተሰብሳቢ የሂሳብ መደብ 4201 ክሬዲት የተያዘ ቢሆንም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በገቢ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 9/4**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

አላግባብ ለተመዘገበው ገቢ የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ በማከናወን ወጥነት ያለው የሂሳብ እንቅስቃሴ ሥርዐትን ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

4 የወጪ ሂሳብ፣

4.1 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣

በ11 መ/ቤቶች ብር **21,919,376.34** የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤-(አባሪ 17)

4.2 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ የወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች፤

በ7 መ/ቤቶች ብር **106,944,766.04** ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን እና የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ ታውቋል፡፡(**አባሪ 18**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማስረጃ ላልቀረበላቸው ወጪዎች ማስረጃ እንዲቀርብ ይህ ካልሆነ ግን ገንዘቡ ከሚመለከታቸው አካላት ተመላሽ መደረግ እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣

በ13 መ/ቤቶች ብር 20,655,586.50 ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡- (**አባሪ 19)**

የማሻሻያ ሀሳብ፣

መመሪያን ያልተከተሉ ክፍያዎች እና ግዥዎች እንዲፈፀሙ እና አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ያደረጉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል በተጨማሪም፡፡

ክፍያዎች በመንግስት የአከፋፈል መመሪያዎች እና ደንቦች መሠረት እንዲፈፀሙ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

4.4 በበጀት ዓመቱ ዕቅድ ሳይያዝለት የተከናወነ ክፍያ

በ2 መ/ቤቶች በዕቅድ ያልተፈፀሙ ግዥዎች ለተፈፀሙበት ብር 50,245.50 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 33)**

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥዎችን አስቀድሞ በማቀድ መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ አንዲያውሉ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

4.5 በበጀት ዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ በላይ የተከናወነ ግዥ፤

በፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር፤

በበጀት ዓመቱ የግዥ ዕቅድ መሠረት 31 ቶነሮችን በብር 20,498.75 እንዲገዙ መደረግ ሲገባው 300 ቶነሮች በብር 198,375.00 በመግዛታቸው ከዕቅድ ውጪ የ269 ቶነሮች ግዥ በመፈፀሙ ብር 177,876.25 የግዥ ዕቅድን በመተላለፍ አለአግባብ ግዥ መፈፀሙን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ (**አባሪ 14)**

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከዕቅድ ውጪ ግዥ እንዳይፈፀም እና ንብረቶች በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውሉ ተገቢው ክትትል ባለመደረጉ የፋይናንስ እና ግዥ ክፍል ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል፡፡

4.6 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፤

ለብሔራዊ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አበል በሚል ለተፈጸመው ክፍያ የጸደቀ የክፍያ ተመን ሳይቀርብ በድምሩ ብር 173,900.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡(**አባሪ 19/3**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ክፍያው በሚመለከተው አካል የጸደቀ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡ በመሆኑም ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

4.7 ስልጣን ባለው አካል ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች፤

በ6 መ/ቤቶች በሚመለከተው አካል ሳይፈቀዱ ብር 744,625.82 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡(**አባሪ 26**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በደንቡና መመሪያው መሠረት በሚመለከተው ሥልጣን በተሰጠው አካል የተፈቀደ ለመሆኑ ተጣርቶ መከፈል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.8 በብልጫ የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎች፣

በ5 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዥዎች ብር 2,829,603.35 እንዲሁም ለውሎ አበል ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች ብር 415,153.28

በድምሩ ብር 3,244,756.63 ያለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 20**)

4.9 በውላቸው መሠረት ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች

የመሠረተ ልማት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቀው ለታቀደላቸው ዓላማ መዋላቸውን ወይም አገልግሎት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የሚያስገነባቸው ህንፃዎች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ3 እስከ 5 ዓመት የዘገዩ መሆኑን፣
- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የሚያስገነባቸው ህንፃዎች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ1 እስከ 3 ዓመት የዘገዩ መሆኑን፣ (**አባሪ 20/5**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለታቀደላቸው ዓላማ እንዲውሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.10 ከሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች ያለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ

በ2 መ/ቤቶች ብር 79,364.61 መ/ቤቶቹን ለለቀቁ ሰራተኞች አለአግባብ ደመወዝ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 19/1**)

4.11 <u>የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች</u>

በ19 መ/ቤቶች

• ያለጨረታ በቀጥታ የተገዛ	ብር	100,865,666.09
• መስፈርቱን ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ	ብር	756,503.78
• በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ	ብር	351,532.48
• የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ	ብር	1,809,791.45
• ሌሎች የግዥ ሂደትን ያልተከተሉ	ብር	29,360 862.22
በድምሩ	ብር	133,144,356.02

የግዥ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 21**)

4.12 <u>በናሙናው መሠረት ለመግባቱና አገልግሎት ለመሰጠቱ ያልተረጋገጠ፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣</u>

የላፕቶፕ ኮምፒውተሮችን የማዕቀፍ ግዥ አቅራቢ ከሆነው ከብርጂቲክስ ኃላ/የተ/የግል ማኅበር በብር 127,290.05 ግዥ የተፈጸመ ሲሆን፣ ኤጀንሲው በላከው የተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር መሰረት መቅረቡ በባለሞያ ሳይረጋገጥ ገቢ መደረጋቸው በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ (አባሪ 21/1)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ንብረቶች ገቢ ከመደረጋቸው በፊት በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሠረት መቅረባቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4.13 **በንብረት ገቢ ደረሰኝ ላይ የዕቃው ብዛት ፣ዓይነትና ዋጋው ያልተገለጸ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር፤**

በኒውዮርክ ኤምባሲ ብር 297,674.69 እንዲሁም በዋሽንግተን ብር 312,702.72 በድምሩ ብር 610,377.41 የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ የተፈፀመ ሲሆን በንብረት ገቢ ደረሰኝ ላይ የዕቃው ብዛት፣ ዓይነትና ዋጋው ባለመገለፁ የግዥውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡(አባሪ 22/ለ)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በንብረት ገቢ ደረሰኞች ላይ ተገቢው ዝርዝር መረጃ እንዲገለፅ መደረግ ይኖርበታል፡

4.14 **<u>ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች</u>**

በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 26,576,551.11 ለተገዙ ዕቃዎች ወጪ የተደረገ ሲሆን ንብረቶቹ በመ/ቤቶቹ ግምጃ ቤት ገቢ ሳይደረጉ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ ታውቋል፡፡(አባሪ 22)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ንብረቶች ገቢ ሳይደረጉ ሂሳቡ በወጪ በመያዙ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ንብረቶቹ አገልግሎት ላይ ለመዋላቸው ማረጋገጫ እንዲቀርብ ወይም ገንዘቡ ከሚመለከተው አካል ተመላሽ እንዲሆን ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.15 **<u>ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተመዘገበ ወጪ የተገኘባቸው መ/ቤቶች፣</u>**

በ6 መ/ቤቶች ብር 2,560,056.19 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡ **(አባሪ 24)**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍያዎች በጀት በተፈቀደበት በጀት ዓመት ውስጥ እንዲፈፀሙ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.16 **<u>የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ፣</u>**

በ15 መ/ቤቶች ብር 158,802,710.30 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡ **(አባሪ 25)**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የወጪ ሂሳቦች በወጪ ከመመዝገባቸው በፊት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ለመያዛቸው መረጋገጥ እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

4.17 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

በ3 መ/ቤቶች ብር 7,763,662.31 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ ታውቋል፡፡ (**አባሪ 28**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው፣ ዕቃዎቹ ገቢ ሳይደረጉ ሂሳቡ በወጪ እንዲመዘገብ በመደረጉ የፋይናንስ አያያዝ ሥርዐትን ያልተከተለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ክፍያዎች በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.18 <u>በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የትርፍ ሰዓት ክፍያ</u>

በ2 መ/ቤቶች ብር 159,256.97 በሚኒስቴር መ/ቤቱን ሳይፈቅድ ከመመሪያ ውጭ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡(**አባሪ 19/4**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

አለአግባብ የሚከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያው እንዲቆም መደረግ ይኖርበታል፡፡ ገንዘቡም ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

4.19 <u>ሰነዱ ለኦዲት ሊቀርብ ባለመቻሉ የወጪውን /ሂሳቡን/ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፤</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤

ንብረታቸው ለወደመባቸው ተቋማት የፋይናንስ ድጋፍ የተከፈለ በድምሩ ብር 134,472,633.18. በሂሳብ መደብ 6412 በወጪ የተያዘ ሲሆን፤ የጉዳቱን መጠን የሚገልፅ ጥናት፤ ገንዘቡ ለሚመለከታቸው አካላት መከፈሉን የሚገልፅ ማስረጃ እንዲሁም ኮሚሽኑ የጉዳት ካሣ ከሚከፈላቸው ድርጅቶች ጋር የገባቸው ውሎች ለኦዲቱ ባለመቀረባቸው የወጪ ሂሳቡን ኦዲት ለማድረግ አልተቻለም፡፡

በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 10,165,689,259.81 ሰነዶቹ ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡ (አባሪ 18)

4.20 በወጪ ሂሳብ ሪፖርቱ ያልተካተተ የወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው፤

በህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋል የኦሮሚያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፤

የ2010 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት እና ከመዝገቡ ጋር ሲነጻጸር የወጪ ሒሳብ በመዝገብ መሠረት ብር 5,387,460.00 ሲሆን በሂሳብ ሪፖረቱ መሠረት ብር 5,286,250.13 በመሆኑ ብር 190,911.83 በሂሳብ ሪፖርቱ ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.21 በወጪ ሂሳብ ላይ የታዩ ዋና ዋና የአሰራር ድክመቶች፤ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) በአግባቡ ባለመመዝገቡ ሰኔ 30,2010 በተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት የተገለፀውን የወጪ ሂሳብ ብር 4,592,514.46 ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- **የውጭ ጉዳይ ሚ/ር**

  በተጠቃለለው የሂሳብ ረፖርትና ሚሲዮኖች ባቀረቡት የሂሳብ ሪፖረት መካከል የታየ ልዩነት ብር 249,600.00
- **የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት**
  - በየሥራ ክፍሎች የሚገኙ የቀጥታ ስልኮች የፍጆታ ተመን ያልወጣላቸው መሆኑን፤
  - የዋና ዳይሬክተር የመስመር ሞባይል ስልክ የክፍያ ጣሪያ ያልተቀመጠለት መሆኑን፤
  - የምክትል ዳይሬክተሮች የሞባይል ካርድ ግዥ ገደብ ያልወጣለት መሆኑን፤

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የልዩነቱ መንስዔ በውስጥ ኦዲት በኩል ተጣርቶ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ልዩነት በታየባቸው የሂሳብ መደቦችና የታዩት ክፍተቶች ላይ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ እንዲከናወን እና እንዲታረም መደረግ ይገባዋል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

የተከፋይ ሂሣቦች በወቅቱ ለባለመብቱ የሚከፈሉ መሆኑን እና የተከፋይ ሂሣቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

5.1 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

በ5 መ/ቤቶች የቆይታ ግዜያቸው

• ከአንድ ወር እስከ አንድ አመት የቆዩ	ብር	45,306,898.32
• ከ አምስት ዓመት እስከ አስር አመት የቆዩ	ብር	82,987.69
• የቆይታ ጊዜው ያልተተነተነ	ብር	59,840,598.84
በድምሩ	ብር	105,230,484.85

የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ሳይወራረድ መገኘቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ (**አባሪ 30**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ተከፋይ ሂሳቦች ለባለመብቶቹ በወቅቱ እንዲከፈሉ የሚመለከተው አካል ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

በ8 መ/ቤቶች ብር 238,155,942.53 በተከፋይ የተያዘ እና ማስረጃው ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ (**አባሪ 31**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማስረጃ ላልቀረበላቸው ተከፋይ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ እና ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ መደረግ ይገባዋል፡፡

5.3 መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) የሚታይ ተከፋይ ሂሳብ

በ2 መ/ቤቶች ብር 20,304,270.08 ባልተለመደ ሚዛን የተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 32**)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ በማከናወን የተከፋይ ሂሳቦች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዲያሳዩ መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.4 የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው ተከፋይ ሂሳቦች የተገኘባቸው፤

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ብር 110,578,538.31 ከተቋራጮች ለተቀነሰ የመያዣ ክፍያ የተቀፅላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት የተከፋይ ሂሳብ መገኘቱ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በተከፋይ ለተያዘው ሂሳብ በእያንዳንዱ ተቋራጭ ሥም ተቀፅላ ሌጀር ተዘጋጅቶለት እንዲመዘገብ መደረግ ይገባዋል፡፡

6. <u>የበጀት አጠቃቀም፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያው መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

6.1 <u>ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ፣</u>

በተለያዩ የወጪ አርእስቶች ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ በመደረጉ፣

• ከመደበኛ በጀት በ6 መ/ቤቶች	ብር	7,260,636.94
• ከካፒታል በጀት በሁለት መ/ቤቶች	ብር	20,292,559.69
በድምሩ	ብር	27,553,196.63

ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ (**አባሪ 33**)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በጥናት ላይ የተመሰረተ የበጀት ዕቅድ በማዘጋጀት የተፈቀደለትን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲያውል እና አስቀድሞ የተፈቀደ በጀት አለመኖሩ ሲረጋገጥ በዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ በቂ በጀት እንዲኖር በማድረግ ክፍያ እንዲፈፀም መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ፣

በተለያዩ የወጪ አርእስቶች የተፈቀደው በጀት ስራ ላይ ያልዋለ በመሆኑ፤

- ከመደበኛ በጀት በ17 መ/ቤቶች ብር 1,291,626,235.28
- ከካፒታል በጀት በ8 መ/ቤቶች ብር 761,269,776.16

በድምሩ ብር 1,923,936,803.68

ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ (አባሪ 33)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተፈቀቀደው በጀት በመመሪያው መሰረት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል የሥራ አመራሩ ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

6.3 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣

በ5 መ/ቤቶች ብር 1,232,709.87 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ ለተፈፀሙ ክፍያዎች ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡(አባሪ 35)

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ወጪ ከመደረጉ በፊት በደንቡ መሠረት በጀት ስለመኖሩ በበጀት ክፍል መረጋገጥ እንደሚገባው ተገልጿል፡፡

7. የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 6/1/ለ እና 11/1 የቋሚ ንብረት አስተዳደር በተመለከተ እንዲሁም የመመሪያው አንቀጽ 16 የስቶክ አስተዳደርን በተመለከተ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለበት በታዘዘው መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ቀጥለው የተመለከቱት የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች፤መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ (ከአባሪ 34)

7.1 የቋሚ ዕቀዎች አያያዝ ችግሮች

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች
ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	8
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	4
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	2
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	2
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	2
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	8
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	11
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	2
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	3
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (7 ለፕቶፕ፣ ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር 13,200.00 ይገኙበታል)	3

ሌሎች ያለአገልግሎት የተጠቀመጡ ንብረቶች

ንግድ ሚኒስቴር፡

- ለስብል ምርት መሸኛ ህትመቶች በጥራዝ፣ የነዳጅ ማደያ መመርመሪያ ሜትር በጥራዝ፣ የንግድ ምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ እና ሌሎችም
- ለጥራት ፍተሻ የተገዙ ብዛት ያላቸው ቆርቆሮዎች፣ ምስማር፡ የቅባት እህሎች ብረቶች እና የኤሌክትሪክ እቃዎች ጠረጴዛዎች ፕሪንተሮች የእንግዳ ወንበሮች
- የሰራተኛ ወንበሮች፣ ጋዜጣዎች፣ ቴሌቭዥን፣ ላፕቶፖች፣ 10 የስነልክ ሚዛኖች እና የተለያየ መጠን ያላቸው የሚዛን ድንጋዮች

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በንብረት አያያዝ አመዘጋገብ አጠባበቅ እና አጠቃቀም ረገድ የተዩ ችግሮች እንዲቀረፉ እና የመንግስት ንብረት ለታቀደለት ዓላማ እንዲውል ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እና ለወደፊቱም ክትትል ሊደረግበት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ (አባሪ 35)

7.2 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም፣

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	5	20	
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	7	58	1
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	1	1	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	2	56	
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	1	1	
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጅ	1		
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1	7	

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በተሽከርካሪዎች አያየዘዝ እና አጠባበቀቅ በታዩ የአሠራር ክፍተቶች ላይ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ በአግባቡ አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ ይኖርበታል፡፡

7.3 ሌሎች የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅ ክፍተቶች፤

ንግድ ሚኒስቴር

ላፕቶፖች ለተጠቃሚዎች ወጪ ሆነው ሲሰጡ መለያ ቁጥሮቻቸው የተገልጋይ ካርዱ /user card/ ላይ የማይጠቀስ መሆኑ፣

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት

- ❖ ብር 3,990.00 ዋጋ ያለው ሀርድ ዲስክ በቋሚ ንብረት መመዝገብ ሲገባው በአላቂ ዕቃ ወጪ ደረሰኝ ለአገልግሎት ወጪ መደረጉን፤
- ❖ 17 የጽ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ከጽ/ቤቱ ግቢ ውጭ እንዲያድሩ የሚደረግ በመሆኑ ደህንነታቸው በአግባቡ መጠበቁንና ለፅ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ መዋላቸውን ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑን፤
- ❖ ለስራ ክፍል ዳይሬክተሮች የሰርቪስ አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ወርሀዊ የነዳጅ ፍጆታ ተመን ያልወጣላቸው መሆኑ፣

❖ የጽ/ቤቱ 21 ሰራተኞች እያንዳንዳቸው ላፕቶፕ እና ዴስክ ቶፕ ሁለቱንም ኮምፒዩተሮች በስማቸው ወጪ አድርገው መያዛቸውን፣

ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

➢ በግምጃ ቤት እና በተጠቃሚዎች እጅ የሚገኙ የጦር መሳሪያዎች እንደ ቋሚ ንብረት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ አለመቻሉን፣

የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር

➢ በብር 96,600.00 የተገዙ 10 ጎማዎች በዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ ተደርገው ለአገልግሎት ወጪ ቢደረጉም አገልግሎት ላይ አለመዋላቸውን፣

8 <u>ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣ (አባሪ 49</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተመላሽ እንዲሆን አስተያየት የተሰጠበት አጠቃላይ ገንዘብ፣ እርምጃ ተወስዶ ተመላሽ የተደረገ የገንዘብ መጠንና ተመላሽ ያልተደረገ ቀሪ ገንዘብ በተመለከተ አባሪ-36 ተመልክቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰዱ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፣ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፣ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወሰዱ፣ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡